ጥቁሯ ፓይለት
በጀርመን

ልብ ወለድ

ከብሩክ ከበደ
ብሬመን ጀርመን 1990 ዓ.ም ተጻፈ።

አዲስ አበባ፣ 1996 ዓ.ም

© ብሩክ ከበደ 1996

Biruk Kebede
Theodro Storm St. 7A
28201 Bremen
GERMANY

መታሰቢያ

ለውድ እናቴ

ለወይዘሮ ብዙወርቅ ወልዴ

ለውድ አጐቴ

ለሻንበል አፈወርቅ ዮሐንስ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ ቅንብር – ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
Computer Typesetting and Design – Ethiopia Book Centre


ምስጋና

- የመጽሐፉን የሕትመት ሥራ ለማስፈጸም ሙሉ ፍቃደኛ ሆነው ውክልናውን በመውሰድ ለሕትመት ላበቁልኝ ለአቶ ብርሃኑ ገብረ ሕይወት፣
- የውጭውን የሽፋን ሥዕል ለሣሉልኝ ለ Mr. Leonid Jssaev፣
- የውስጡን የተለያዩ ሥዕሎች ለነደፉልኝ ለ Mr. Anila Hossain፣

ረቂቁን አንብበው ሰሕተቶችን እንዳስተካክል ምክርና እርማት ለሰጡኝ፣

- ለወይዘሪት ሊያ ይብራሕምና ለአቶ ሰሎሞን ውብ አየለ፣
- ሕግን በተመለከተ ጉዳይ ላማክሩኝ ለMr. Bernd Hollmann፣
- የመጽሐፉን መግለጫ ለጻፉልኝና በቶሎ እንዳሳትመው የሞራል ድጋፍ ለሰጡኝ ለዶክተር ፍቃዱ በቀለና ለውድ ባለቤታቸው ለወ/ሮ ቦሰና ንጉሤ፣
- በአጠቃላይ ለሌሎችም ስማቸውን ላልጠቀስኳቸው ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ደራሲው



ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ከሰድስት ዓመት በፊት፣በ1990 ዓ.ም አካባቢ ነው በዚህ ልዩ ምክንያቶች እስከአሁን ሳይታተም ቆይቷል።

ስለዚህ አንባብያን ታሪኩን በዛን ጊዜ ከነበረው ወቅታዊ ድርጊቶችና ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ እንዲያነቡት ደራሲው በትህትና ያሳስባል።



ክፍል አንድ

ሰሜናዊ ጀርመን የበጋ ምሽቱ የነጋ ነው። ጊዜው መሸቶ ጀንበር አትጠልቅም። ወራቱ ሞቃት ቢሆንም ምሽቱ ይበርዳል።

ብሬመን (Bremen) የምትባለው የጀርመን ትንሿ ክፍለ ሀገር የምትገኘው በዚሁ አካባቢ ነው። ከተማዋ በሁለት ሰፋሪ ወንዞች መሐል ሆና ከቀትሩ ሀሩር ለማሸለብ ተዘጋጅታለች።

ብሬመን በሰሜን በኩል ሁለት የባሕር ወሽመጦች ያዋስኗታል። ቀዝቃዛው አየር ከዛ ሰፊ ባሕርና ከሁለቱ ጠባብ ወንዞች እየተነነና እየተራደ መጥቶ ይነፍሳል።

በየመንገዱ ጠርዝ ዳርና ዳር በመደዳ የሚታዩት ዛፎች ደማቅ አረንጓዴ ቅጠላቸውን አንዠርገዋል። የተፈጥሮ ውበትን ተጐናጽፈው እስክስታ እንደሚወርድ ቅጠልና ቅርንጫፋቸው በንፋሱ እየተመታ ይርገፈገፋል። እነሱን አምሶና ዳሶ የመጣው ንፋስ የቀትሩን የቆየ ሙቀትና ላቦት ከሰውነት በለዘብታ እየዳሰሰ አራግቦ ያናፍሳል። ምሽቱን አበራርዶ የሰውን ድካም ወስዶ ብርታትን ለግሶ ያዝናናል።

በሰፊው ተስተካክሎ የተሠራው የመኪናና የሌላም ተሽከርካሪዎች አስፋልት በኑግ የታሰሰ ሰፊ ምጣድ መስሏል። የማታዋ ጀንበር ከምዕራብ በኩል እሰማዩ አድማስ ከንፈር ላይ የጋለ አሎሎ መስላ ተለጥፋለች።

ብልጭ ድርግም እያለ ዓይኖችን የሚያባብለው ጨረሯ ቬዘር (Weser) በሚባለው ወንዝ ላይ አርፎ ያብረቀርቃል። በዚህም ከተማዋ በወርቅ ቀለም የተለሰነች ውብ መስላለች።

ብሬመን እንደውበቷ የሚያምሩ አዳዲስና አሮጌ የባህር ወደቦች አሏት። (Neustadter Hafen) ከሚባለው አዲሱ ወደብ ላይ አምስት ትላልቅ መርከቦች መሐለቃቸውን ጥለው የምድሪቷን የባህር አፈር ደለል ተደግፈው ቆመዋል። ወዲያ ባሕሩ ላይ ከወዲያ ወዲህ የሚዋዥቁም ትንንሽ፣ ጀልባና መርከቦችም አሉ።

ደመና አልባ በሆነው የምሽቱ የጠራ ሰማይ ላይ የባህርና ሌላም የሰማይ በራሪ ወፎች በተለያየ ድምፅ እያስካኩና እየዘመሩ የባህሩን ሰፊ ሜዳ በክንፋቸው እየጨለፉ ይቀዝፉሉ። ከወዲያ ወዲህ ብር ብር እያሉ እርስ በእርሳቸው ይጫወታሉ። ዓሣ የሚበሉት ዓሣ አውጥተው ተሻምተው ይቀራመታሉ። የቀሩት አንድ ላይ እጅብ ብለው ወደ ሰማይ በጣም ተመንጥቀውና እርቀው ሲታዩ ለምሽቱ የቀረቡ ልዩ ትርኢት ይመስላሉ።

ዓለም አቀፍ የብሬመን አየር ጣቢያ (Flughafen) ሰፊ የአስፋልት ሜዳውን እንደ ባህር በሰፊው አንጣሎ በምሽቷ ጀንበር ጮራ ቆንጅቷል። ቦታው ከላይ አንጃበው ትኩስ አየር ተንፍሰው ቀዝቃዛውን እየገፈተሩ ዝቅ ብለው የሚመጡትን አይሮፕላኖች በተራ ተቀብሎ ያስተናግዳል። ወደ ላይ ወደ ራቀው፣ ሰማይ አቆብቅበው የሚመነጠቁትንም በሥርዓት ይሸኛል።

ብሬመን የባቡር ዋና ጣቢያም (Haubtbhanhof) አላት። ይህ ስፍራ ከልዩ ልዩ ሀገር የመጡ ደራሽ ወይም ወደሌላ ሀገር የሚሄዱ ገሥጋሽ፣ ባቡሮች ያሉበት ስፍራ ነው። በዘመናዊ ቴክኒክ የተሠሩ እነዚህ ያማሩ ባቡሮች በብረት ጐማቸው መንታ ሀዲዱን ጨብጠው በየመስመራቸው በመቆም ሕዝቡን ያስተናግዳሉ።

በአስፋልት ላይ የሚነዱ ሌላ ተሽከርካሪዎችም እንደጥበብ በተሣለው ነጫጭ የመስመር ክልል ተለይተውና አብረው ተሰልፈው ከወዲያ ወዲህ በተለያየ ፍጥነታቸው ይሽከረከራሉ።

አለቱ የሰንበት ቀን እሁድ በመሆኑ ብዙ የትራፊክ ግርግር ሩጫና ጥድፊያ ጨርሶ አይታይም። በበጋ ወራት ውጪ እየተዝናና የሚታየው የሕዝብ ብዛት አያሌ ነው። ያም ሆኖ ሁካታና ጩኸት እንብዛም ጐልቶ አይሰማም።

በዚህ ምሽት የብሬመንን የምሥራቅ ሥፍራ እሩቅ ባሻገር አተኩረው ሲመለከቱት ሰማይና ምድር ተገጣጥመው የሚሳሳሙ ይመስላሉ። ከዛ ከራቀና ከጨገገ የአድማስ ድንበር ሥርቻ አንዲት የሰርዲን ቆርቆሮ የምትመስል ነገር ብቅ ብላ ታየች። የምሽቱን የብርሃን ጨረር ተቀብላ መልሳ እያንፀባረቀች፣ መንገዱን በጐማዎቿ ምላስ እየሰለቀጠች በከፍተኛ ፍጥነት ገሥግሣ ወደ ከተማው እንብርት ተጠጋች። ያቺ በርቀት ሲያይዋት የሰርዲን ቆርቆሮ የመሰለችው፣ እየቀረበች ስትመጣ በግልጽ መታየት ጀመረች። ኢ ክላስ(E.Klasse) ማርቼዲስ ታክሲ መኪና ነበረች።


ይህች መኪና በዛ ግስጋሴና እሩጫ ፈጥና ቫለ ከሚባለው ከብሬመን አንዱ ቀበሌ ደረሰች። ኡት ብሬመን ከሚባለው ትልቅ ዋሻ (Tunnel) ጭንቅላቷን ዝቅ አድርጋ ሽው ብላ ገባች። ዋሻውን በሞተር ድምጿ አስደንግጣ ሽቅብ እየበረረች በሌላ በኩል የሲኦል አፍ ከመሰለው የገደል አስፋልት አፍ ውስጥ ብቅ ብላ ተተፍታ ደምቃ ወጣች።

የዚች መኪና አሽከርካሪ ጀርመን ሀገር ብሬመን ከተማ የምትኖር ቆንጅዬ ኢትዮጵያዊት ናት። መኪናዋን ዘወትር አፍጥና ስለምትነዳ ጥቁሯ ፓይለት ብለው ይጠሯታል። መልኳ እንደ ስሟ ጥቁር አይደለም። ጠይም ናት። ግን ጀርመኖች ጠይም ሆና የቀይ ዳማ ቆዳው እነሱን ካልመሰለ ሁሉንም በደፈና ጥቁር ብለው ነው የሚጠሩት። ይቺው የታክሲ መኪና አሽከርካሪ ሹፈር በቀጭኑ የተሠሩ ሹርባዋን ከወዲያ ወዲህ እየነሰነሰች ጥቁር የፀሐይ መነጽር አድርጋ መሪዋን ጨብጣ በጉልህ መታየት ጀመረች። ቆንጅዬ ጠይም ዓሣ መሳይ ኮረዳ ነች። መነጽሯን ከዓይኖቿ አውጥታ ግንባሯ ላይ ሰካችው። ትልልቅ ዓይኖቿ የብር ጉልላት ይመስላሉ። እንደ ምሽቱ ጀንበር ብልጭ ድርግም እያሉ ተመልካችን ያባብላሉ። ፈገግታዋ ልብ ይሰርቃል። ሰልከክ ብሎ ወደ ታች ባጭሩ የወረደው አፍንጫዋ ለገጽታዋ ግርማ ሞገሥ ሰጥተውታል። ጉንጮቿ ስርጉድ ብለው አፏን ወደ ፊት ገፈት በማድረግ ሞጥሞጥ ስላደረጉት ልክ የሲዳሞ ቆንጅዬ ትመስላለች። በስሱ ከርከም ብለው አበጥ ያሉት ከንፈሮቿ ያምራሉ። ግን ልማድ ሆኖባት አዋዜ በመሰለ

የከንፈር ቀለም ስለምትቀባቸው ገና የሚፈነዱ እንቡጥ ጽጌረዳ ይመስላሉ። ይህም የውበት አድራጐቷ ሌላ የቅጽል ስም አትርፍላታል። በሥራዋ ጥቁሯ ፓይለት፣ በውበቷ ሮዚ ተብላ ትጠራለች።

ሮዚ መኪናዋን እንደ ንፋስ እያበረረች B.75 አውራ ጐዳናን ይዛ በአልድንበርግ ሰፊ ጐዳና ወደ ታች ሸመጠጠች። የስቴፋኒን ድልድይ ተሰፈንጥራ አልፋ ወደ ፊት ገሠገሠች። ከላይዋ በሰማይ የሚበር ትልቅ ቦይንግ አይሮፕላን ጥላውን አጠላባት። ጠይሟ ቆንጆዬ ሹፌር ደብዘዝ ብላ የእምድሯ የጀርመን ጥቁር ፓይለት መስላ ታየች። አይሮፕላኑ ከላይ እሷ ከታች ሆነው ሁለቱም ባላቸው ፍጥነት ይበራሉ ይከንፋሉ። ሁኔታውን ልብ አድርጐ ለተመለከተ «እኔ ልቅደም እኔ ልቅደም» እያሉ የፍጥነት እሩጫ ውድድር የሚያደርጉ ይመስላሉ።

ሮዚ ፍጥነቷን ሳትቀንስ ቁልቁለቱን ወርዳ የትራፊክ መብራቱ እንዳጋጣሚ ፍጥነቷን እንደሉጋም ስቦ ባይገታው ኖሮ ላንደር ከተባለው ሰፊ ጐዳና ዘው ብላ ጥልቅ አለች። ትንሽ ተጉዛ ወደ ቀኝ በመታጠፍ የብሬመን ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ደረሰች። እንግዶቿን በተባለው ሰዓት በማድረሷ ደስ አላት። የሹፌርነት ድካሟን የታክሲ ሂሳቧን ተቀብላ እንግዶቿን በፈገግታና በጥሩ ምኞት ሰላምታ ተሰነባበተች። ሮዚ ጉርሻ ቢሰጧት ባይሰጧት ግድ የላትም። የምትጠላው ነገር ቢኖር የተሳፋሪዎችን ትልልቅ ሻንጣዎች አንድ በአንድ ተሸክማ መጫን ወይም ማውረድ ነበር። በእለቱ ግን ተሳፋሪዎቹ ወጣቶች በመሆናቸው ጓዛቸውን እራሳቸው በራሳቸው ስላጠናቀቁ የደስታ እፎይታ ተነፈሰች። የሚጻፈውን የእለቱን ተከታታይ የጉዞ ዋጋ (Fahrbericht) መዝግባ ትንሽ ተዝናናች። መኪናዋን ከአካባቢው ብዙም ሳትርቅ ፈቀቅ አድርጋ ከጥላው ሥር አቆመቻት። ሲጋራዋን ለኩሳ ሁለት ምስት ጊዜ ወደ ውስጥ ማግ ማግ አድርጋ ቦለለል የሚለውን ጭስ ለቀዝቃዛው አየር ላከችው። የሚያምሩ ዓይኖቿ አካባቢውን እያማተሩ ተመለከቱ።



የብሬመን የአይሮፕላን ማረፊያ የ60 ዓመት ልደቱን ለማክበር በመታደስ ላይ ይገኛል። ሀገሪቱ ሃብታም ባትሆንም የድህነት ገመናዋን ለመሸፈን የምታደርገውን ሽር ጉድ ተመልከታ ታዘበች። በብድር ገንዘብ በቅርቡ የተሠራውን የአትላንቲክ ሆቴልና ሌላም ብዙ እድሳቶች አይታ ተገረመች። በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጀምሮ በማለቁ አደነቀች። «ሀገርም እንደሰው» «ሳይታጠቁ ይከናነቡ» ብላ ተረተች።

ጩኸቱ እንደ ነጐድጓድ የጐላ፣ ድምጹ ውቃቢ የሚገፍ አስደንጋጭ የሉፍታንዛ ቦይንግ አይሮፕላን እምድሯን በጐማው ምላሱ ሊልስ አፍን ጫውን አሹሉና ወደታች ደፈት አድርጐ ቀረበ። ትላልቅ ክንፎቹ እንደጣረሞት ተንገፓርገው አየሩን ለሁለት ሰነጠቁ። ሞተሮቹ ግለው አካባቢውን በትንፋሻቸው ወላፈን አሞቁት። አንዱ ከሩቅ መጥቶ መሬት ነክሶ ሲቀዘቅዝ ሌላው ወደ ላይ አቆብቁቦ መሬት ለቆ ወደ ሰማይ እየበረረ ይመነጠቃል።

በዚህ ወቅት የሮዚ የሩቅ ትዝታ ከጂቱ ጋር አብሮ ተንሳቦ ርቆ ተመነጠቀ። በልጅነቷ የአየር ላይ አስተናጋጅ ለመሆን ታላቅ ምኞት ነበራት። አባቷ ግን «የአየር ላይ አለሌ ገረድ መሆን የለብሽም ከሆነ ሕግ አጥንተሽ ዳኛ ካልሆነም ጠበቃ መሆን ነው ያለብሽ» ብለው የመከሯት ትዝ አላት።

ሮዚ ፓይለት ለመሆን ባትመኝም ከቅርብ ጊዜ የሹፈርነት ሙያዋን የሚያደንቁ አንዳንድ ሰዎች «የጀርመኗ የምድር ጥቁር ፓይለት» ስለሚሏት የሰማዩንም ጭምር እንዲሆንላት አልፎ አልፎ ትመኛለች ታልማለች። ገና እድሜዋ ትኩስ በመሆኑ ሁልጊዜ ትሮጣለች። ፍጥነትና በረራ ደስ ይላታል።

አንዳንድ ጊዜ በሰማይ የሚበሩትን አሞሮችና ወፎች እንኳን ወደ ላይ አንጋጣ ስትመለከት «ምነው እነሱን ባደረገኝና እንደነሱ በከነፍኩ» ትልና በስሜት ኃይል ሳታውቀው የቤንዚኑን ፔዳል ትረግጠዋለች።

መኪናዋ ይፈጥናል እንጂ መሬት ለቆ ባለመብረሩ ትበሳጫለች። በዚሁ ፍጥነቷ ሁለት ጊዜ በትራፊክ ራዳር ፎቶ ተነስታ ተቀጥታለች። የጀርመን ጥቁር ፓይለት የሚለው መጠሪያዋ ይገፋፋት ይሁን ወይም ሌላ የፍጥነት አመሏ አሁንም ያው ነው። ቅጣት የማይገታው በእርግጥም የምድር ላይ በራሪ ጥቁር ፓይለት ነች።

ሮዚ ከሀሳቧ በመጠኑ ነቅታ የመኪናዋን ሞተር ለኮሰችው። ሙዚቃዋን ከፍታ የሩጫ ስሜቷን በለሰለሰ የእንግሊዘኛ የፍቅር ሙዚቃ ስልት ልትገታው ሞከረች። መኪናዋ ግን ቸኩላ ከአይሮፕላን አየር ጣቢያ ተፈተለከች። ሮዚ በአካባቢው የሚገኘውን የሉፍታንዛ የፓይለቶች ማሰልጠኛ ሕንፃ ተመልክታ ምኞቷ ዋዠቀ። መኪናዋ መፍጠኗን ሳታውቀው እከተማው እንብርት አካባቢ ደረሰች።

የሆነ ድምፅ ከሙዚቃው በልጦ ሮዚ መኪና ውስጥ ተሰማ። አዎ ከሴንተራል የሚተላለፍ የታክሲ ሹፌሮች መጠቀሚያ እንደራዲዎ ያለ መሣሪያ ነበር። ፉንክ (Funk) ይሉታል። እያንዳንዱ ታክሲ ይህ መሣሪያ አለው። ከሴንተራል ቢሮ የሚተላለፈውን የታክሲ አገልግሎት በር (Tour) መቀበል ወይም የራስን ሀሳብ ለሴንተራል ቢሮ መግለጽ በዚሁ ፉንክ በተባለው መሣሪያ መግለጽ ይቻላል።

ሮዚ መኪናዋን እየነዳች በሀሳብ ተውጣ ስትጋልብ፣ ድንገት ከሴንትራል ቢሮ ጥሪ ደረሳት። ከሙዚቃዋ በልጦ ከነበረችበት የምኞት ሕልም ያባነናት ይሄው ድምፅ ነበር። ከማዶ ተናጋሪው ፉንከሩ የጠራው ስሟን ሳይሆን የድርጅቱን ስምና የመኪናዋን ቁጥር በማከታተል «ሮላንድ 20» ብሎ ጠራት። ጥሪው ከሰማይ በረራ ሕልሟ መነጠቃት። የተጠራው ቁጥር የምትነዳው አዲስ ሊሞዚን ታክሲ ነበር። ጥሪው ከሙዚቃው ባሕር አውጥቶ ከምታስበው የሕልም ሰመመን ስለመነጨታት ፉንከሩን ጠላችው። እሷም በተመናጨቀ ድምፅ ተቆጥታ ድምጿን አሰማች። አመሏን የሚያውቀው የሴንተራሉ ቢሮ ሠራተኛ ፉንከር ትዕግሥት አድርጐ በለሰለሰ ድምፅ የታክሲ ደንበኛዋ ከምታውቀው ቦታ ለታክሲ አገልግሎት ሥራ እንደሚፈልጋት በለዘብታ ነገራት። ያስጠራት ሰው ማን እንደ ሆነ በሀሳቧ ገምታ በሰመመን ደስ አላት። ፉንከሩን በቁጣ ቃል በመናገሯ ጸጸታት።

አዎ ሮዚን ያስጠራት የሮላንድ ታክሲ ድርጅት የረዥም ጊዜ ደንበኛ ባለትዳር የናጠጠ ሀብታም ነጋዴ ነው። ታዲያ ከሥራው በአዲሱ ፓርሼ መጥቶ እሰፈሩ አካባቢ የሆነ ቡና ቤት ገብቶ ብቅል ብጤ ቀማምሷል። ይህ ሰው ሞቅ ሲለውና ሲሰክር የግል መኪናውን በሚያውቀው ሹፌር አስነድቶ እሱ ተዝናንቶ ሌላ ታክሲ አስከትሎ ወደቤቱ መሄድ አልፎ አልፎ የሚያደርገው ልማድ ነው። ጀርመኖች ይሄን አሠራር የመላእክት ጉዞ (Engelfahrt) ይሉታል በአጠቃላይ ትርጉሙ «ከጠጡ መኪና አይንዱ ነው» ሁኔታው ጤናማ ተግባር ነው።

ይህ የታክሲ ደንበኛ ቱጃር መኖሪያ ቤቱ ዘወትር ከሚጠግበት ቡና ቤት እንብዛም አይርቅም። ግን ክብሩን ለመጠበቅ ይሁን ወይም ሞቅ ሲለው ባለው ለጋሥነት ጉራ በተለይ ሲሰክር ለሮዚ የሚሰጣት ጉርሻ ከተጓዘበት የታክሲ መደበኛ ሂሳብ አሥር እጥፍ ይሆናል።

ሮዚ ባለጋርሼ ከበርቴውን እቤቱ አድርሳ የታክሲ ሂሳቧን የደለበ ጉርሻዋን ተቀብላ ደስ አላት። በእሁድ ምድር ባላሰበችው ጸጋ ተዝናናች። በሌላ ታክሲ ለተከተላት ሹፌር የሚከፈለውን ሂሳብ ከትንሽ ጉርሻ ጋር ሰጥታ መኪናዋን ሮላንድ 20 ታክሲ ያቆመችበት ቦታ ስትደርስ ከዚህኛው ታክሲ ወጥታ እመኪናዋ ውስጥ ገባች። እዛው እንዳለች ሲጃራዋን ለኩሳ ጭሱን በደስታ ትንፋሽ ወደ ላይ ቡን! ቡን! አደረገችው። «ዛሬ ገዳም ቀን ነው» ብላ ምሽቱን አሞጋገሰች።

ብሬመን ውስጥ የታክሲ ገበያ በተለይ እሁድ እሁድ የመነመነ ነው። በተለይ በጋ ሆኖ ሙሉ ጨረቃ ከወጣ ሕዝቡ እንብዛም አይዝናናም። በአጉል አምልኮ የፍጥኝ ታሥሯል። ታዲያ ሮዚ ይህ አጉል አምልኮ ሀገሯ ብቻ ሳይሆን እዚህም በመሆኑ ሠለጠንን የሚሉትን ሕዝቦች ሁሌ ትታዘባለች።

ጥቁር ድመት መንገድ ስታቋርጥ የኬከብ ቆጠራ ጋዜጣ ንባብ የ13 ቁጥር ጥላቻ የሙሉ ጨረቃ መጥፎ እምነትና አንዳንድ ጊዜ በሠርግ ድግሥ ለጥሩ እድል ሥምረት የበሉበትን ሠሃን መሰባበርና የሌላም ልዩ ልዩ አምልኮት ጨርሶ አትወድም። እምነቷ በአንድ እግዚአብሔር የፀና ነው። ቅዱስ ገብርኤልን ከልቧ ትወደዋለች። የሱን ገድልና የሰኔ ጐሎጐታን የጸሎት ትንሽ መጽሐፍት ዘወትር ይዛ ታነባለች።

ሮዚ ሥራዋ አደገኛ ቢሆንም በእምነቷ ጽናት ሁሉንም ትደፍራለች። የናቷ ጸሎትና ምርቃት ከክፉ ነገር እንደሚጠብቃት ታውቃለች። ተፈጥሮዋ ይሁን ብርታቷ እምነቷ ይሁን ንቃቷ የሴትነት ድክመቷን ሸፍኖ የወንድነት ብርታት አጐናጽፏታል።

ሮዚ ለቤተሰቦቿ በተለይ ለወላጅ እናቷ ያላት ፍቅር ከፍተኛ ነው። ይህንና ይህን በመሳሰለ ስሜት ሌት ተቀን ሠርታ ያጠራቀመችውን ገንዘብ ያለገደብ በየጊዜው ሲያመቻት ትልካለች። «እባክሽን የሚቸግረን ነገር የለም አትላኪ» ቢሏትም አትሰማም። የኢትዮጵያ ችግር የይሉንታ ባሕልና ያለማስቸገር ግድርድርነት በደንብ ጠንቅቃ ታውቃለች። አልፎ አልፎ ናፍቆቷ አይሎ ሆዷን ባር ባር ሲላት ስልክ ደውላ ሁሉንም ቤተሰብ በደንብ ታነጋግራለች። በተለይ እናቷን እንደ ሕፃን በማቆላመጥ «ማምዬ እንደምን አለሽልኝ በጣም ናፍቀሽኛል እወድሻለሁ ከልቤ አፈቅርሻለሁ» ብላ ለአባቷ ሰላምታ ትነግራለች። ያሳደጓት የዘመድ ሞግዚት አሮጊት እቤትም ስላሉ «እሙዬን ሳሚልኝ ጋሼ በቀለንም አትርሳቸው። ያኔ በደርግ ጊዜ የጀመሩት የማታ ትምህርት እምን ደረሰ? አይ እሳቸው» ብላ ሁሉን ጠይቃ ትተከዛለች። ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ እጆቿ ሲንቀጠቀጥ መልሳ ስልኩን ትዘጋዋለች።

ይህ ሁኔታ ሮዚን ድንገት ትዝ ብሏት ተከዘች። የለኮሰችውን ሲጃራ ብዙም ሳትምግ በግማሹ ተርኩሳ አጠፋችው። ሙዚቃም ከፍቶ ማዳመጥ አስጠላት። የመኪናዋን ሞተር አስነስታ የፉንከሩን ድምፅ ብቻ እያዳመጠች ወደ ግራ ታጥፋ ቢሰማርክ ከሚባለው ሰፊ ጐዳና ጥልቅ አለች።

አንዳዷ እንደ ወትሮ አልፈጠነም። የፍጥነት መቆጣጠሪያ የትራፊክ ራዳር ካሜራዎች የት የት እንዳሉ በክፈል ታውቃለች። በዚሁ ጐዳና ትንሽ ተጉዛ አለፈች። እንደ አጋጣሚ የእሁድ ምሽት አቶቢስ የረፈደባቸው ሁለት ተሳፋሪዎች እጃቸውን ወደላይ ወድረው አቆሟት። የሚሄዱበት ቦታ ባይርቅም እንግዶቹን በደስታ አሳፍራ ዋናው ባቡር ጣቢያ አደረሰቻቸው። ከአካባቢው ብዙም ሳትርቅ የሆነ ቦታ ታክሲዋን አቁማ ሌላ ተሳፋሪዎችን የምታድንበት ወይም ከፉንከ ቶሎ ቶሎ ጥሪ የሚሰጥበትን ሥፍራዎች በሀሳቧ አሰላሰለች።

የሮዚ ዓይኖች አካባቢውን ከወዲህ ወዲያ አተኩረው አማተሩ። ጀንበሯ ብትጠልቅም ምሽቱ ገና የወገገ ነበር። ብዙ የታክሲ መኪናዎች በአካባቢው ተደርድረዋል። ጠጉራቸው የሸበተ፣ ዓይኖቻቸው የደከሙ፣ ምናልባት ጡረታ የወጡ የፉንከ ጩኸት የሰለቹ ሽማግሌዎችና አንዳንድ ወጣት ጀማሪ የታክሲ ሹፌሮች መኪናቸውን ይዘው ቆመዋል።

እነዚህ ሰዎች እንደ ቁራ ውሻ ተቅለብልበው ወይም እንደ ጨልፊት ከንፈው የቾኮለ ታክሲ ተሳፋሪ እንግዳ አሳደውና ተከታትለው አሰባስበውና ሞነው የእለት ጉርሳቸውን የኑሮ ግዴታቸውንና ገቢያቸውን በቅጡና በትጋት የማይመለከቱትን ለውዛዛ ታክሲ ነጂዎችን ታዘበች።

አንዳንዶቹ መኪናቸውን ተራ አሲዘው ብዙ ሰዓቶች በመጠበቅ የትዕግሥት ሰሜታቸውን ለማባበል መኪናቸውን በእጃቸውና በትንሹና ምላሳቸው ሳይቀር ተጠቅመው ይወለውላሉ። ሌሎቹ መኪናቸውን ተደግፈው ወደ ሰማይ አንጋጠው ሙሉ ጨረቃን በማየት የሰማይ መና ድፎ ዳቦ ታወርድላቸው ይመስል እያዛጉ በአጉል አምልኮ «የእለት እድሌን እሱ ካለ አይነሳኝም።» በማለት ያላዝናሉ።

የደከሙት ደግሞ ታክሲያቸው ውስጥ ተኮፍሰው ጋዜጣ ይሁን ሌላ መጽሔት ወይም ፓርኖ መነጽራቸውን ደቅነው አተኩረው ወደ ታች ይመለከታሉ። የደከሙትም መሪያቸው ላይ ተደፍተው እያንቀላፉ ተራቸውን ይጠብቃሉ።

የቀሩት ደግሞ ደጅ ቆመው ስለ እለቱ አየር ሁኔታ ይሁን እስፖርት፣ ስለጥጆች ብዛት ይሁን ወይም ስለእለት ገቢያቸው ማነስ ብቻ ጉዳዩ ባልታወቀ ጉዳይ አየተከራከሩ እጆቻቸውን ከወዲያ ወዲህ ያወናጭፋሉ። «እሰጥ አገባ» እንደሚሉ ጠበቃዎች ይጨቃጨቃሉ።

ሮዚ እነዚህን ሰዎች በዓይኖቿ ገርምማ እንደ ንፋስ ፈጣን ከሆነ ባቡር አካባቢ ሆነው እንደ ኤሊ የሚያዘግም ቀርፋፋ እለታዊ ተግባራቸውን ታዝባ ተጠየፈች። ይህ የስንፍና በሽታ ሳይጋባባት ፈጥና ከቦታው ሹልክ ብላ አመለጠች።

ብዙም ሳትርቅ ሮዚ ከፉንክ የሆነ ሌላ የታክሲ አገልግሎት በር (Tour) ደረሳት። ከተባለው ሥፍራ ሄዳ ሁለት ባለትዳር ባልና ሚስቶች አሳ ፈረች። ጉዞው ወደ ዲልመን ሆርስት በመሆኑ እርቀት ስላለው ደስ ብሏት ሞተሯን አስነሳች።

በጉዞው መሐከል ሰላምታ ተለዋውጠው ውይይት ተጀመረ። ወንድ የው ተሳፋሪ

«ማን ትባያለሽ» ብሎ ስሟን ጠየቀ።

«ሮዚ» ብላ እየሳቀች መለሰች።

የጠያቂው ሚስት ከዚች ጥቁር ሹፌር ጋር ንግግር መክፈቱን እንብዛም አላስደሰታትም።

«ከየት ሀገር ነሽ?»

«ከኢትዮጵያ።»

«ምሥራቅ አፍሪካ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ» ብሎ በአንክሮ በማድነቅ ስማቸውን ጠራ።

ብዙ ጀርመኖች ኢትዮጵያን የሚያውቁ የንጉሡን ስም በመጥራት ስለ ሆነ አልደነቃትም። እንዳውም በማወቁ ደስ እንዲለው ብላ አሞገ ሠችው። ተሳፋሪው ቀጠል አድርጐ «የኢትዮጵያና የኤርትራ ልዩነት ምንድነው?» ብሎ ጠየቃት።

ሮዚ በዚህ ጉዳይ የበሰለ በፖለቲካ የተደገፈ መልስ አልሰጠችም በደፈና ግን ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንደ ነበረች አስረድታ ከረዥም የእርስ በእርስ ውጊያ በኋላ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን ብቻ በደፈናው ተናገረች።

ተሳፋሪው የጀርመኖችን መከፋፈልና መልሶም አንድ የመሆን ታሪክ የሆንግ ኮንግና የቻይናን መልሶ መገጣጠም በአጭሩ አስረድቶ «ኤርትራም አንድ ቀን መልሳ ከኢትዮጵያ ጋር ትደባለቅ ይሆናል» ብሎ የሩቅ ተስፋ በመስጠት ጥያቄውን አቆመ። ሮዚ እራሳቸውን «ከቻሉ የነሱ መገንጠል አይጐዳም» ብላ የመኪና ማርሾቿን እየቀያየረች ወደ ፊት በረረች።

የተሳፋሪው ሚስት ለስለስ ባለ አንደበት በሚቀጥለው ወር ወደ ኬንያ ለዓመት እረፍት እንደሚሄዱ ነግራ ስለሰሞኑ የዩኒቨርስቲ ዴሞኒስት ሬሽን አስጊነት ጠየቀቻት። ሮዚ ዘወትር የሲዲና የካሴት ሙዚቃ እየለዋ ወጠች ከማዳመጥ በስተቀር ስለ ኬንያ ሆነ ስለ ሌላ የፖለቲካ ውዝግብ የምታውቀው አልነበረም። አለማወቋን ለመሸፈን «የሚያሰጋ ከሆነ ለምን ወደ ኢትዮጵያ አትሄዱም? ብዙ አስደሳች ነገሮች አለላችሁ። ኬንያ ውስጥ የሚታዩት የዱር አራዊት ጥንት የኢትዮጵያ ነበሩ የኬንያ መንግሥት በሂሊኮፕተር ጨው እየነሰነሰች አስደንብራ ወስዳብን ነው። አሁንም የቀሩ ብዙ አራዊቶች አሉን የጥንት አብያተ ክርስቲያን መቅደሶች የሕዝቡ ባህልና ታሪክ የአየሯ ሁኔታ አጅግ አስደሳች ነው» ብላ የራሷን ስሜት ማስታወቂያዊ አነጋገር አሰማች። የሀገሯን የውስጥ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ግን ምን ያህል እንደምታውቅ እንጃ።

ሮዚ በዚህ ዓይነት እያጫወተች እንግዶቹን ቤታቸው አድርሳ ወደብሬመን ተመልሳ መጣች። ፉንከሩን በሁለተኛ ካናል ክላውዝን እንዲያቀርብላት ጠየቀችው። ክላውዝ በፉንክ ተፈልጐ አልተገኘም። ምናልባት እራቅ ያለ ቦታ ታክሲውን ይዞ ሄዷል። ክላውዝ ጀርመናዊ የሆነ የሮዚ የልብ ወዳጇና የሥራ ባልደረባዋ ነው።

ሮዚ ክላውዝን የፈለገችውና ያስፈለገችው አብረው እራት ለመብላት ፈልጋ ነበር። ሌላ አንድ ሁለት በሮች (ማለት የታክሲ አገልግሎት ሥራ) ሠርታ ሰዓቷን ተመለከተች። ባይርባትም ክላውዝን ለማየት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ፈልጋ አጣችው። ትንሽ የቅናት ስሜት ብን አለባት። ሲጋራዋን ለኩሳ አጨሰች።

ሮዚ ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ስትዘዋወር ድንገት የሆነ ቀልደኛ ሽማግሌ ከመንገድ አስቁሞ ታክሲዋ ውስጥ ጥልቅ አለ። ትንሽ ሞቅ ስላለው ብቻውን ይሰቃል። እንደሌሎቹ ተሳፋሪ ስለሮዚ ማንነት አልጠየቀም። ልዩ ልዩ የሚያስቁ ቀልዶች እያወራላት እሷም በቀልዱ ከልብ እየሳቀች ቤቱ አደረሰችው።

ሮዚ ፣ ቅድም ብን ያለባት ቅናት በሽማግሌው ቀልድ እየተረሱ ፊዱ። ጥርሷ ይሳቅ እንጂ ልቧ ግን አልተደሰተም። የእለት ገበያዋ ጥሩ

ቢሆንም የክላውዝ አጠገቧ አለመኖር ይሁን ወይም ሌላ ስሜቷን ቀፈፋት። መኪናዋን ኢድል ቫይስ (Edlweiss) ከተባለ የታክሲዎች ማቆሚያ ቦታ ተራዋን ጠብቃ አቆመችው። ከፊት ለፊቷ በርካታ ታክሲዎች ቢኖሩም ስለደከማት ትንሽ ለማረፍ አልከፋትም። እግሮቿን ዝርግትግት ወገቧን ሽቅብ ለምጠጥ በማድረግ ዓይኖቿን ጨፍና ወደ ላይ ተንጠራርታ ወደኋላዋ በጀርባዋ ለጠጥ ብላ ተዝናናች። የሆነ የሀገር ቤት የሙዚቃ ካሴት አድርጋ ስታዳምጥ ድንገት ሀሳቧ ከዘፈኑ ቅኝት ጋር ተዋሕዶ ሀገር ቤት ገባ። የልጅነት ትዝታዋ የሀገር ፍቅር ስሜቷ የወደፊት ምኞቷ ተደራርበው መጥተው ወተወቷት። እንቅልፍ ብጤ በዓይኖቿ እየዞረ ሸለብ አደረጋት።

ሮዚ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ አራት ኪሎ ተወልዳ እዛው ያደገች የ28 ዓመት ኮረዳ ነች። ለእናቷ ለወ/ሮ ቦጋለች ለአባቷ ለፊታውራሪ አሥራት የመጨረሻ ልጅ ናት። የተማረችው ናዝሬት ት/ቤት ነበር። ከቤቷ ወደ ት/ቤት ከት/ቤት ወደ ቤቷ ያለውን መንገድ ጠንቅቃ ታውቃለች። ከእዛ አልፎ አቧራ፣ ግንፍሌ ቀበና ካሳንቺስ ወዘተ. የሚሉትን መንደሮች ሲባል እንጂ ከየት ተነስቶ መንገድ አቆራርጦ እንደሚደርስ ጨርሶ አታውቅም።

አንድ ቀን የሆነ ገጠሬ መንገደኛ ይቅርታ ጠይቆ የጐጃም በረንዳን ቢጠይቃት ግራ ተጋብታ «ይቅርታ እኔ አላውቅም ማዶ የቆሙትን ታክሲ ነጂዎች ጠይቃቸው» ብላ በማመናጨቅ የመለሰችለትን መልስ ትዝ ብሏት አዘነች። «እሩቅ ሀሳቢ ቅርብ አዳሪ» እንደሚባለው ዛሬ ሀገሯን ጥላ ጀርመን ገብታ የብሬመን ጥልፍልፍ ጐዳና አውቃና የመንገዶችን ስምና ሌላም መንደሮች አጥንታ ድሮ የናቀችውን የታክሲ ሹፌርነት ሙያ አሁን በመያዟ ገረማት። የእድልንና የሕይወትን ጠመዝማዛ መንገድ በማተኮር በራሷ ፍልስፍና በሀሳብ ዋዣቀች። ሹፌርነቷ ሁል ጊዜ ሕልም ይመስላታል። ሁሉን ለመሆን ተመኝታ የናቀችውን ሙያ ሳታስበው በመያዟ እድሏን እረገመች። በየእለቱ የምታገኘውን ገንዘብ ብዛት እያሰበች ግን ደስ ብሏት እራሷን በራሷ አጽናናች። አልፎ አልፎ ምኞቷም መንጥቆ እሩቅ ስለሚሄድ ያለችበትን ቦታ ትረሳለች። ፓይለት፣ ጋዜጠኛ፣ ጠበቃና ዳኛ የመሆን ምኞቷ ግን ለጊዜው ይመንምኑ እንጂ የትምህርት ከፍተኛ ፍላጐቷ አሁንም ጨርሶ አልጠፋም።

እንዳጋጣሚ ሐጐስ የሚባለው ኤርትራዊ ስደተኛ ከሩቅ አይቷት እየተንገዳገደ መጥቶ መኪናዋ ውስጥ ሳይገባ በግራ በኩል ደጅ ቆሞ ሰላም አላት። ሮዚ የመኪናዋን መስኮት ከፍታ አየችው።

«ከሜለሃ ሮዚ ፅቡቅ አልሀ» ብሎ በትግርኛ በጐለደፈ ድምፅ ሰላምታ ሰጣት ሮዚ ሐጐስ ሲሰክር የሚያደርገውን መጥፎ ጠባይ ስለምታውቅ ለሰላምታው ሰላምታ አልመለሰችለትም። ሐጐስ በመንተባተብ የትግርኛ ሰላምታውን ደገመላት።

«አባክህን አትዘባነን በአማርኛ ትናገር እንደሆን ተናገር እኔ የናንተ ቋንቋ አይገባኝም» አለችው መንጨቅጨቅ ባለ ስሜት።

«በቋንቋዬ እንደሀሪ ዘይ ተዛረብኪ በቋንቋኺ አይዛረብን።» ብሎ ቆጣ ቆጣ አላት። ሮዚ ኤርትራዊም ሆነ ሌላ አበሻ የሰከረም ሆነ ጤነኛ በሥራዋ ላይ መጥተው ሲለፈልፉባት ጨርሶ አትወድም። በሀገር ፍቅር ስሜት ይሉኝታ ስለሚይዛት ግን የሚሉትን ሁሉ በትዕግሥት ታዳምጣቸዋለች። የሐጐስ የተደጋገመ ሰላምታ ለነገር መሆኑ ገብቷት፣

«ምንድነው ከእኔ የምትፈልገው?» ብላ ጮኽችበት።

«ታክሲ ነጂ አይደለሽ እቤቴ እንድታደርሺኝ ነው። ጠጥቼ ደክሞኛል።» ብሎ በትግርኛ ቅላጼ በአማርኛ አናገራት። ድልህ የመሰሉ ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ አፍጥጦ።

«ሥራችን በተራ ስለሆነ መጀመሪያ እረድፍ የቆመውን ታክሲ ጠይቀው በናትህ ከሥራ ጓደኞቼ አታጋጪኝ።»

«በፈለግሁት ታክሲ ለመሄድ መብቴ ነው።»

«የራስህን መብት ስትጠብቅ የሌሎችንም መብት እያከበርክ መሆን አለበት ደደብ!» ብላ ጮኽችበት።

ሐጐስ በግራ በኩል ቆሞ ወደ መኪናዋ ተጠግቶ «ባፉንኩሎ ገንዘብ እይደለም የምትፈልጊው ይሄውልሽ!» ብሎ ከኪሱ የታመቀ ብሮች በእጁ ጨምቆቆ አሳያት። «እኔ ያንተን ገንዘብ ጨርሶ አልፈልግም እባክህ በፈጠረህ አምላክ ሥራዬን ልሥራበት ተወኝ። አትረብሸኝ።»

«አበሻ አበሻ ስንት ዓመት በኛ ላይ ያደረጋችሁት ጨርሶ አይ ረሳም...እ» ብሎ ሊቀጥል ሲል ሮዚ ንግግሩን አቋርጣ፣

«አሁንም ገና እንረግጣችኋለን። ነፃነት አላችሁ ሰጠናችሁ ምን ድነው ከኢትዮጵያ ጋር የሚያሟዝዛችሁ። ምንድነው የምትፈልጉት?» ብላ ጮኸችበት።

«መሬት ሰፊ ግዛት! ይገባሻል? ለኛ ዛላንበሳ ሽራሮና ባድማ የሚበቃን አይምሰልሽ ዓላማችን ትልቅ እቅዳችን ሰፊ ነው። ግን ላንቺ ለመሐል ሀገር አበሻ መንገሩ አያስፈልግም በቅርቡ ታይዋለሽ»

«ምንድነው የማየው? የያዛችሁትንም መሬት ሳትወዱ በግድ ትለቃላችሁ።»

«አንዴ የዋጥነውን መልሰን አንተፋውም ገባሽ?»

«ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ እየረገጠ ነው የሚያስተፋችሁ ድንግል መሬታችን የማንም ከዳተኛ መፈንጫ አትሆንም ገባህ?»

«ማነው ከዳተኛ ሎቅማጽ»

«እዚህ ጀርመን እኔ ላይ ሰክረህ ከምትለፋደድ ወንድ ከሆንክ እዛ በርሃ ገብተህ ተዋጋ ሰካራም ደደብ!»

«ማነው ደደብ? ሰካራም አንቺ ሃድኒ! ሎቅማጽ ሸርሙጣ!»

«አንተ ለሃጫም አጋሚ የአሰብ ኩሊ ጀርመን መጥተህ አለፈልህ ወንድ ከሆንክ ለምን ሄደህ ወንዶቹን አትናገርም ቅማላም አተላ» ብላ በመረረ ሁኔታ ግንፍል ብሏት ተናገረችው። ሙልሞ አርጋ ሰደበችው።

ሐጐስ «ነሐልዲነክ ሸርሙጣ» ብሎ በቃሪያ ጥፊ በተከፈተው የመኪናው መስኮት በኩል አሾልኮ ጀሮ ግንዷን ጨምሮ አጠዛት። ሮዚ ጭው አለባት ደንግጣ ሳይደግማት የመኪናዋን መስኮትና በር ጥርቅ ምቅም አርጋ ዘጋጋችው።

ሐጐስ በንዴት መኪናውን በርግጫ በሩን በጡጫ ብሎ የተዘጋውን መስታወት በቴስታ ሲመታው ግንባሩን የመኪናው በር የላይኛው ጠርዝ ተረከከው። በአልኮል የሞቀ ደሙ ከግንባሩ ቡልቅ እያለ ምድሩን አለበሰው።

ሮዚ ከዛ ቦታ ለመሄድ የመኪናዋን ሞተር ለማስነሳት ሞክራ አቃታት። እጆቿ ተንቀጠቀጡ። ትንፋሿ ተቆራረጠ። ጀሮዋ ጭው የሚል ድምፅ አስተጋባ። ጉንጯ ቀልቶ የደም ሥሮቿ ተግተረተሩ። ሰውነቷ ሞቅ አለባት። አፏ የሆነ ያልሆነውን እየቀበጣጠረ ፎከረ። ዓይናቿ ሐጐስ የደረሰበትን ፍንክት በቅጡም አላዩ። መኪናዋን በግድ አስነስታ እንደ ጥይት ተፈትልካ ከቦታው እራቀች።

ሐጐስ የሮዚ ስድብና ቁጣ በሰካሩ ላይ ተጨምሮ ሰውነቱን እንደ ቋያ እሳት ለበለበው። የግንባሩ ፍንክት ደም ይትፋ እንጂ ሕመሙ ለጊዜው አልተሰማውም። ሁለት እጆቹን ግንባሩ ላይ ደፍቶ በዛቻ እየፎከረ የሮዚን የመኪና ጭስ ተከናንቦ የጭዳ ደም የለበሰ የጣአት ሐውልት መስሎ እዛው ቆሞ ቀረ።

• • •

የብሬመን የበጋ ምሽት ደባብዞ እየጨለመ እኩለ ለሊት ተቃርቧል። አየሩም የሙቀት ብልኮውን እያወላለቀ በለዘብታ እየነፈሰ ቅዝቃዜን ተክቶአል። በለሊት የሚጓዘውን መንገደኛ ያናፍሳል። ሰካራሙን እየፈወሰ ለጤነኛው ቆፈኑን እየላከከ ተፈጥሮን እንደ ሕፃን ልጅ «እሹሩሩ» እያለ ከታች ወደ ላይ ከላይ ወደታች የሕይወት ዥዋዥዌ መጫወቱን ቀጥሏል።

በየመንገዱ በመደዳ የተተከሉ ትልልቅ መብራቶች የኤሌትሪክ የብር ሃን ጨረራቸውን ለኩሰውና በርተው ጨለማውን ገፍትረው አሸሽ ውታል። በየንግዱ ቤት በራፍ ላይ የተለጠፉ ማስታወቂያዎች በልዩ ልዩ ቀለማት ተኩለው ብልጭ ድርግም እያሉ በማንፀባረቅ የበጋውን ምሽት በፋናቸው አቆንጅተውታል።

በጥቁሩ ሰፊ ጨለማ ሰማይ ላይ ድፎ ዳቦ የመሰለ ቅርጽ ያላት ሙሉ ጨረቃ ትታያለች። ብርሃኗ ደምቆ ከተማውን በመጠኑ አወግሯታል።

በመስቀለኛ የመኪና መተላለፊያ ሰፊ ጐዳና ላይ ያሉትም የትራፊክ መብራቶች ቆመዋል። የቀለም ፋናቸውን ብልጭ ድርግም እያደረጉ ይጠቃቀሳሉ። ሹፌሮች ቸኩለው እርስ በእርሳቸው እንዳይጣሉ በሥርዓት ያስተናግዳሉ።

ነጭ አልማዝ (አድልቫይስ) የሚባለው የታክሲዎች ማቆሚያ ስፍራ ነው። በምሽቱ ጥቂት የታክሲ ሹፌሮች መኪናቸውን በተራ አሰልፈው የፋንክ ጥሪ እያዳመጡና ሌላም ተሳፋሪ እየጠበቁ ተደርድረዋል። ይህ ቦታ ሐጐስ ከሮዚ ጋር ተጣልቶ በገዛ ጥፋቱ ተፈንክቶ ደሙን የረጨበት ነው። አሁን ሰላም የሰፈነበት መስሏል።

አንድ አርበ ሰፊ ኩንቢ ታክሲ መኪና እሳት ጐርሶ እሳት ለብሶ ከሩቅ እየበረረ መንገዱን አቆራርጦ ከዚሁ ስፍራ ደረሰ። የሞተሩ ጩኸት የፍሬኑ ስጢታ ተደባልቆ አካባቢውን አስተጋባው። የሁሉም የታክሲ ሹፌሬች ዓይን በዚሁ መኪና ላይ አፈጠጠ።

የመጣው ክላውዝ የሚባል ጀርመናዊ የሮዚ የቅርብ ጓደኛ ወዳጅ ነው። የጠቡን ሁኔታ ሰምቶ ከነበረበት እሩቅ ስፍራ መምጣቱ ነበር። የመኪናውን ሞተር ሳያጠፋ ሰፊ ትከሻውን እረዥም ቁመናውን ገፈታ ትሮ ከመኪናው ወጥቶ ጐልያድ መስሎ ታየ። ትንንሽ ዓይኖቹ ተቅበዝብዘው አካባቢውን እየገላመጡ አፈጠጡ። ሮዚም ሐጐስም ሁለቱም በስፍራው የሉም።

ክላውዝ የሚበላው አጥቶ ከወዲህ ወዲያ እንደሚንገዋለል ዳልጋ አንበሳ ተንቆራጠጠ። ተቅበዘበዘ ደረቱ ተነፍቶ ጡንቾቹ ተውጠረጠሩ እንኳን የሚወዳትን ሮዚን የሚያህል ነገር ነክተውበት ያለምክንያት ጠብ ጭሮ የሚጣላ ሰው ነው።

የክላውዝ ብስጭት የገባቸው የታክሲ ሹፌሮች ነገሩን ለማብረድ ደፍረው አልቀረቡትም። እሱም ተጠግቶ አልጠየቃቸውም። እርስ በርሳቸው ግን በመንሾካሾክ «ምን ለአንዲት ጥቁር ሴት ብሎ ደረቱን ይነፋል አሁን እኮ አንዱ ደፍሮ ቢጠጋው እንደ ታይሰስ ጆሮ ከመንከስ አያልፍም» ብለው አሙት። አልሰማቸውም።

ክላውዝ የሰውነት ማዳበሪያ ስፖርት ስለሚሠራ ካለው ረዥም ቁመና ጋር ትልቅ ያስመስለው እንጂ ገና ወጣት ነው። በመንትያ የተወለደ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው። ታክሲ የሚነዳው በሳምንት ምስት ቀን በትርፍ ጊዜው ብቻ ነው።

ክላውዝ ማንንም ሳያነጋግር ወዲህ ወዲያ ተንጐራዶ በወጣበት ሁኔታ ተመልሶ መኪና ውስጥ ገባ። ሞተሩን አጥፍቶ ሲጋራውን ለኩሶ ቶሎ ቶሎ በመሳብ ንዴቱን በመጠኑ የገታው መሰለው። ሀሳቡ ግን ሮዚ አካል ላይ ሄዶ ተጠመጠመ።

«መታጠቢያ ክፈል ሆና» ክላውዝዙ ፎጣ አቀብለኝ ስትለው ሰውነቷን በፎጣ አደራርቆ እንደ ሕፃን ልጅ ታቅፎ መኝታ ክፍሏ የሚወስዳት፣ አንዳንዴ በሆነ ባልሆነ ነገር ብስጭትጭት ብላ ፊቷ ቅሬታ ያጐመነ ሀዘን የተከናነበ መስሎ ሲታየው አቅፎ የሚያባብላት እሷም ደረቱን ተደግፋ ሀዘኗን የምትወጣው። ስትደሰት ደግሞ አብራ የምትደንሰው ሁኔታዎች በሀሳብ ተመላለሱበት።

ሌላው የሮዚ ተቆርቋሪ የታክሲ ሹፌር ኢትዮጵያዊ ዮሐንስ ይባላል። ብዙ ሰዎች ግን የሚጠሩት ጆኒ-ብለው ነው። የሮዚ የልብ ወዳጅ ንጹህ ጓደኛ የሥራ ባልደረባዋ ነው። ይህን ሥራ የጀመረው ከእሷ ቀደም ብሎ ስለ ነበር ሮዚን በዚህ ሙያ እንድትሠማራ ወይም ትምህርቷን እንድትቀጥል የመከራት ሰው ነው።

እሱም እንደክላውዝ የሮዚንና የሐጐስን ጠብ ሰምቶ እዚሁ ስፍራ ደረሰ። ሁለቱንም አላገኛቸውም። ክላውዝ ጆኒን ስላየው ከመኪናው ወጥቶ ጨበጠው ሁለቱም በደንብ ይግባባሉ። ስለጠቡ የሰሙትን እርስ በእርሳቸው ተጨዋወቱ። ጆኒ የጠቡን ምክንያት ለማወቅ የነበሩትን የታክሲ ሹፌሮች ጠየቀ። አንድ ቀጠን አጠር ያለ ጀርመናዊ ታክሲ ነጂ ከመኪናው ወጥቶ «የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ አላውቅም በራሳቸው በአፍሪካ ቋንቋ ነበር የሚነጋገሩት» አለ። «ቋንቋው ባይገባህ ሁኔታው የጠብ መሆኑን መገመት ያቅትሀል?»

«ምን አፍሪካኖች በሰላሙም በጠቡም ሲያወሩ እንደ አውሬ እየጮሁና እየተጨቃጨቁ እጃቸውን ከወዲያ ወዲህ እያራገቡ ስለሆነ ሁኔታው የፍቅር ይሁን የጠብ ሊገባኝ አልቻለም»

ጆኒ ተናዶ «ጥቁሮች ከሌላው ሰው የተለየ ጠባይ አላቸው? በአንተ አስተያየት አውሬ ናቸው ማለት ነው» ብሎ የኩቱን ኮሌታ አንቆ ወደ

ጓላ መኪናው ላይ ገፈተረው። ሹፈሩ በዛቻ ምንም ሳይናገር ዘሎ መኪና ውስጥ ገባ። ሌሎች ታክሲ ነጅዎች ከወዲህ ወዲያ አጉረመረሙ። ክላውዝ በቁጣ ቃል «አፋችሁን ዝጉ!» ብሎ ጮኸባቸው። ሁሉም ዝም ጭጭ አሉ። ሌላ ደም የጠማው የታክሲ ቦታ የክላውዝን ጩኸት ወስዶ አስተጋባ። ክላውዝና ጆኒ መኪናቸውን አስነስተው በተለያየ አቅጣጫ ሮዚን ፍለጋ የሽምጥ ጋለቡ።

የሹፈሩ ስድብ ጆኒ በነበረበት ንዴት ላይ ስለጨመረ ቁጭቱን በመኪናው የቤንዚን መስጫ ፔዳል ላይ ተወጣው።

ወዲያ ወዲህ እየተቅበዘበዘ አብዛኛውን ጊዜ ሮዚ ታክሲዋን የምታቆምበት ወይም ሲርባት ምግብ የምትበላበትን ቦታዎች ተመለካከተ። እቤቷም ስልክ ደውሎ አጣት። ጆኒ ሮዚን በንጹህ ወዳጅነት የሚወዳት እንደ ታናሽ እህቱ አይቶ አንዳንዴም እንደ መጀመሪያ ልጁ ገምቶ ከልብ ያፈቅራታል። በዚህ መጥፎ አጋጣሚ ሳያገኛት በመቅረቱ አዘነ። ይህን ሙያ አደፋፍሮ ሥራ ያስጀመራት እሱ በመሆኑ። ለሚደርስባት ጥቅም ሳይሆን ጉዳቱን እያሰበ ዘወትር ይጨነቃል። ሮዚ ግን «የራሴ ጥረትና ትጋት ነው» እያለች በራሷ ትኩራራለች። በሆዷ ግን የእሱ አርአያነት መሆኑን አትክድም። በሥራውም ስትጠቀም ትረሳዋለች ስትጐዳ ግን አሱነቱን አስታውሳ ታማርራለች። ጆኒን ሲአል ይክተተው ወደ መከራ ከተተኝ ብላ የምትረግምበትም ጊዜ አለ።

ጆኒ የሮዚን ጠባይ እንደ ልጁ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በወቀሳና በአድራጐቷ እንብዛም አይከፋም። አሁንም ቢሆን ይሄን ሥራ አቁማ ዩኒቨርስቲ ገብታ እንድትማር ከመምከር አልተቆጠበም።

«አንተ ተምረህ የት ደረስክ? ሁለት ዲፕሎም ይዘህ ይሄው እንደኔ ታክሲ ነጂ ነህ። እባክህን ተወኝ ልሥራበት» ብላ ታመነጫጭቀዋለች። በርግጥም ጆኒ በተማረው ትምህርት ሥራ አላገኝም። ይም በመሆኑ ለመማር እንቅፋት ሊሆን አይችልም። ምናልባትም ከቦታ ቦታ ባለመዘዋወሩ ወይም የራሱ የሆነ የግል ምክንያት ይኖረዋል። ጆኒ በእድሚውም የገፋ በመሆኑ ለችግሩ ሌላ ምክንያትም ነው።

ጆኒ ሊያዩት ሰውነቱ የሞላና የተደላደለ ጥሩ ትከሻና ግርማ ሞገሥ ያለው ነው። የግንባሩ መሸብሸብ የፀጉሩ መሸበት እድሚውን ይመሰክራሉ። ፈዘዝ ብለው ሞኝ የሚያስመስሉት ትንንሽ ዓይኖቹ በወርቃማ ፍሬም መነጽር ቆንጅተዋል። በአለባበሱ እስከዚህም ጥንቁቅ አይደለም አንዳንዴ ሸሚዙ ከሱሪው እያፈተለከ ያስቸግረዋል።

ጆኒ ጠባየ ሸጋ ቂምና ተንኮል የማያውቅ የዋህ ሰው ነው። ለወደደው ይሞታል። የሀገር ፍቅር ከፍተኛ ስሜት አለው። ብዙ ኢትዮጵያኖች በስደትና በልዩ ልዩ ጉዳይ ብሬመን ሲመጡ ቀድሞ የሚያስተናግደው አሱ ነው። በዚህም ቤቱን የጐጃም በረንዳ እያሉ ይጠሩታል። የእርስ በእርስ መረዳጃ ማኅበር ለማቋቋም ሞክሮ ብዙ ጥረት አድርጓል።



ጆኒ ባለትዳር የሦስት ልጆች አባት ቢሆንም ኑሮው የወንደላጤ ነው። ሚስትና ሁለት ልጆቹን ጀርመን ለማስመጣት ሞክሮ አልተሳካለትም።

ጆኒ ሮዚን በየቦታው ፈልጐ አጣት። ምናልባትም በጠቡ ምክንያት በተፈጠረው ግጭት ለህክምና ይሄዳሉ ብሎ ከሚገምትበት የለሊት የድንገተኛ የሕክምና እርዳታ የሚሰጥበትን ክሊኒኮችና ሆስፒታል ጠያይቆ የተገኘ ፍንጭ የለም።

የታክሲ ሥራ አገልግሎት ሥራውን ቀጥሎ ለሊቱ ተገባደደ። ሊነጋጋ አካባቢ ታክሲውን ከሆነ ሆስፒታል አጠገብ ከሚገኘው የታክሲዎች ማቆሚያ ቦታ አሰልፎ የመጀመሪያውን ረድፍ ያዘ። አንዲት ቀኝ እጇ በፋሻ የታሠረ ቆንጅዬ ሴት ከዚሁ ሆስፒታል ወጥታ ወደ ታክሲው ስትጠጋ አይቶ በር ከፍቶ አስገባት። ጥቂት እንደ ተጓዙ ለንግግር መክፈቻ «እሜቴ ምን ነክትዎት ነው አደጋ ነው? ብሎ በአከብሮት በአንቱታ ጠየቃቸው። ሴትየዋ «አዎ አደጋ ነው። ግን አንቺ ብለህ ብትጠራኝ እወዳለሁ» አሉት።

«ምን ዓይነት አደጋ?»

«ከብሊሲ ወድቄ ነው።»

« ምንድነው ብሊሲ?»

«ፈረስ ነው። የፈረሴ መጠሪያ ልዩ ስም ብሊሲ ነው» አላት።

«የፈረስ ባለቤት ከሆንሽማ ባለፀጋ ነሽ ማለት ነው» አላት።

የሀገሩን የፈረስ ዋጋ ከጀርመኑ እያወዳደረ በአንኮሮ አድንቆ በተፈጠረው አደጋ አዝኖ ድምጡን አለስልሶ።

«ባለጸጋ አይደለሁም ግን ፈረሱን የሸጠልኝ አንድ የማውቀው ሰው በቀላል ዋጋ ነው።»

«ቀላል ሲባል ስንት ነው?» አላት የጀርመንን የፈረስ ዋጋ በትክክል ለማወቅ ፈልጉ እየጓጓ።

«በመሠረቱ ፈረሱ ብዙ ዋጋ የሚያወጣ ነበር ግን ጠባዩ መጥፎ ስለሆነ በቀላሉ ለመገራት ባለመቻሉ ነው ሻጩ በቀላሉ የሸጠልኝ።»

ጆኒ ለጠየቀው መልስ ባለማግኘቱ እራሱን አከክ አድርጉ ከሦስተኛ ማርሽ ሁለተኛ ማርሽ አግብቶ መኪናዋን ቀስ በማድረግ ቀይ ከሚበራው የትራፊክ መብራት ገተረው። ውይይቱ ቀጠለ።

«ያልተገራ ፈረስ በመጋለብሽ ነዋ አደጋ የተፈጠረው» ብሎ ፈገግ አለ።

«አይደለም ብሊሲን ከገዛሁ በኋላ ጠባዩ ያማረና የተገራ ሆነ። አንገቱን እያሻሸሁ ፍራፍሬና ዳቦ ስለማጉርሰው ወደደኝ። አኔም እየወደድኩት መጣሁ። ብሰግረው ብጋልበው በእግሬ ሆዱን እየኮረኮርኩ መጭ እያልኩ ባስሮጠው የማይቆጣ ገራም ፈረስ ሆነልኝ...» እንዳለች ከኋላቸው የቆመ መኪና በክላስክ አስደነገጣቸው። አረንጓዴ መብራቱን ጆኒ ዘንግቶት በሴትየዋ ጫዋታ ፈዞ ነበር። ማብራቱን አልፈው ወደቀኝ ታጠፉ።

«ታዲያ ፈረሱ አንዲህ ገራም ከሆነ አደጋው አንዴት ተፈጠረ?»

«ጥፋቱ የኔ ነው። በሆነ ነገር ተበሳጭቼ ንዴቴን ለመወጣት ባለመደው አለንጋ ጀርባው ላይ ሆኜ ገረፍኩት ሽምጥ ጋልቦ ወደላይ ሲዘል ኮርቻው አጋድሎ ከጀርባው ወድቄ እመሬት በቀኝ ጉኔ ተፈጠፈጥኩ። ደግነቱ መሬቱ ሣር ያበቀለ ልል በመሆኑ ከእጂ በስተቀር

ሌላ ሰውነቴ አልተጐዳም።» እያለች ሰባራ እጂን ወደ ፊት ቀና የቀረ ሰውነቷን ከወንበሩ ጋር ዘና አድርጋ የአደጋውን ሁኔታ ለጆኒ አጫወተችው።

ጆኒ የአደጋውን ሁኔታ አዳምጦ ከልብ ባያዝንም «አሀያውን ትቶ ዳውላውን» ብሎ በሀሳቡ ተረተ። ከንፈሩን በሀዘን መጥጦ:-

«ለመሆኑ ለፈረሱ ምን ያህል ወጪ ታወጪለሽ?»

«ለምግብና በረቱን በንጽሕና ለመያዝ የማወጣው ወጪ እንብዛም ብዙ አይደለም። የጐዳኝ ለከብት ሐኪም የምከፍለው ነው። ከገዛሁት ለሦስቴ ምርመራና ክትባት ከሺ ማርክ የሚበልጥ አውጥቻለሁ።»

«ለመሆኑ የት ነው የምትጋልቢው?» አለ ጆኒ።

በከተማው መሐል የፈረስ መጋለቢያ ሰፊ ሜዳ በዓይናቹ እየፈለገ።

«አ! የምጋልበው ከምኖርበት ከከተማው ትንሽ ወጣ ብሎ ከሚገኘው መንደር ነው። በአካባቢያችን ትልቅ ሜዳ አለ...» ብላ መቀመጫዋን ከታክሲ ወንበሩ ጋር አሸት አሸት በማድረግ ተቁነጠነጠ ጠች። የተባለው ቦታ ደርሰው ጆኒ መልካሙን ተመኝቶ ሴትየዋን አውርዶ ወደ ባዝል ሄደ።

ክላውዝ ሮዚን ፈልጉ በማጣቱ ታክሲውን ባዝል አቁሞ በግል መኪናው የመጨረሻ አርሙን የፍለጋ ድካሙን ለመወጣት ወደመኖሪያ ቤቷ ገሠገሠ።

ጆኒ የምሽቱን ሥራ ጨርሶ ሲነጋጋ ታክሲውን አቁሞ የግሉ አሮጌ አልኮና አፔል ውስጥ ገባ እቤቱ አንደ ደረሰ ለሮዚ ስልክ ደውሎ መልስ አጣ። ጉዳዩን ለፖሊስ አመልክቶ ተጠቅሎ ተኛ።



ክፍል ሁለት

እሁድ አልፎ ሰኞ የሰኔን ግማሽ ወር ተንተርሶ ከደማቅ የፀሐይ ጮራ ጋር እየሳቀ ብቅ አለ። የሰው ልብ ግን አብሮት አልሳቀም። የሳምንቱ የመጨረሻ የሁለት ቀን እረፍት አደካክሞታል።

ሮዚ በደንብ ባትተኛም በሰዓቱ ተነሳች። ለእሷ የቀን ቦታ የለውም። እሁድ ሰኞ ማክሰኞ ቅብጥርሴ ምንትሴ የሚሉት የእለት ስም አጠራር ትርጉም የለውም ያለ አንዳች እረፍት ሰባቱን ቀን ትሠራለች። ከአልጋዋ ላይ እያዛጋች ተንጠራርታ በግድ ብድግ አለች።

ያው የብሬመን የበጋ ምሽት የነጋ ነው። ጀንበሯ አሁንም አልጠለቀችም። ሮዚ ጊዜውን ተጠራጥራ ሰዓቷን ተመለከተች። ሥራ ለመግባት በቂ ጊዜ ስላላት በዝግታ ተጣጥባ የበጋ ልብሷን ለበሰች። መስታወት እየተመለከተች ያን ሮዚ ያሰኛትን የከንፈር ቀለም አንስታ ተቀባች። ቁንጅናዋን በመጠኑ ያጐደለውን የዓይኖቿን ሥር መጠቋቆር አይታ ቅር አላት በትላንቱ የሐጐስ ጥፌ ብስጭት ያለቀሰችበት ጦስ ነበር። የሆነ ቅባት መሳይ በስሱ ቀባብታ ጥቁረቱን አድበሰበሰችው። ጓደኛዋ ከላውዝ ሲነጋጋ መጥቶ ባያጽናናት ኖሮ ዓይኖቿ ብቻ ሳይሆኑ ጠቅላላ መልኳ ባልተቋረጠ ንዴት በበለዘ ነበር።

ሮዚ የሚያበሳጭ ትንሽ ነገር ሲያጋጥማት ሥራ አቁማ እቤቷ ገብታ እድሏን እየረገመች ምርር ብላ ማልቀስና ማንባት ልማዷ ነው። በዚህም ሆድ ይብሳታል። ትንሹ ነገር ያናድዳታል። ይህ ጠባይ ጀርመን ከመጣች በኋላ ያገኘችው ልዩ አመል ነው። የስደት ኑሮ ይሁን የሀገር ፍቅር ስሜት የናት ጓዳ እጦት ይሁን ወይም የሥነ ልቦና ችግር ሆዷን ቦርቧራ፣ አመሷን ነጭናጫ፣ አድርጐታል። ሁኔታው እንደሚጐዳት ብታውቅም ይህ አጉል ልማድ የሙጥኝ ብሏታል።

ሮዚ ምክንያቱ ባልታወቀ ጉዳይ ትበሳጫለች። ትንሽ ከነኳት አኩርፋ ብው! ትላለች። በእጇ ያለውን እየወረወረች ያዙኝ ልቀቁኝ ትላለች። ደሟ ሙቅ ነው። ስትናገር ለአፏ ለከት የለውም። የሆነ ያልሆነውን ትቀ በጣጥራለች። ማንም ይሁን ማን ካናደዳት ደፍራ ሙልጭ አርጋ ትሳደባ ለች። እንደ ሌሎቹ የንዴት ስሜቷን ውጣና ገትታ አስመላይ የማስክ ፊት በማሳየት እየሳቀች ጠላቷን በዘዴ መጉዳት አይሆንላትም። በአጠ ቃላይ የዲፕሎማሲ ኑሮ መኖር አታውቅበትም። በፊት በፊት ገና ጀር መን እንደ መጣች በሰው ላይ ቂም መያዝ አትችልም ነበር። ሲውል ሲያድር ግን ቂሟን እንደ መዥገር መያዙን ለምዳበታለች። ሮዚ ለጠላ ችው የጭቃ እሾክ የቡሄ ጅራፍ ናት። እራሷ ነገር ፈልጋ ሲነኳት ዋይ! ብላ ትጮሃለች። እንደ ተልባ ትንጣጣለች። አመሏን የሚያውቁ ሰዎች እንብዛም አይቀርቧትም። እሷም አትቀርባቸውም። በተለይ ከሀገሯ ልጆች ማለት ከኢትዮጵያኖች ከጥቂት በስተቀር ግንኙነቷን አቋርጣለች።

ሮዚ ባለፈው ጊዜ ማለት ገና ጀርመን እንደመጣች የሆነ ቦታ በአሳ ላፊነት (Kellnerin) ስትሠራ የሆነ ሰካራም አበሻ መጠጥ በነፃ ካልሰጠሽኝ ብሎ ቂም በመያዝ በጥቁር ነው የምትሠራው (ያለመንግሥት ፍቃድ) ብሎ ለፖሊስ ጠቁሞባታል። የሆነች ሌላ የሴት ጓደኛዋ በትንሽ ጉዳይ ተኳርፈው የሆነ የማጭበርበር ክስ አቅርባ አስቀጥታታለች። ሌላው ኢትዮጵያዊ አውቆም ይሁን ሳያውቅ የፖለቲካ የጥገኝነት ታሪኳን ብልሽ ልሽ አድርጐ በመጻፍ የስደተኛ ተቀባይነት እንዳይኖራት አድርጓል። ሌላው ደግሞ ባለትዳር ከአንቱታ አልፎ ዶክተር የሚባል ሚስቱ በሌለ ችበት ሮዚን በእህትነት ጋብዞ ሊደፍራት ሲሞክር ፊቱን በጥፍሯ ቧጥጣ ያደማችው ሁሉ ተደማምሮ ሁሌ ትዝ ይላታል።

«ተውኝ ስላቸው የማይተው መንቻካዎች። አበሻ ሲባል ለሌላው የማይተኛ ምቀኛ የሰው እድል ቀማኛ» እያለች በጥላቻ በሆዷ ትራገ ማለች። ያደረጉባትን ተንኮልና ክፋት በሀሳቧ እየመጣ ያበሳጫታል።

እሷም አበሻ ሆና በመፈጠሯ እድሏን ታማርራለች። በዚህም ይሁን በሌላ ሮዚ ሰሞኑን የአማርኛ ሙዚቃ ማዳመጥና የአማርኛ መጽሐፍ ማንበብ ጨርሶ ትታለች። አንዳንዴ እራሷን በራሷ እየተመለከተች ለሌሎች ያላትን የልብ ቅንነት መውደድና ፍቅር በሕሊናዋ በፅሞና ማንነቷንና እውነተኛ ስሜትን ምቀኝነትና ክፋቷን አስተውላ ስትገምተው ያው ሌሎች አበሾች እንዳለባቸው የቅናትና የጥላቻ ስሜት እሷም እንዳለባት ገምታ ስታውቅ እራሷን ትታዘባለች።

ሮዚ ስትደሰት ቅብጥብጥ ያደርጋታል። መሳቅ መዝፈን መቀለድ መጫወት ይቀናታል። እስክስታም ለመውረድ ይቃጣታል። ደስታዋ ሲጋሽም ወደ ላይ እንጠር እንጠር እያለች እንደ ሕፃን ትቦርቃለች። እንዲህ ያለው ስሜት አይብዛ እንጂ አልፎ አልፎ በጣም ደስ ሲላት የምታደርገው ጠባይ ነው። የደስታዋ ምንጭ ግን ከየት እንደሚመጣ ጨርሶ አታውቅም።

ሮዚ ስታዝንና የሆነ ቅሬታ ሲሰማት እንደ አገር ቤት ልጆች አክርማ ቀጥፋ በጥርሷ እየሰነጠቀች አትተክዝም። አክርማም ጀርመን ውስቀ ብትፈልግ አታገኝም። በፋንታው ሲጋራዋን በከንፈሮቿ መሐል አጣብቃ በግራና በቀኝ በትከሻዋ የወረዱትን የሹርባ ክምር አንገቷን ሰበቅ ሰብቅ አርጋ በመበታተን በቀኝ እጅ ጣቶቿ ይዛ ፊቷን በሀዘን ክሽም አድርጋ ወደቀኝና ወደ ግራ ታፍተለትላቸዋለች። ትገምዳቸዋለች። ድንገት ብልጭ ካለባት ደግሞ ፀጉሯን ሳብ አድርጋ መንጨቅ እያደረገች መልሳ ትፈትላቸዋለች ትቋጨዋለች ትፈተልጋቸዋለች። ታፍጨረ ጭራቸዋለች የብስጭቷ መወጫዋ የሀዘን መተከጥዋ የውበት ግርማ ሞገሷ በቀጭኑ የተፈተሉት ሹርቤ ፀጉሯ ናቸው።

ሮዚ ሁሉን ጨራርሳ ከቤት ወጣች። የግል መኪናዋን አቁማ ሊሞዚን ከሆነ ታክሲዋ ውስጥ ጥልቅ አለች። ለሴንተራል አመልክታ የለሊት ሥራዋ እንዲቃና ግንባሯን አማተበች። ሲጃራዋን ለኩሳ ሙዚቃዋን ከፍታ በለመደችው ፍጥነት ወደከተማው እንብርት ፈረጠጠች።

የሰኞ የትራፊክ ምሽት እንደ እሁዱ የሚያወላዳ አልነበረም። ፍጥነትን ያለገደብ ለቆ በመኪና ፈረስ መጭ! ተብሎ የሚጋለብበት አራተኛና አምስተኛ ማርሽ አግብቶ እንደ ጥይት ሽው ፈትለክ ተብሎ

የሚነዳበት አልነበረም። የበጋውን አየር የሚሻማ እግረኛ፣ ቢስክሊተኛ የሕፃናት ጋሪ የሚገፉ እመጫቶች፣ ከትምህርት በኋላ በየመንገድ የሚጫወቱ ሕፃናቶች፣ ተሽከርካሪ በተገጠመለት ጫማ እየተንዱ ጉብጠው ከወዲያ ወዲህ የሚበሩ ወጣቶች ሰፈውን ጉዳና አጣበውታል።

ሮዚ የTic Tac Toc ፈጣን ሙዚቃ እያዳመጠች ሹሩቤዋን አንደ Tic Tac Toc ዘፋኝ Lee ወዲህና ወዲያ ብትን ዘርጋ እርግፍ ግፍ ግፍ እያደረገች ከዋናው ጉዳና እየበረረች መጣች።

የመኪናዋን ፈጥነት ትንሽ ቀነስ አድርጋ ወደጠባቡ መንገድ ወደ ግራ ተጠመዘዘች። አንድ የሆነች ሴት ችኩል ብስኪሊተኛ ድንገት ሳታስበው ጥልቅ ብላ እፊቷ ላይ ድቅን! አለች። ሮዚ በድንጋጤ ክው! ብላ ፍሬን ረግጣ ሳትገጫት ለጥቂት ሳተቻት።

ቢስክለተኛዋ ከሩቅ ሆና በማይሰማ ቋንቋ በንዴት ለፈለፈች። ጥፋቱ የሷ መሆኑን ብታውቀውም እንዲህ ያለው የግልምጫ ጩኸት ማንኛውም ብስክለተኛ የሚያደርገው ልማድ ነው።

ሮዚ የሴትየዋን ስድብ ጨርሶ አልሰማችም። ቀልቧ በንዴት ተገፏል። መኪናዋን የሆነ ጥግ አሲዛ አቆመች። ሰውነቷ በበጋው አየርና በድንጋጤው ግሎ አላባት። የሆነ ሶፍት ብጤ ከቦርሳዋ አውጥታ የፊቷን ላብ አደራረቀች። በረሸሙ ተንፍሳ «ቅዱስ ገብርኤል እንኳን ከዚህ አወጣሽኝ» ብላ ግንባሯን አማተበች። ክፉ ነገር ሲደርስባት የሚታያት እሱ ብቻ ነው። በእርግጥም ለዚህ ታላቅ ታቦት ያላት እምነት የጸና ነው።

ድንጋጤዋ ትንሽ በረድ ሲልላት ሲጃራዋን ለኩሳ በሌላ ጣቷ ፀጉሯን እያፍተለተለች ተከዘች መኪናዋን አስነስታ የሁትኒ ሁስተንን ዘፈን አድርጋ ስቴፕ ባይ ስቴፕ የሚለውን ሙዚቃ እያዳመጠች ፍጥነቷን እንደ ሙዚቃው ስልት አስተካክላ ወደ ድንጋይ በር ቀበሌ የሞቀ መንደር ገባች። ታክሲዋን እንደ ሌሎቹ ቅደም ተከተል ተራዋን አሲዛ ጠበቀች። ከአደጋ የሰወራትን መኪና አበክራ ጀርመኖች መኪና ይሥሩ ብላ አደነቀች። በሹፌርነቷም ኮርታ እራሷን በኩራት አመጻደቀች። ያኔ በሕፃንነቷ የአባቷን የቆመች ቮልስ ቫገን መኪና ውስጥ ገብታ ከመሪው ጋር ስትታገል ትዝ ብሏት ሳቀች።

ሮዚ ተራዋ ደርሶ የመጀመሪያውን የታክሲ ቦታ ያዘች። ድንገት አንድ አፍሪካዊ ዘሎ መኪናዋ ውስጥ ገባ። ሐጐስ መስሏት ድንግጥ ብላ ነብሷ ከሥጋዋ ተለየ። ተሳፋሪው ስሜቷ አልገባውም «ሃሎ ሲስተር» ብሎ ሰላምታ ሰጣት።

«ሃሎ ብራዘር» ብላ አልመለሰችለትም። ድንጋጤው አደናግሯትም ይሁን ወይም በጥላቻ የሚሄድበትን ቦታ ብቻ ጠይቃ ሞተሯን አስነስታ ተፈተለከች። ሮዚ እሷ ጥቁር ሆና ለምን ሌላ ጥቁሮችን እንደምትጠላ አይገባትም። ነጮችንም ቢሆን ከልብ አትወዳቸውም። ግን ከጥቁሮች ይሻላሉ ብላ ትገምታለች።

ተሳፋሪው ለሰላምታው ምላሽ ባለማግኘቱ እንብዛም አልተናደደም። እንዳውም ሹፌርነቷን አድንቆ የየት ሀገር ተወላጅ መሆኗን ጠየቃት። እሱ ከምዕራብ እሷ ከምሥራቅ አፍሪካ መምጣታቸውን ተገላልጠው ያለበት ቦታ ደርሶ ሂሳቡን ከፍሎ በፈገግታ እያያት ከመኪናዋ ወረደ።

አንዱ አንዱን ሲጎቅ ጀንበር ጥልቅ እንደሚባለው ሆኖ ሮዚ:-

«እኔ ጥቁር ሆኜ ጥቁር ሰው አልወድም

ሰይጣን ይመስለኛል የዳቢሎስ ወንድም»

ብላ እየዘፈነች በራሷ እያላገጠች። ተመልሳ ወደከተማው እንብርት መጣች። የተለመደውን የታክሲ ቦታ ይዛ ተራዋን ጠበቀች።

አንድ በደንብ የለበሰ በእድሜው ትንሽ ገፋ ያለ ሰው ታክሲዋ ውስጥ ገባ። ሮዚ ብዙ ሳትቆይ ሌላ ደንበኛ በማግኘቷ ደስ አላት። እንግዳው የሚሄድበትን ቦታ ነግሮ ሲጀራ ማጨስ መቻሉን በትህትና ጠየቃት። ፈቀደችለት። አውጥቶ አጨሰ። ሮዚ የመጠጥ ፋናና የሲጀራ ጢስ አወዳት። በግራ በኩል ያለውን መስኮት ዝቅ አርጋ ከፈተችው። በቀኝ በኩል የተቀመጠው ተሳፋሪ አድራጐቷን አነዳድና የመንገድ አመራረጧን አደነቀ።

«ጥሩ ነው የሚነዱት አቂራጩንም በደንብ አውቀውታል ለመሆኑ ስንት ጊዜ ሆንዎት? ታክሲ ሲነዱ።»

«አንድ ሁለት ዓመታት አለፈኝ።»

«ከውጪ ለመጣ ብዙ አይባልም» ብሎ «እርሶ» እያለ አንዳንድ ጥያቄዎችን በአንቱታ አከብሮት አቀረበ። ጀርመን ውስጥ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኙ በአንቱታ ነው። በደንብ ግን ከተዋወቁ ወይም ወዲያው «አንቺ» በሉኝ «አንተ በይኝ» ከተባባሉ በዚሁ አነጋገር ስልት ይቀጥላል።

«ግን ይሄን ቁንጅና ይሄን የለጋ እድሜ ይዘው ይህን ሙያ መምረጥዎ...ይሻላል?»

«ምን ይደረግ ቁንጅና ታጥቦ አይጠጣ።»

«ማለቴ ለፎቶ ሞዴል ለፊልም ተዋናይነት...»

«ጀርመኖች ለዚህ እኔን መርጠው? ድንቄም እቴ ለዚሁም የሚቀ ኑብኝ ብዙ ናቸው። ምናልባት ባሉት ሙያ ጥቁሮች እድል ያላቸው አሜሪካን ሊሆን ይችላል። እዚህ ግን ይቅርታ አድርጉልኝና ዘረኝነቱ «እኛ ጀርመኖች ከሁሉ በላይ ነን» ማለቱ አሁንም አልቀረ። ተሳፋሪው «የሚሉት ትክክል ነው። ግን ቢሞክሩ ጥሩ ነው» ብሎ የሚወርድበት ቦታ ደረሰ። መልካሙን በመመኘት ሂሳቡን ከፍሎ ወረደ። ሮዚ «ጐመን በጤና» ትከሻዋን ከወዲህ ወዲያ ነቀነቀች። «እወቂኝ እወቂኝ ማለት በኋላ ደብቂኝ ደብቂኝ» ያመጣል ብላ ተረቱን ለራስዋ ተረተች።

የሆነ የታክሲ ማቆሚያ ቦታ ሮዚና ጆኒ ተገናኙ። ልክ ተለያይቶ እንደ ከረመ ዘመዳሞች ተቃቅፈው ተሳሳሙ መኪናቸውን ጥግ አሲዘው ቡና ለመጠጣት የሆነ ቦታ ጐራ አሉ።

ያለፈው ለሊት ጆኒ ሮዚን ፍለጋ የደከመውን ድካም በጠቡ ተበሳጭቶ ሥራ እንኳን በደንብ አለመሥራቱን በመጨረሻ ሁኔታውን ለፖሊስ ማስታወቁን ዘርዝሮ ነገራት። ሮዚ ጆኒ የነገራትን ሁሉ ከክላውዝ ሰምታዋለች። እሱ ለእሷ ያላትን የወንድምነት ፍቅር ታውቃለች። ግን አንድ ብስጭት ሲያጋጥማት ከማንም ሰው ጋር መነጋገር አትፈልግም በሯን ጥርቅም አርጋ ዘግታ ጥቅልል ነው። ስልክ ቢጮህ ቢንጣጣ አታነሳም ወዳጅና ዘመድ ለእሷ ቢቸገሩ ባይቸገሩ ግድ የላትም።

«ይቅርታ ጆንዬ ጠባዬ ሆኖ ሲከፋኝ ከሰው መነጋገር አልፈልግም ብቸኝነቴን እመርጣለሁ»

«አይደለም ሮዚ የተጣላሽው ከሀገራችን ሰው ጋር ነው ዝም ብለን የምናልፈው ጉዳይ አይደለም ተመልሶ እንደገና ሊጣላሽ ይችላል።»

«ጆኒ ልከ ነህ ብቻ እልህ ንዴት...» ብላ ያለፈውን የሐጐስንና የእሷን ጠብ ዘርዝራ አሜውተችው። ዓይኖቿ እንባ አቆረዙ። በሁኔታው አልቅሳ ተንዘፈዘፈች። ጆኒ አብሯት አዘነ። ብርታት እንድታገኝ ሐጐስን ፈልጐ ልክ ልኩን እንደሚነግረውና ለወደፊቱ አጠገቧ እንደማይደርስ አስጠነቅቀዋለሁ። እርቅም ከፈለገ አስታርቃችኋለሁ ብሎ ትከሻዋን በሁለት እጆቹ ጨብጦ «አለሁልሽ» በሚል ስሜት አየነቀነቀ አባበላት። የወንድምነት እውነተኛ ፍቅሩን ለመግለጥ ከደረቱ ጋር አጣብቆ አቀፋት ለማንኛውም እለታዊ ችግር ተገን እንደሚሆናት እየፎከረ በመሐላ ቃል ገባላት።

ሮዚ ወደ ሽታይን ቶር (Steintor) ጆኒ ወደ ኤድል ቫይስ (Edlweiss) የምሽት ሥራቸውን በትጋትና በቅልጥፍና ለማከናወን መኪናቸውን አስነስተው በተለያየ አቅጣጫ ተሰነባብተው ነጐዱ።

ሮዚ የታክሲዋን ተራ ጠብቃ እያንሸራሸረች ወደ ፊት ገፋ ጠጋ እያደረገች የመጀመሪያውን ቦታ ያዘች። አንድ የተተለተለና የተጣፈ ጅንስ ሱሪ የታጠቀ ከላይ እጅጌ ጉርድ ሸሚዝና የቆዳ ሰደርያ የለበሰ ወደ ታክሲዋ ተጠጋ። ፀጉሩ በአረንጓዴ ቀለም ቀልሟል። በግራ ጆሮው ትልቅ ሎቲ አንጠልጥሏል ክንዶቹ ላይ ንቅሳት ያለበት ፓንከር ጀርመናዊ የሮዚን መኪና በር ብርግድ አድርጐ ዘው አለ። ሮዚ ደንግጣ ክው አለች። ውቃቢዋ ተገፈፈ። «ውይ እድሌ ክፉ ነገር አታምጣ» ብላ ፈጣሪዋን ተማፀነች።

ሒሜሊንገን ወደተባለው አሩቅ ቦታ 12 DM እከፍልሻለሁ የሂሳብ መቁጠሪያ ሰዓቱን አጥፊው» አላት ትእዛዝ በተቀላቀለበት አንደበት። ትንፋሹ ግን እንደሰከረ ሰው አይሸትም።

«በአሉት ዋጋ ተመን አልስማማም የያዝኩት ታክሲ ማንኛውም ተሳፋሪ ሲቀመጥበት መቆጣጠሪያ ጨረርና የዋጋ ተመን የሚያሳይ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መክፈል አለብዎት።» ብላ ጣቷን ወደ ሂሳብ መቆጣጠሪያው ሰዓት እያመለከተች ፊራ ተባ በሚል የተቆራረጠ አንደበት አስረዳችው። «ፖሊስ ስለሆንኩ በቶሎ ያልኩሽ ቦታ ውሰጂኝ» አላት ትከሻውን እያውረገረገ አንገቱን ቀና አድርጐ የሥራውን ሙያ ሳያስበው ከአፉ አፈትልኮ።

ታዲያስ ፖሊስ ቢሆኑ ያለበቂ ሂሳብ ተጓዙ የሚል ሕግ አለ?» ብላ ሀገሯ ብዙ ታክሲ ነጂዎች ለትራፊክ ፖሊሶች የሚያደርጉት ነፃ አገልግሎት ትዝ ብሏት እዚህም ለነሯ ለባሽ ፊርማ ቶሪ ይደረግ እንደሆን ተጠራጠረች።

«ያልሽውን እከፍላለሁ እንሂድ» ብሎ ደስ የማይል ፈገግታውን ገለፈጠባት። መኪናው ተንቀሳቀሰ። የሂሳቡ ሰዓት 3.80 DM ጻፈ። ሂሳቡ እንዳ መንገዱ እርዝማኔ በኪሎ ሜትር 2 DM እየጨመረ ወደ ተባለው ስፍራ አብረው ተጓዙ።

«አንቺ ብዬ ስለጠራሁሽ ይቅርታ» አላት ፖሊሱ «ግድየለም ታክሲ ነጂ አይደለሁ በፈለጉት ይጥሩኝ» አለች አልባሌ ቢመስልም በፖሊስነቱ እያከበረች። «አንቺም እንደኔ አንቱታውን ትተሽ አንተ ብትይኝ ደስ ይለኛል» አላት እየሳቀ። ሳቁ እሷንም አሳቃት። የሁለቱ ግንኙነት አሁን ከመፈራራት ደረጃ አልፎ ተዝናንቶ ወደመነጋገሩ ተቀራረበ። የሮዚ ትንሽ ልብ የትርታ ፍጥነቱን ቀነሰ። ፖሊሱ ስሟን ሳይጠይቃት ከየት እንደ መጣች ጀርመን ምን እንደምታደርግ ጠየቃት። ሮዚ የመጣችበትን ገምቶ እንዲናገር ሥራዋ ያው የታክሲ ሹፌር መሆኑን ነገረችው።

ፖሊሱ ከብራዚል ከኩባ ወይም ከጃማይካ እያለ ሲቀበጣጥር ከላቲን አሜሪካ እንደ ዕድልም ሆኖ ከጀርመን ዘር አለመፈጠሯን ገልጻ ከምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ሌላ ሙከራ እንዳያደርግ እድል ሰጠችው።

"Somalia? Kenia? Eritria?" እያለ አሁንም ሲቀበጣጥር ሮዚ የኤርትራ ስም በመነሳቱ ብስጭት አድርጐ የትላንቱን የሐጐስን ጠብ አስታወሳት። ንግግሩን አቋርጣው «ይገባሃል? ኢትዮጵያዊ ነኝ» ብላ ትከሻዋን እየወዘወዘች አንገቷን እየነቀነቀች ጐላ ባለና ጉራ በተቀላቀለበት አንደበት እሷነቷን ዜግነቷን አሳወቀችው። እሳ ብዙ ቆንጆ ሴቶች እንዳሉ አድንቆ ነገራት። «በርግጥ ሞልተዋል እኔንም እዚሁ ማየቱ በቂ ነው» አለች ቁንጅናዋን በፈገግታ አቆንጅታ የሳይኖጅን መጠቋቆር እንዳያይበት አፈር ብላ ወደ ጐን እያየች። ነገሯንም ቀጠል አድርጋ ከሴቶች ቁንጅና ሌላም ብዙ ውብ ነገሮች እንዳሉ ነገረችው።

ፖሊሱ «አዎ በርግጥ ቆንጆ ልጅ ነሽ እንዳንቺ ያለ ውብ ሴት ለምን ታክሲ ይነዳል?» ብሎ ሌላ ሀሳብ ሳይጨምርበት ሀሳቡን ለውጠ የብሪማን የሴት ጠለፋ ወንጀል በሀሳቡ እየታየው ሙያዋ አደገኛ መሆኑን ገልጾ እንዳትሰጋ ያላትን ድፍረት አድንቆና አክብሮ ጠየቃት።

«ምን ላድርግ በተማርኩት ሙያ ሥራ አጣሁ» ብላ ዋሸችው። «ምንድነው የተማርሽው? ብሎ ዝብዝብ እንዳያበዛ የንግግራቸውን አዝማሚያ በልዩ ጥያቄ በቅጽበት ለወጠችው።

«እውነት አንተ ፖሊስ ነህ?» አለችው መታወቂያውን ከኪሱ አውጥቶ አሳያት።

«ይገርማል ይቅርታ አርግልኝና ሲያዩህ የመንገድ ጀንኪ ወይም ፓንከር ነው የምትመስለው»

«መሆን አለበት አለበለዚያ የከተማ ወንበዴና የድራግ (እፅ) ነጋዴዎች (Dealer) ለማጥመድ ይከብዳል። እነሱን መስሎ መጠጋት ያስፈልጋል።» አላት በሀሳቡ የሥራውን አደገኝነት ከሮዚ ሹፌርነት ጋር አብሮ እኩል እያወዳደረ። ቀጠል አድርጐ «እንደሚመስለኝ ብሪማን ውስጥ የመጀመሪያዋ ጥቁር ሴት ታክሲ ነጂ አንቺ ትመስይኛለሽ ወይስ ሌላ አለ?» ብሎ ጠየቃት።

«የለም እኔው ነኝ ያለሁት» ብላ የመጀመሪያ ጥቁር ሹፌርነቷን እያደነቀች ደረቷን በኩራት ነፍታ አንገቷን እየነቀነቀች መለሰችለት።

ስለሥራዋ ድፍረት በጋዜጣ እንዲወጣ ሀሳብ አቀረበ። «መታወቅ ምን ይጠቅማል ብለህ ነው? ሁሉም ወሬ ነው። እንዳውም እጅግ መታወቅ ያስጠቃል። ብዙ የታወቁ ሰዎች እድለኞች አይደሉም። እንደዚሁ ሳልታወቅ ኑሮዬን መኖር እሻለሁ። በዚህም በቂ ደስታ አለኝ።» አለችው። «አንተስ? ብላ ጀምራ «ግን ለምንድነው ፖሊስ መሆንክን ሳልጠይቅህ የነገርከኝ» አለችው። ሰውዬው በጥያቄው ዱብዳ ድንግጥ ብሎ «ወንጀል ላልሠሩ እንዳንቺ ላለ ንጹህ ሰው መናገሩ አይጐዳም። እንዳውም ፍቃደኛ ከሆንሽ በዚሁ ሥራ ላይ ሆነሽ አንዳንድ ነገሮችን በመጠቆም የምትጠቀሚበትን የፊርማቶሪ ሥራ ልንሰጥሽ እንችላለን» አላት።

ሮዚ «ከምጣዱ ወደ ረመጡ» ይቅርብኝ ይሄው የያዝኩት ይበቃኛል» አለችው።

ፖሊሱ የሚወርድበት ቦታ ደርሶ ሂሳቡን ከጉርሻ ጋር ከፈላት። በፈገግታ አተኩሮ እየተመለከታት «የሆነ ችግር ሲያጋጥምሽ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውይልኝ ብሎ ካርዱን አውጥቶ ሰጣት። "Thank you" የእኔም ካርድ ይኸውልህ ብላ ሰጠችው።

ሮዚ የታክሲ ሥራ ከጀመረች ጀምሮ ከነጠጠ ከበርቴ ከታወቀ ጠበቃ ከሴናተርና ከሌላም ታላላቅ ሰዎች የሰበሰበችው ካርዶች ብዙ ናቸው። ግን ሆን ብላና አስባ ለአንዳቸውም ደውላ አታውቅም። በአጠቃላይ ወንዶች ትልቅም ይሁኑ ትንሽ ያገቡም ይሁኑ ፈት ወይም ወንደላጤ ሴትን የሚፈልጓት ለአንድ ጉዳይ መሆኑን ልቧ አጣርቶ ያውቃል። አንድ ጊዜ አንዱን ደውላለት እራት ጋብዟት «ልተኛሽ» ያላትን አትዘነጋ ውም። «ወንዶች ጉረኞች ሀብትማ ሲኖራቸው ሴትን እንደ እቃ እኮ ነው የሚያዩት» «ታክሲ ለምን ትነጂያለሽ እኔ ላግባሽና አርፈሽ ቁጭ በይ» የሚለው ሽማግሌ ሌላው ብቸኝነት ያጠቃው «አብሬው እንዳወራ እንቆይ ብቻ ገንዘቡን ተማምኖ «ይሄን ልክፈልሽ፣ አሻንጉሊት ላርግሽ» የማይለው የለም። ውይ ወንዶች ይህ የታክሲ ሥራ ስንቱን አሳይቶኛል። ታዘብኳቸው። እኔ ልጅቷ «ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ» ብላ ተረቱን ለራሷ ተረተች።

ሮዚ በእርግጥም ከዚህም ከዚያም መባለግና መቀባበጥ ጨርሶ አታደርገውም ያስጠላታል። ግን ከሁሉ አብራ ስለምትጫወትና ስለም ትሳሳቅ ከሩቅ የሚያይዋት የሥራ ጓደኞቿና ሌላ ሰዎች ባለጌ መስላ ቻቸው ያሟታል። እሷንቷን ስለምታውቅ ለእጉል ሀሜት ሥፍራ አትሰ ጠውም። በእርግጥ ክላውዝን ትወደዋለች ከሱ ሌላ ወንድ ወንድ መስሎ አይታያትም።

ሮዚ ሌላ ብዙ የተለያዩ ብሮች ከፉንክም ከመንገድም ለቃቅማና አግኝታ አሰባስባና ተሯሩጣ የእለት የምሽት ገበያዋ ጠርቀምቀም ብሏል። የገንዘብ ማስቀመጫ ቦርሳዋ በብር እረብጣ–ጠግቦ ተወጥሯል። ሆዲ ግን ከመሸ ምንም ስላልቀመሰች ባዶ ነው። በእለቱ አብሯት

የሚያባላት ከላውዝ ሥራ አልገባም። ጀኒን በቶንክ አስፈልጋ አጣችው። ብቻዋን ዘወትር ከምትመገብበት "Kismet" ከሚባለው ምግብ ቤት ለመግባት አቀደች። ታክሲዋን አመቺ ቦታ አቁማ በእለቱ ያደረገችውን ነጠላ ጥልፍልፍ ጫማ እግሮቿን ስለወጠሯት የመኪናዋ ፔዳሎች ላይ ዘረጋግታ ዘለበቱን አላላችው። በእርግጥ የጫማዎቿ ማሠሪያ ጠፍር ከወጠጤ ፍየል ቆዳ እንደተሠሩ ሁሉ ሎሚ ተረከዞቿን የሚያምሩ የእግር ጣቶቿን እንደሚዋደዱ ፍቅረኞች ጥርቅም አርገው ይዘዋት ነበር። የቶን ኩንና የሬዲዎኑን መዘወሪያ ቁልፍ ወደ ግራ ዘውራ አጠፋፋቻቸው። የእፎይታ ትንፋሽ ተንፍሳ መኪናዋን ቆላልፋ ወደምግብ ቤት ሄደች።

ልክ እሷ እንደ ወጣች የመኪናዋ ቁሳቁሶች በከፊል እንደ ሰው ተመሰለው እርስ በእርሳቸው ተንጫጩ ሀሜትና እሮሮ ከሮዚ ጋር ያላቸውን ፍቅርና ጥላቻ አፍ አውጥተው ተናገሩ ለፈለፉ። አቶ የቤንዚን መስጫ ፔዳል የቀበሮ አፍንጫ በመሰለ በዛ ታኮ ጫማ ሮዚ አየረገጠች አናፍጣ የምታደማው የቤንዚን ደም ብዛት አንገፍግፎታል። ከሥር ሆኖ ወደ ላይ እየተመለከተ በቀጭኑ የተፈተለ ትልቅ ልቃቂት የመሰለውን የሮዚን ባትና ጭን ውበት ያድንቅ እንጂ ምሬቱ እሮሮውና ወቀሳው ሌላ ነው «ቶሎ! በል ፍጠን! ገሥግሥ! ብትችል ከነፍ!» እየተባለ የሚቀም ሰውን እርግጫና ጡጫ አይጣል ነበር። በዚህ ምክንያት ምርር ብሎት «ሌሎች ሹፌሮች ነካ ነካ አሸት አሸት አርገው በለሰለሰ ሥልት ገፋ ገፋ ሲያደርጉኝ የዳሰሱኝ እንጂ የተጫኑኝ አይመስለኝም። እየኮረኮሩ የሚያስቁኝ ነው የሚመስለኝ። ሮዚ ግን አይጣል ነው። የእርግጫ አመል እንዳለበት አህያ ወይም በቅሎ መንጋጭላዱን ታናፍጠኛለች። ሆድ ቃዬን ተጭና ትዳምጠኛለች። ጭንቅላቴን ጨፍልቃ መጭ! እያለች ታሰግረኛለች። ትጋልበኛለች። ታስጋልበ ኛለች። እንደ ንፋስ በርሬ እንድ ፈረጥጥ ታደርገኛለች። የደም ቤንዚንና ናፍጣ እየነሰርኩ አታዝንልኝም መልሳ መላልሳ ትረጋግጠኛለች እኔስ እኔ ነኝ መጥኔ እሷን ለሚያገባ...» ብሎ በመንገፍገፍ አራሱን ነቅንቆ ብስጭቱን ገለጠ።


ከጐኑ ያለው የፍሬን ፔዳል የጐረቤቱን አባባል አዳምጦ ታዘበ። «አባይን ያለየ ምንጭ ያመሰግናል» ብሎ ተረተ። «እንደኔ ሆነህ ባታየው ነው ጃል። ለትንሹም ለትልቁም እንደ ነጋሪት እየተጐሰምኩና እየተነረትኩ የምጠለዘው ከአንተ ይልቅ መጠን የሌለው እርግጫ

የምቀምሰው እኔ ጐረቤትህ ፍሬን ነኝ ለቀይ ማብራት እርግጫ። ከሌላ መኪና ግጭት ለመትረፍ እርግጫ ለአጥር፣ ለገደል፣ ለተከለከለ መንገድ እሩጫ ጫን ያለ እርግጫ የምቀምሰው እኔ ነኝ። ለእግረኛ ለቢስክሊት ለድመት ይሁን ጥንቸል ለውሻ ይሁን ለሌላ እንስሳት ሮዚ የሆነ ነገር ውልብ ሲላት ያላግባብ ትጠልዘኛለች። በእርግጫ ከአደጋ እንድሰ ውራት፣ ከፍጥነት እንድገታት ባለ በሌለ ጉልበቷ ወደ ታች ተጭና የምትረግጠኝ ከአንተ ይብስ እኔን ነው። እሪ ብዬ በሲጢታ ብጮህ ባታስት እንደ ቁብ ዶሮ ባስካካ ከጐማ ጋር ሆኜ ምድሩን ብቧጥጥና ብጭር ማን ሊሰማ! እንደ ፈረስ ልጓም ማንቁርቴን ወደኋላ ስባ በእርግጫ የምትጨፈልቀኝ ፍሬን ማለት እኔ ነኝ። ጀርባዬ እንደ አጋሠስ በጭነት ብዛት ቆስሎ ባይገባበጥም የሁሉ ጭቆናና እርግጫ በኔ ላይ ብቻ መሆኑን እመነኝ» እያለ አቶ ፍሬን ለጐረቤቱ በምሬት ሊያስረዳ ሞከረ።

የሁለቱን ወቀሳና እሮሮ ቁጣና ሀሜት በጥሞና የሰማው ሌላው ጐረቤት አቶ ፉሬሲዎን ከት ብሎ ሣቀ። የስንቱ ሹፈር ያልታጠበ ካልሲ ያልተለወጠ ወፍራም ጫማ ግማትና እርግጫ ያንገፈገፈው አቶ ፉሬሲዎን የሮዚን ለስላሳ ጫማ ያለውን ጽዳትና መአዛ እየወሰደ አሞገሠ ለጐረቤቶቹ ለአቶ ፍሬንና ቤንዚን መስጫ ከሮዚ ጋር ያለውን የፍቅር ወዳጅነት በለዘብታ ገለጠላቸው።

«የውሻ ምላስ በመሰለ የታኮ ጫማዋ እርግጫ ልዩ ሰመመን የሚሰጥ ዳበሳ እንጂ ምሬት ያለበት ጥለዛ አይደለም። በተለይ አየሩ ሞቅ ሲል ያን ታኮ ጫማዋን ወደ ጐን ፈንጠር ፈንጠር አድርጋ በባዶ እግሯ ነካ ነካ ዳበስ ዳበስ አርጋ ጫን ስትለኝ ሰውነቴ ይቀነዝራል። በተለይ ቁንጣ ሱሪ ወይም ሚኒ ሮክ ስትለብስማ ከታች ሆኜ የባትና የጭኗን ውበት እየተመለከትኩ የምቀምሰው የእግር ጥፊና እርግጫ ሕመም ጨርሶ አይሰማኝም። ትንሽ የሚጐረብጠኝ ከዋለ ካደረ በኋላ ነው። በወቅቱ ግን የሚሰማኝ በፍቅር ዳሰሳና እርግጫ ጣመኝ ድገመኝ የሚያሰኝ የደስታ ሰመመን ነው።...ብሎ ሌላ ሳይቀጥል ሮዚ መኪናዋን ከፍታ ዘው አለች። ሁሉም ደነገጡ ውይይታቸው ከመቅጽበት ተቋረጠ። ዝም በሉ! እንደተባሉ ሕፃናቶች ሁሉም አፋቸውን የዘው ጭጭ አሉ። በእርግጥ

ሮዚ ድንገት ገብታ ባትረብሻቸው ኖሮ ማርሽም ሆነ መሪ የወቀሳ ሳይሆን የውደሳ አስተያየት ለመስጠት ፈልገው ነበር። በወቅቱ ግን የሚለው አይሰማ እንጂ ደፍሮ የተነፈሰው እንደ ኮርቻ የሚደላው የመኪናዋ መቀመጫ ወንበር ነበር። የሱን ቦታ ለመያዝ ስንቱ ወንድና ስንክ ሣር እንደ ምድር አሸዋ የበዛ መሆኑን ስለሚያውቅ የመቀመጫነት ክብርና ሞገሱን ይዞ ሮዚን እንደ ሕፃን ልጅ እሹሩሩ እያለ አቅፎና ደግፎ እንደ ኮርቻ የመቀመጫነት ማእረጉን ሳይለቅ የእሷ ጥሩ ወንበር ሆኖ መቅረቱን መረጠ።



ሮዚ – የመኪናዋ ቁሳቁሶች ያሉትን አል ሰማችም። መኪናው እስከሮጠ ለእነሱ ያላት ስሜት የላላ ነው። ሊረ ገጥ የተፈጠረ መረገጥ ሊዘወር የተሠራ መዘ ወር፣ ሊገፉ የተበጀውን መግፋት እንደሚገባው ታውቃለች። ለዚህ ዝባዝንኬና ቁሳቁስ ትርኪምርኪና ቅራቅንቦ ግድ የላትም እሷ የምት ወደው ክላውዝን ብቻ ነው። ሮዚ ሲጃራዋን ለኩሳ ሙዚቃዋን ከፍታ ሞተሯን አስነስታ ከዛ መርካቶ መሰል አካባቢ ፈትለክ ብላ ወጣች።

ሮዚ ሰዓቷን ተመልክታ ለክላውዝ ስልክ ለመደወል መኪናዋን ጥግ አሲዛ የሕዝብ መደወያ የቴሌፎን ሳጥን ውስጥ ገባች። ማነጋገሪያውን አንስታ ካርዲን ሻጥ አደረገች። ቁጥሮቹን በሌላ ጣቷ ነካ ነካ ማዶ ጭርርር! ጭርርርር! ሮዚ «ሃሎ!» ዳርሊንግ

«ሃሎ!» ሊብሊንግ።

«እስካሁን አልተኛህም።»

«አጠናለሁ ፈተና የሚቀጥለው ሳምንት አይደል።»

«እረሳሁት በርታልኝ የኔ ቆንጆ የኔ ፍቅር።»

«እባክሽን ለምን እንደሆን አልገባ ብሎኛል።»

«ፍቅር ይዞህ ይሆናላ።»

«ከማ?»

«ምን አውቃለሁ አንተው ንገረኝ እንጂ።»

ክላውዝ እሮዚ ያለችው እውነት መሆኑን ቢያውቅም አፍሮ «እባክሽን ፍቅር አይደለም።»

«ታዲያ ምንድነው?» ክላውዝ እንደሚያፈቅራት ብታውቅም ለምን «እወድሻለሁ አፈቅርሻለሁ» ብሎ እንደማያውቅ ይገርማታል። መልሱን ሳትጠብቅ «በቃ ጥናቱ ካልገባህ ተወው» «ፈተና አለብኝ እያልኩሽ እንዴት ልተወው?» ዓይንሽንስ በጉ ሆንሽ? ትንሽ ተሻለሽ?»

«አዎ በጣም ተሽሎኛል»

«ሥራስ እንዴት ነው?»

«ጥሩ ነው። የዛሬው ምሽት ከነጭ ለባሽ ፖሊስ ጋር አስተዋውቆኛል።»

ክላውዝ ትንሽ የቅናት ስሜት ብን ስላለበት ሲጃራውን አቀጣጥሎ ቡን በማድረግ «የፖሊስና የቤንዚን ዝምድና ይቅርብሽ» «አንዳንዴ ይጠቅማል ያንንም አጋሜ ትላንት የተጣላኝን «እሱን ለኔ ተይው ይቅርታ» ብሎ ስልኩን አስቀምጦ የጣደውን መረቅ ስለገነፈለ ምድጃውን ሄዶ አጠፋው።

«ምንድነው? የት ጠፋህ»

«መረቅ ጥጄ አሮብኝ ነበር»

«መጥቼ ላባላህ እንዴ?»

«በማን እድሌ» አለ እንደማትመጣ እያወቀ ቅር ብሎት።

«ስቀልድ ነው አልመጣም። መልካም ምግብ ይጣፍጥህ»

"Thank you my sweet!"

ሁለቱም የፍቅር ውይይታቸውን ሰለቁ። በአንድ ቀን ልዩነት እረዥም ጊዜ እንደ ተለያዩ ሰዎች ተነፋፈቁ። በፍቅር ለመተቃቀፍ ትንፋሽ ለትንፋሽ እየተለዋወጡ አፍ ለአፍ ገጥመው መሳሳም ጐመጁ። አረፋ የሞላ የመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ገብተው እየተሻሹ ለመን ቦረጫጨቅ ወይም የፍቅር ግለትና ጥማቸውን ለመወጣት ዛሬ አልቻሉም። ሁለቱም በቀጭኑ ሽቦ የሞቀ ትንፋሻቸውን ፍቅርን ምኞታቸውን ተለዋውጠው ስልካቸውን ዘጉት።

ሮዚ በእለቱ እስከሚነጋ የሠራችውን ሠርታ ያተረፈችውን ገንዘብ ቁጥራ ብቻዋን እቤት ገባች። የእለቱ ሽቶ፣ የመጠጥ ታና፣ የመኪናው ናፍጣ የእሷ የድካም ላቦት ሽታ ተጨማምሮ ያቆሸሻትን በሻወር ሙልጭ አድርጋ በሳሙና ፈትጋ ታጠበች። ከላይ የሚወርደው ሙቅ ውሃ አረፋውን ወደታች ወደ ጭኖቿ መሐከል፣ እየገፋ ሲያወርድ እሷ ሁለመናዋን በልስላሴ እያሸች ስትለቃለቅ፣ ውሃው ከጠየመ አረፋ ጋር ሆኖ ከጀርባዋ እየተንሸራተተ ይወርዳል። እግሮቿ መሐከል የተጠራቀመው እጣቢ የቆሸሸ ውሃ እርስ በእርሱ ተያይዞ ተሰባስቦ አዙሪት እንደያዘው ውሃ እየሾረ እየተሽከረከረ በትንሹ የመውረጃ ሽንቁር ቀዳዳ ውስጥ እየተመጠጠ አልፎ ዘልቆ ሄደ። ሮዚ ለስላሳ ሰውነቷን በፎጣ አደራርቃ ቅባቷን ተቀባብታ ስስ የሐር ፒጃማዋን ለብሳ ሙዚቃዋን ከፍታ ሶፋው ላይ ዘርፈጥ ብላ ተዝናንታ ተቀመጠች። ቀና ብላ ግርግዳውን ስትመለከት የወላጅ እናቷ ፎቶግራፍ አፈጠጠባት።

ሲጃራዋን ለኩሳ ማግ ማግ እያደረገች ቀጥሎ የምታረገውን አሰበች። የወር መጨረሻ ስለሆነ ሰሞኑን የሠራችውን የገንዘብ መጠን ለማወቅና ሀገር ቤትም ለእናቷ ለመላክ ወሰነች። ከባንክ ቀናንሳ በየሥርቻው እቤት ያስቀመጠችውን ጉልጉላ ጠረጴዛው ላይ ዘረገፈችው። ብሩ እንዳልታወቀ የእህል ክምር እፊቷ ተቆለለ። በደስታ ተውጣ ብቻዋን ከት ብላ ሳቀች። ሌት ተቀን የደከመችበት የላቧ ዋጋ በመሆኑ ኮራች። በዛ ለጋ ጣቶቿ እያንዳንዱን የብር ኖት እያነሳች ቆጠረች። የብሩ ሽታ የቆየ የልጅነት ትዝታዋን እፊቷ አምጥቶ ደቀነባት።

እጆቿን ታጥባ የሆነ ሰፕሬ በክፍል ውስጥ እረጨች። ድሮ ልጅ ሆና እናቷ ወ/ሮ ቦጋለች ጭሰኞቻቸው ከሲዳሞና ከአሩሲ የሚሸጠውን ሸጠው ለቀለብ የሚሆነውን በአህያ እየጫኑ የሚያመጡላቸውን መጠን የሌለው እህል በላስኪት የተጠረዙ እረብጣ አሮጌ ብሮች እጭቅ እጭቅ የሚል ሽታና ብዛት ትዝ አላት። የጪሰኞቹ አለቃ ወደ እናቷ እጅ እየነሳ ቀረብ ሲል «አቶ እከሌ እንደምድነህ ደህና ነህ?» ብለው ጭሰኛው እግራቸውን ለመሳም ጠጋ ሲል «ደግ! ደግ! እዛው ሁን ቁጭ በል» እያሉ የገጠር ጉንፋን ብጤ ነገር እንዳይጋባባቸው በመጠንቀቅ በዘዴ የሚያገልሉት ሁሉ ታያት። ሠፈርተኛው በዓመት ሁለት ጊዜ ጪሰኞቹ ሲመጡ «ዛሬ የወ/ሮ ቦጋለች አህዮች ዲሞክስትሬሽን ቀን ነው» እያለ ያማቸዋል። በርግጥም ለጐረቤቶቹ የሚተርፈው ከገጠር የመጣው የእህልና ጥራጥሬ ፍሳሽ ሳይሆን የአህዮቹ ፋንድያ ብቻ ነበር።

ወይሮ ቦጋለች ደምቤና ፊታውራሪ አሥራት አበጀ ረዥም ዘመን አብረው በትዳር ይኖራሉ። ከአብራካቸው አንድ ወንድ ልጅና ሦስት ሴቶች አሏቸው። አንደኛዋ በደርግ ጥይት ስትሞት የቀሩት ውጪ ሀገር ናቸው።

ወይዘሮ ቦጋለች አብነት አካባቢ ያሠሩት መደዳ ሱቅ፣ ናዝሬትና አዲሳባ የሚያከራዩት ቪላ ቤቶች ሲዳሞና አርሲ የነበራቸው አሥር ጋሻ መሬት በአብዮቱ መፈንዳት ተወርሰዋል። የመጀመሪያ ልጃቸው ከ(E.P.R.P.) ጋር ሆና በማደጓ በደርግ ጥይት ተመታ አርፋለች። የቀሩትም ልጆቻቸው የሷን ፈለግ በመከተል መንግሥትን መቃወም ጀመሩ። ወላጆች ተባብረው በዘመድ አዝማድ በጉቦ ብርታት ሁሉንም ከሀገር አስወጧቸው።

በዚህም ምክንያት ይሁን የድሮ ሞጅነታቸው ልማድ ዘወትር የሚለብሱት ጥቁር የሀርና የሱፍ ድብልቅ ቀሚስ ነው። ባለቤታቸው ፊታውራሪ አሥራት ተበጀ ታታሪና ትጉህ ሠራተኛ ናቸው ሲዳሞ እንዳሉ በጃንሆይ ጊዜ ፓርላማ ተመርጠው የሕዝብ እንደራሴ ነበሩ። ከዛም በኋላ በጥብቅና ሥራ አገልግለዋል። አሁን ሁለቱም የሚተዳደሩት በወር በሚሰጣቸው የቤት ኪራይ አበልና የባልየው የጡረታ ገቢ ገንዘብ

ብቻ ነው። ብዙ ቤተሰብ ስላላቸው እውጪ ያሉት ልጆቻቸው የሚል ኩላቸውን ጥቂት ገንዘብ በማሰባሰብ አብቃቅተው በጥሩ ሁኔታ ይኖራሉ።

ሮዚ ጠረጴዛ ላይ፣ የቆለለችውን ገንዘብ ቆጣጥራ ለቤተሰቦቿ የምትልከውንም ለይታ አስቀመጠች። ለመኝታ የሚረዳትን ወተት አሙቃ ከማር ጋር አድርጋ ተቀመጠች። የእለቱን ዜና በTV ለመመልከት CNN ፕሮግራም ከፈተች ሰዎች ወደ ማርስ የሚያደርሰውን መንገድ ሲዳስሱ አየች «ዓለም ውስጥ ስንት የሰው እግር ያላረፈበት መሬት እያለ እዛ መንጠራራታቸው ‹የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች›» ብላ መልሳ TV አጥፍታ ትኩስ ወተቷን ተጐንጭታ ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች። እሹሩሩ እያለ የሚያስተኛትን ለስላሳ ሙዚቃ ድምጹን ዝቅ አድርጋ እያዳመጠች እንቅልፍ እንደ ቀልድ ሸለብ አድርጐ ሕልም እያሳየ ወሰዳት።



ክፍል ሦስት

የብሬመን ትልቅ የሕዝቡ መገበያያና መናኸሪያ ቀበሌ ሽታይንቶር (Steintor) ይባላል። ትርጉሙ የድንጋይ በር ማለት ነው። የሰው ግርግር የሚታይበት፣ የደላላ የከበርቴ መገናኛ፣ የነጋዴና የሸማች የገበያ ቦታ ነው።

አካባቢው ግራና ቀኝ የተለያዩ የንግድ መደብሮችን የያዙ አሮጌና አዳዲስ ትልልቅ ሕንፃዎች እንደዝናር ተጠጋግተው መደዳውን ተደርድረው እንደ ተራራ ተልቀው ይታያሉ። በመሐከላቸው ጠባብ የመኪናና ኣጭር የፉርጐ ባቡሮች (Strassen Bahn) ይተላለፋሉ። እግረኛና ብስኪሊተኛ ተጨምሮ መንገዱ ዘወትር እንደ ተጣበበ ነው።

በዚህ ሥፍራ ከአውሮፓ፣ ከኢሽያ ከአፍሪካና ከሌላም ልዩ ልዩ ሀገሮች የመጡ ሰዎች ሠፍረው ከጀርመኖች ጋር በመሆን (Melticultüral) የሆነ የባህል ትርኢቶችና ልዩ ልዩ ምግቦች ተሰናድቶ ይቀርብበታል። በዚህ ምክንያትና በሌላም ጭምር አካባቢው 24 ሰዓት በሕዝብ ተሞልቶና ደምቆ ይታያል።

ሀገር የሚጐበኝ ቱሪስት፣ በስደት የሚኖር እንግዳ፣ የአሽሽ የሌላም እፅ ነጋዴ፣ ሥራ ፈትና ቁጩር፣ ሌባና ጃንኪ፣ ወሮበላና ዱራዳሪ፣ ነጭ ለባሽና ባለመለዮ ፖሊስ ተደበላልቀው ከወዲህ ወዲያ ይተላለፉበታል። የአንዙላንስ የመኪናዎች ጥሩንባ፣ የዳንስ ቤቶች የሙዚቃ ጥለዛ፣ የሕዝቡ ሁካታና ጩኸት ተደባልቆ ዘወትር የሚሰማበት ግርግርና ሽብር የሚታይበት መንደር የብሬመን ቀበሌ የድንጋይ በር ይህን የመሰለ መልክ አለው።

ሽታይንቶር ይህ የድንጋይ በር ቀበሌ እንደ ስሙ ሆኖ እንደ ሐረሩ መጋላ በር ዙሪያው በግንብ ታጥሮ ቀስተ ዳመና የሚመስል ትልቅ በር በአካባቢው ጨርሶ የለም። በእርግጥ የዘረፈ መሸሸጊያ፣ ላለው ትልቅ መዝናኛ ለሌላው መቀመጫ፣ ለሚባልግ የሴተኛ አዳሪዎች መዳሪያ፣

ደስ ላለው መደነሻ፣ ላዘነው መተከዣ ሌላም ብዙ የንግድ መነሻሪያ ግል ጹና ስውር በሮች አሉት።

ሽታይን ቶር ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የንግድ መደብሮች አሉበት። በተለይ የባህል ቅይጥ ምግቦች ከየሀገሩ ይቀርብበታል።

ሂፓክራትስ፣ ታንቶር፣ ቶሮስ ክስሜት ኤዳና ታኬ የሚባሉ ምግብ ቤቶች ቀን ከለሊት አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። የግሪክ፣ የቱርክ፣ የአረብና የኢራን፣ የጀርመንና የሩቅ ምሥራቅ ሀገሮች ወዘተ. ልዩ ልዩ ምግቦች በደንብ ተዘጋጅተው ይቀርባሉ።

ግሪኮች ይህን የመሰለ የሥጋ ክምር ልቃቂት ስሙን ጅሮስ ብለው የዚህንም የምግብ አሠራር ጥበብ ለዓለም ያስተዋወቅነው እኛ ነን ብለው ይመካሉ፣ እሮኬት የሠሩ ይመስል።

ቱርኮችም የዚህን የሥጋ አሠራር ስም ዱነር በማለት ጥበቡን ከግሪኮች በፊት እንደ ጀመሩት ይናገራሉ። ያም ሆነ ይህ ጅሮስ የተባለውን የሥጋ ሙልሙል ጥበብ ለብሬመን ከተማ በመጀመሪያ ያስተዋወቁት የሂፓራትስ ምግብ ቤት ባለቤት አቶ Ali Papoutsalakis የሚባሉ ግሪካዊ ዜጋ ናቸው። በዚህ ሥራ ብሬመን ውስጥ ከ35 ዓመታት በፊት ጀምረው አሁንም ይህንኑ ሥራ ስለሚሠሩ "The King of Giros" የሚባል ስም አትርፈዋል።

አቶ Ali Papoutsalakis በዚህ ስም ከመጠራታቸው ሌላ፣ በቀለም ልዩነት የማያምኑ፣ የሰው ልጅን እኩልነት የተገነዘቡ ብልህ ሰው በሆናቸው፣ ጥቁሮችን ቀጥረው በኃላፊነት ሥራ በድርጅታቸው ውስጥ ያሠራሉ።

ታዲያ ይሄ የምግብ የጥበብ ሥራ ውጤት የሆነው ጅሮስ ሲያዩት ለጠገበ ተመልካች ወስፋት ይዘጋል። ጥቂት ሲቀምሱት ግን አፍ ውሃ ሞልቶ እያስጎመጀ ጣፍጦ ብሉኝ ብሉኝ ይላል።

ሄለን የተባለው ዝግ ችሎት ጉዳና በቀያይ መብራቶች ያሸበረቀ የሴተኛ አዳሪዎች መናኸሪያ በሕግ የተፈቀደ ቦታ ነው። ሴቶቹ ለዚህ ሥራቸው ለመንግሥት ቀረጥ ይከፍላሉ። መንግሥት ደግሞ በየጊዜው ጤናቸውን እየመረመረ ፍቃድ ይሰጣል። ያካባቢውን ጸጥታ በፖሊስ ያስጠብቃል። በዚህ ስፍራ ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላ ወጣቶች እንዳይገቡ ይከለክላል።

ታዲያ በዚህ ስፍራ የተለያዩ ዜጐች፣ ቆንጆም ይሁኑ ፉንጋ፣ ሴቶች ሁሉ በቡታንቲና በጡት መያዣያ ብቻ እራቁታቸውን ሆነው በየበርና መስኮታቸው ተኮልኩለው ለወሲብ ጨዋታ፣ ለጊዜያዊ ደስታ የሚሸጡበት የብልግና መናኸሪያ ጥንቃቄም ካልተወሰደ የበሽታ መተላለፊያ ልዩ ሥፍራ ሊሆን ይችላል።

ቆንጆ ሚስቱን እቤቱ አስቀምጦ ሌላዋን በወረት የሚከጅል፣ ብቸኛ ወንደላጤ የተፈጥሮ አምሮቱን የሚወጣበት፣ ከአገር ሀገር የሚዘዋወር ቱሪስት ወይም በቅርቡ ከአፍሪካና ከሌላም ሀገር የመጣ ስደተኛ ገንዘቡን ከስክሶ ፍላጐቱ ሳይደርስ ወይም ደርሶ እንደ ነገሩ ተልከስክሶ ወይም በሥርዓት ተዝናንቶ የወሲብ ጥማቱን የሚያረካበት ቦታ ነው።

ፈርፈልድ Fehrfeld የሚባለው ሌላው የታክሲዎች መቆሚያ ነው። ቀምቶ የሚሸሽ፣ ሰክሮ የሚመጣ፣ የደከመ ወይም የበረታ የተለያዩ ተሳፋሪዎች እንደ ልብ የሚገኙበት ሥፍራ ነው። በዚህም ብዙ ታክሲዎች ቀን ከሌሊት ሳይሉ በተራ ተራቸው ተሰልፈውና ተኮልኩለው ይታዩበታል። አንዱ ሲሄድ አንዱ እየተተካ ሌላው ተሳፋሪን ወስዶ ተመልሶ እየመጣ ይቆምበታል።

ሮዚም ሆነች ክላውዝ ጀኒም ሆነ ፋጡማ ሙራትም ይሁን ሌሎች ታክሲ ነጂዎች ይህን ቦታ አዘውትረው ይመጡበታል። ቡና ለመጠጣት ሆነ ምግብ ለመብላት እርስ በእርሳቸው የሚገናኙበት ቦታ ግቢ ክስሜት የሚባል ፈጣን ሬስቶራንት ነው።

የክስሜት የበሬ ሥጋ ዝልዝል በሚሽከረከር ምድጃ (ግሪል) ላይ ሆኖ በቅመም ተለውሶ በስስ በስሱ የተቆረጠው ስጋ ቡትክክል ተለጣጥፎ ሲያዩት ልክ በትልቁ የተፈተለ ልቃቂት መስሏል። ከግራና ከቀኝ የሚጠብሰው የኤሌትሪክ ወይም የጋዝ ወላፈን ክምር ሥጋውን ለብልቦ አብስሎታል። ጭፍ ጭፍ የሚል ቅባት ያዘለ ላቦት ከሚሰጡ እየነሰረ ወደታች ይወርዳል። ሠራተኛው የበሰለ የበሰለውን በትልቅ ጐራዴ መሰል ቢላዋ በስስ በስሱ በብልሃት አስተካክሎ ሲቆርጠው እንደ ሕፃን ልጅ ለቅሶ ያነፈርቃል። የቅባት እንባውን ያነባል።

ይህን የመሰለ የሥጋ ልቃቂት ጥብስ ግሪኮች ጅሮስ ሲሉት ቱርኮች ደግሞ ጹነር ይሉታል። ሲያዩት ለጠገበ ተመልካች ወስፋት ይዘጋል። ለራበው ግን አፍ ውሃ ሞልቶ ያስጉመጃል።

ከዚህም ሌላ በዚሁ ሰፈር አካባቢ፣ በየመስኩቱ መደዳ ተዘጋጅተው ለሕዝብ እንደላንቲካ የሚታዩ ልዩ ልዩ ምግቦች ከሥር የፈላ ውሃ ከላይ ትኩስ መረቅ እየተጋቱ መንገደኛውን ያስጉመጃሉ። የጥብሱ ሽታ የምግቡ ቃና እየተነነ በመስኩት በመውጣት ያለውዴታ በግድ ያስርባል።

መቼም ይህን የላንቲካ የምግብ ትርኢት አንድ ከአዲስ አበባ የመጣ ገጠሬ ቢያይ ሳይገረም አይቀርም። በሃሳቡ «የስንቱ ዓይን ያረፈበትንና ያፈጠጠበትን ምግብ መብላት ለጤናም አይበጅ» ማለቱ ምናልባት የማይቀር ነው። ይህም ባይሆን «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» እንዲሉ ሆኖ የጠራማ ክርስቲያን ከሆነ ማን እንደ ባረከው ሳያውቅ ንክችም አያደርጋት። ቢነገረውም እንኳን ምግቡ ከአሳማና ከሌላ ነገር የተነካካ ስለሚመስለው በቀላሉ አይቋደስም። ጠኔና እርሃቡን ከማተቡ ጋር እንደሉጋም አጥብቆ ይዞ ይሞታል እንጂ።

በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳንዱ የተራበው እህል ጠፍቶ ሳይሆን ይህን በመሳሰለ ልማዳዊና ሃይማኖታዊ ባህል መሆኑ ጥርጥር የለውም።

ሌላው የምግብ መሸጫ ሱቅ ደግሞ የዶሮ ነው። እንደ ሀገር ቤት ደንብ ብልታቸው ሳይወራረድ መላላጫ ፈረሰኛ አጭሬና ወዘተ. ተብሎ በወጉ ሳይቆራረጥ ሙሉ ድፍን ዶሮዎች በደንብ ታጥበውና በቅመም ተለውሰው በማንቁርታቸው የብረት ዘንግ ገብቶ እርስ በእርሳቸው ተሰካክተው በሄንጂን ግሪል እየተሽከረከሩ በኤሌክትሪክ እሳት ይጠበሳሉ።

የራበው መንገደኛ ግማሽ ወይም ሙሉ ዶሮ አዞ በቢላዋ ወይንም በእጁ እየገነጣጠለ ስንት ቤተሰብ አጥግቦ የሚመልሰውን ሙሉ ዶሮ ብቻውን እየገሸለጠ ቆረጣጥሞ ይጨርሳል።

በሌላ የሥጋ መጥበሻ ግሪል ደግሞ ክራካዋ ብራት ቮረስት በክ ቮረስት የሚባሉ የጀርመን አንዱ የባህል ምግባቸው ነው። አዲስ የመጡ

የሀገራችን ሴቶች ቢርባቸውም «ያን ነገር ይመስላል» እያሉ ጨርሶ አይነካኩትም። በአርግጥም ሲታዩ ትንሽ ቆልመም ብለው የሙዝ ቅርጽ አላቸው። ሮዚ ጀርመን ብትቆይም ይህን የመሰለ ምግብ ንክችም አርጋው አታውቅም። የድንጋይ በር የምግብ ነጋዴዎች ግን በሺ የሚቆጠር ቩረስቶችን በየእለቱ ጠብሰውና ቀቅለው ለሌላ ተመጋቢ ወስፋቱን በባህልና በሌላ ሳቢያ ለማይገታው ሸጠው ይጨርሳሉ።

በዚህ አካባቢ በርካታ የሆኑ የቁማር መጫወቻ ካዚናዎች አሉ። ደረቅ ሻይ እየጠጡ ሲጋራ እንደ ችቦ አቀጣጥለው እያጨሱ በሰፊ ጠረጴዛ ዙሪያ ገጥመው የካርታ ድብ ድብ፣ የጠጠር ውርወራ የዳማ አይነት ጫወታ ብዙ ገንዘብ አሲይዘው ቀን ከለሊት ሳይሉ ይቋመራሉ። ያሸነፈው ገንዘቡን ጠርጐ እየሳቀ ሲወስድ፣ የተበላው አንገቱን ደፍቶ በንዴት ጠረጴዛውን እየቧጠጠና እየመታ እድሉን አማሮ ሲተክዝ ይታያል።

በሌላ አንጻር ሽታይንቶር የሴቶች እራቁት ገላ የሚታይበት (ላይፍ ሾ) አለ። ለአንዳንድ ሰው መቆሚያ ክፍል ተሠርቶ ትርኢቱን ለማየት የፈለገ በዚህ ክፍል ውስጥ ገብቶ በትንሿ መስኮት ማዶ የምትታየውን ሴት ይመለከታል፤ ፒፕ ሾ ይሉታል። ጠባቦ ትርኢቱን ለማየት ገንዘብን በላይ በላዩ እንደ ስልክ በተቀመጠ የገንዘብ ካዝና ውስጥ መጨመር ያስፈልጋል። ገንዘቡ ካለቀ መስኮቱ አውቶማቲካሊ ይዘጋል።

ይህ ትርኢት መልካም ሥነ ምግባር የጎደለው ጋጠውጥ ተግባር ቢሆንም በንግድ አንጻር ጥሩ ገበያ አለው። በእለቱ ሁሉም ክፍሎች በወንዶች ተሞልተዋል። እውስጥ ያለችው ቆንጅዬ ሴት በተሽከርካሪ አልጋ ላይ ሆና እራቁቷን ትታያለች። ዳሌዋን እያገላበጠች በእንብርክኳ አፈንድሳ በጀርባዋ ተንጋላ እግሮቿን እየበረጋገደች ነውሯን ታሳያለች።

ተመልካቹ በሩቅ እያየ መቋመጥ ብቻ እንጂ ጨርሶ ሊደርስባት አይችልም። ንክኪነት የሌለበት የዓይን የወሲብ ሲሳይ የስሜት ማቀንዘሪያ ልዩ ስፍራ ነው።

ውስጥ ያሉት ሴቶች እየቀያየሩ ያለማቋረጥ የወሲብ ትርኢታቸውን ያሳያሉ። አሁን ተሽከርካሪው አልጋ ላይ የምትታየው ጠቆር ያለች ጠይም ቆንጅዬ ናት። ጭንና ታፋዋ መሃከል ትንሽ የበለዘ ምልክት

አለባት። ሌላው ሰውነቷ እንደመስታወት የጠራ እንደ ሳሙና የለሰለሰ ይመስላል። ቡታንቲዋን አውልቃ በጀርባዋ ተንጋላ እግሮቿን በረጋግዳ ትኩስ ትንፋሽ ተነፈሰች። ከወዲያ ወዲህ ተገለባበጠች። ተመልካች ዓይኑን ተክሎ አፈጠጠ። እሷ በሀሳብ ባሕር ተውጣ ጭልጥ ብላ ከቦታው እራቀች። ልጅነቷ አጭር በመልበሷ አባቷ ተቆጥቶ አጭር ቀሚሷን ገልቦ የቀጣትን፣ እናቷ በቁንጥጫ ዝምልግ ያደረጓትን የበለዘ ጠባሳዋ ሁሉ ያስታውሳታል። ታፋና ጭኗ ያኔ ድሮ የቅጣት መቀበያ የልጅነት ገላዋ ዛሬ የገንዘብ ማካበቻ ንብረቷ መሆኑን አሰባ ሕይወትን ታዘበች «ጭን ያለው ሀብቱን ልፋ ያለው መጁን» ብላ ተረተች። ተረቱ ግን እሷን የሚያባብል እንጂ ለሌላው እንደማይጠቅም ልቧ እያወቀ፣ «ሴላቪ» ብላ ስታ ሳይሆን ተክዛ ከወሲብ መድረኩ ተፈናጥራ ተነስታ ወጣች።

ሽታይንቶር የሽብር የግርግርና የንግድ መናኸሪያ ለአንዱ ገነት ለሌላ ሲኦል ቢሆንም የሕዝብ ብዛት ተለይቶት አያውቅም። ሁል ጊዜ የደመቀና የደራ ሳቅና ፈንጠዝያ ለቅሶና ዋይታንም ጨምሮ ስለሚታይ የኮሚዲና ትራጀዲ የድራማ መድረክ ይመስላል።

ድንገት የፖሊስ መኪናዎች ሰማያዊ መብራታቸውን ብልጭ ድርግም እያደረጉ፣ በነጭ የተሸለመ አረንጓዴ መኪናቸውን እየሰገሩ የዋይ ዋይታ ጩኸታቸውን እያቧረቁ መጡ። ሕዝቡ የሆነውን ለማየት ጓጓ እንጂ በጩኸቱ እንብዛም አልበረገገም ዘወትር የሚሰማው በመሆኑ ለምዶታል።

እንደ ወትሮ የተፈነካከተ ወይም ሰክሮ የተዘረፈ ሰው በሰፍራው አልነበረም። አንዲት ጀርመናዊት ወጣት ሴት የሆነ መጠጥ ቤት የሴቶች ሽንት ቤት ገብታ ከመጠን በላይ ሄሮይን የሚባለውን አደንዛዥ እፅ ተወግታ ሞታ በመገኘቷ ብቻ ነበር። ይህም ፖሊሶችንም ሆነ የአካባቢውን ሕዝብ አላስደነገጠም። አንቡላንስ ተጠርቶ አሱም እያቋጨ መጣ። ምስኪኗ ሟች በቃሬዛ የሳንሳ ተይዛ አንቡላንስ ውስጥ ገብታ ወደ ሆስፒታል ተወሰደች። ፖሊሶችም ወዲያው ተበታተኑ።

አንዱ ሰካራም «በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ» እንደሚባለው «እነዚህ ከአፍሪካ ተጠረቃቅመው የመጡ ጥቁሮችን ከዚህ ካላስወጣን ልጆቻችን

ማለቃቸው ነው! በስደት ስም እዚህ እየመጡ ይህን መርዛማ እፅ የሚሸጡት እነሱ ናቸው ከአገራችን ከስፍራችን ይውጡልን» ብሎ በተጐላደፈ ድምፅ ጮኸ። አጠገቡ የቆመ ደንደሳም ጥቁር መንጋጭላውን በቦክስ አጠዘው። መሬት ወድቆ ተንከባለለ። ጥቁሩ ሮጦ አመለጠ። ሌላ አንቡላንስ ተጠርቶ እየጮኸ መጣ።

ለሊቱ ተጋምሶ የሽታይንቶር ሁካታና ጩኸት ትንሽ በረድረድ እያለ መጣ። የታክሲዎች ግር ግር ከወዲያ ወዲህ ውር ውር ማለት፣ ሰው ጭኖ መፈርጠጥ ወይም ሌላውን አምጥቶ ማድረስ፣ በሂሳብ ክፍያ ተጨቃጭቆ ወይም ተግባብቶ መለያየት አበቃ።

ሮዚና ጆኒ መኪናቸውን አቁመው ለእረፍት ኪስሜት ከሚባለው ፈጣን ምግብ ቤት ገቡ። የምግብ አዳራሹ እንደ ወትሮው አልሞላም። ገና ሲገቡ ግን የምግቡ ሽታ ያውዳል። ማዶ ሰፊው ጠረጴዛ ላይ ሌሎች ታክሲ ነጅዎች ማለት ሙራት አንድሪያስና ፋጡማ ተቀምጠው እርስ በእርሳቸው እያወጉ የቀረበላቸውን ምግብ ይመገባሉ።

ሮዚና ጆኒ ገብተው የሥራ ባልደረቦቻቸውን በሩቁ በእጅ ውዝዋዜ ሰላምታ ተለዋውጠው ለብቻ ሌላ ቦታ ይዘው ተቀመጡ። የምግብ ቤቱ አስተናጋጅ አጭር ወፍራም ፊቱ ሞላላ ነው። ነጋሪት ሆዱን ዘርጥጦ እየተቁለጨለጨ በፈገግታ ዱጭ ዱጭ እያለ ሊታዘዝ መጣ። ሌላ ገበያተኛም ቢኖረው ሮዚ ከመጣች ቶሎ ብሎ ለእሷ የመታዘዝ ግዴታ አለው። ሮዚ በሆዷ እንደሚፈልጋት ጠርጥራ «ልብ እንቅርት ይመኛል» ብላ ለእሷ ኮትሌትና ሻሽሌክ ለጆኒ የበግ ጥብስና ሰላጣ አዘዘች። ምግብ እስኪመጣ ሲጃራዋን ለኩሳ ጭሱን ወደ ላይ እያቦነነች ለንግግር መጀመሪያ ብላ ጆኒን «ገበያ እንዴት ነው?» ብላ ጠየቀች።

«ደህና ነው።»

«እስካሁን ስንት ሠራህ?»

«እንጃ አላወቅሁትም በግምት 300 ይሆናል አንቺስ?»

«በእርግጥ ካንተ ይበልጣል። ሥራ ከጀመርኩ ምንም ፋታ አላገኘሁ በዚህ ላይ ጉርሻው ይገርመሃል አይነሳ ጆኒ።»

«ታድለሽ እንግዲህ የዛሬውን እራት ግብግ ማለቴ ክፍያ ያንቺ ነው ልበል?»

«መጠርጠሩሳ የኔ ነው ጋብዤህ አይደለም አብረን የመጣነው።»

«አመሰግናለሁ ዛሬ ከላውዝ አይሠራም እንዴ?»

«እንግዲህ ጀመረህ ገና ሳልበላ አትልከፈኝ። ምስት ቀን ብቻ እንደሚሠራ ታውቃለህ ለምን ስለ እሱ ትጠይቀኛለህ?» አመሏን ስለሚያውቅ ጆኒ ለምን ብሎም አልጠየቃትም።

ምግቡ ቀርቦላቸው መብላት ጀመሩ። ማዶ ካሉት ታክሲ ነጂዎች ውስጥ ሙራት የቀረበለትን ምግብ መብላት አልቻለም። አይኖቹ እሮዚ ላይ ተተክለው ፈዘዋል። ሮዚ ለእሱ ጉዳይም አላለችው። ቀደም ሲል ያኔ በአፍላው አብረው ነበር የሚመገቡት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ባልታወቀ ምክንያት ችላ ስላለችው ምናልባት በዚሁ ምክንያት አዝኖ ሊሆን ይችላል። ሮዚ «ብላ እንጂ ጆኒ የምን ቆንጠር ቆንጠር ነው» ብላ ከራሷ አንድ ኮትሌት አንስታ እሱ ሰሃን ላይ አስቀመጠች።

ጆኒ «የራሴን ፋንታ ሳልጨርስ እባክሽ አትጨምሪብኝ» እንዳውም የኔ ጥብስ በጣም ይጣፍጣል ቅመሽው» ብሎ በሹካ የጥብሶቹን ሥጋ ወጋግቶ አጉረሳት። በቀስታ አላምጣ ከጉረሰች በኋላ «እውነትምያንተ ይጣፍጣል» ብላ የራሷን ምግብ ትታ እጇን በማዘለል በሹካ አንድ ሁለት ወሳሰደችለት። «ይሄኛውን ደግሞ ቅመሰው» ብላ ከሻሽሌኩ ሥጋ በሹካ አጣብቃ ለጆኒ አጉረሰችው። አሳላፊው ዶጮ ሮዚን በዓይኑ እየቀላወጠ የተረፈውን ምግብ አንስቶ ሳይታዘዝ ሁለት ብርጭቆ ሻይ ይዞ መጣና አቶ ሙራት ነው የጋበዛችሁ ብሎ አስቀመጠው። ሮዚ እንብዛም ደስ አላላትም። ሲጃራዋን በድጋሚ ለኩሳ የምትለው ብታጣ ጆኒን ተጫወት እንጂ» አለችው «እዛ ከነሱ ጋ ሄደን ብንጫወት ይሻላል» ብሎ ሻያቸውን ይዘው ወንበራቸውን አጠጋግተው ሌሎች ታክሲ ነጂዎች ያሉበት ቦታ አብረው ተሰብስበው ተቀመጡ። ጆኒ ፋጡማን ስለሚወዳት አብሮ መቀመጥ ወደደ። ሙራት ሮዚ በመቅረቧ ልቡ ጮቤ አረገጠ። ደስ ብሎት በተስፋ ተቁነጠነጠ። ጆኒ ስለሻዩው ግብግ አመስግኖ ሌላ

ወሬ ቀጠሉ። መቼም ታክሲ ነጂዎች ሲገናኙ የሚያወሩት ያው ስለእለት ገቢያቸው ወይም በእለቱ ስላጋጠሟቸው የተሳፋሪዎቻቸው ሁኔታ እንጂ ስለ ፖለቲካ፣ ባሕል ወይም ኪነት ጨርሶ ንክችም አያደርጓት። ሀሜት ግን እንጀራቸው ነው። አንዱን ዘርጥጦ ሌላውን ክቦ ማውራት። በአጠቃላይ የዓለም ታክሲ ነጂዎች አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር እንደ ሥራ ቤት ይሄው አሉባልታና ሀሜት የቆጥ የባሱን ቀበጣጥሮ እርስ በእርስ መሳሳቅ በትንሽና በትልቁ ተኮራርፎ መጨቃጨቅና መጣላት፤ ወይም ያደረጉትን ትንሽ ብልጥነት እንደዝያ ማውራት ይሆናል። ብዙዎቹ ትምህርት ጨርሰው በሙያቸው ሥራ ያጡ ጥቂቶቹ ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ የሚገኙ ቢሆንም ገና የታክሲ መሪ ሲጨብጡ «ከአህያ የዋለች ጊደር» ሆኖባቸው ይሁን አሉባልታን ሥራዬ ብለው መሰለቅ ይጀምራሉ።

እንድሪያስ እድሜው በ30 የሚገመት ጀርመናዊ ለግላጋ ወጣት ታክሲ ነጂ ነው «ትላንት የሆነውን ላጫውታችሁ» ብሎ ወሬ ጀመረ «ከሆነ ቦታ መጠጥ ቤት አንድ ሴትና ወንድ ተሳፋሪዎች አሳፈርኩ ሁለቱም ተያይዘው ኋላ ወንበር ተቀመጡ ትንሽ ሞቅ ብሏቸዋል። አብረው ለፍልፈው ተቃቀፉ። በኋላ ግሩፕሊንገን ብለውኝ ይዣቸው ሄድኩ። ቦታው ሲደርሱ ሴትየዋ አልወርድም ብላ መኪና ውስጥ ቀረች። ሰውየው ቢለምን ቢለማመጥ ተናዶ ቢቦርቅ ሴቲቱ ወይ ፍንክች። ፖሊስ እጠራለሁ ብዬ ስናገር ሰውዬው ፈርቶ ገንዘቡን ከፍሎ ሴትየዋን ትቶ ሄደ።

ታክሲው ውስጥ የቀረችው ሴት ሲያዩዋት ደስ የምትል ደርባባ ወይዘሮ ነች። «ከፈቀድክልኝ እፊት ልቀመጥ» ብላ ቦታ ቀየረች። የሆነ ጠረን ቢሸተኝም። «የት ልውሰድዎ» ብዬ በአክብሮት ጠየቅሁ። «የፈለግህበት አንተ ደስ ያለህ ቦታ። ዛሬ መዝናናት አሰኝቶኛል» አለችኝ «ምን ዓይነት መዝናናት?» ስላት ታፋዬን ጨበጥ አድርጋ «ይቅርታ» አለችኝ። በሚጣፍጥ ቃና ግራ ተጋባሁ። «ከሰውዬው ጋር ለምን አልወረዱም?» አልኳት «እርሶታውን ትተህ አንቺ በለኝ ብወፍር ያረጀሁ መስሎህ ነው? ገና ወጣት ልጅ ነኝ» ብላ ከት ብላ አስካካች። ፊቷ ቢያምርም አፏ ጋን ጋን ይላል። ይቅርታ ብላ እንደ ገና ታፋዬን

ጨበጥ አርጋ ያዘችው። ሰውነቴን የሆነ ነገር ወረረኝ። ያንንም ነገር ዳበስ፣ ዳበስ፣ ስታደርግ ስሜቴ ቋመጠ ሰውነቴ ሞቀ። ሮዚ እንዲህ ያለ ወሬ በይፋ ሲወራ መስማት ያሳፍራታል። «እባክህ አርእስት ቀይረህ ሌላ ነገር እናውራበት» አለችው በልቧ ግን የነገሩን መጨረሻ ለማወቅ እየከጀለች። አንድሪያስ «አኬ ካልፈለጋችሁ ተውት» ብሎ ቡናውን ተጐነጨ። ጆኒ «እንስማው ምን የሚያሳፍር ጉዳይ አለበት» ብሎ አስተያየት ሰጠ። ሙራት እሮዚን እየተመለከተ ተክዟል። አንድሪያስ ሲጃራውን ለኩሶ ወሬውን ቀጠለ።

«ምን ላይ ነበርኩ?» ብሎ ትንሽ ካሰላሰለ በኋላ መልሶ አስታወሰ «አዎ ሴትየዋ ገንዘብ ይጐለሁ የሆነ ቡና ቤት ሄደን አብረን እንጫወት» አለችኝ። ምን ችገረኝ ብዬ ጆይ ከሚባለው ቡና ቤት ይዣት ሄድኩኝ። ወደመንጋቱ አካባቢ ስለ ነበር ቡና ቤቱ ጭር ብሏል። ለእሷ ኮኛክ ለኔ ቡና አዛ አብረን እየተጨዋወትን ትንሽ ቆየን። ታክሲው ቆሞ ሂሳቡ ይቆጥራል። እሷ ኮኛኳን በላይ በላይ እየደጋገመች ጠጣች። በኋላ መዘባነንና መጨመላለቅ ስትጀምር መልሳ አስጠላችኝ። «የታክሲውን ሂሳብ ክፈይና መኪናዬን አስረክቤ በግሌ መኪና ተመልሼ እመጣለሁ» አልኳት መቶ ዶች ማርክ አውጥታ ሰጠችኝ ተመልሼ አልሄድኩም።

ሙራት ሚስት ቢኖረውም ይህ ሁኔታ ቢያጋጥመው የትም ወስዶ እንደሚዳራት በልቡ አሰበ። ለእንደዚህ አይነት ሴት ጊዜ መስጠት አያስፈልግም ብሎ አለ። ጆኒም ቢሆን እንደሚያደርገው ጥርጥር የለውም። ግን በሞኝ ፊቱ ሁሉንም አላላቸው። የታክሲ ነጅዎች ከሚያገኙት የገንዘብ ጉርሻና ሂሳብ አንዱ በረከት እንዲህ ያለው አጋጣሚ ነው። የሴት ሹፌሮችም ምሰጢራቸውን ይደባብቁ እንጂ አንዳንድ ሃብታም የሆኑ ቱጃሮች ገንዘባቸውን ተገን በማድረግ ለመዳራት መከጀላቸው ያለ እውነት ነው። የእረፍት ጊዜያቸው አልቆ ብዙዎቹ ታክሲ ነጅዎች ለሚቀጥለው የለሊት ንጋት ሥራ በመጣደፍ ሂሳባቸውን ከፍለው ከምግብ ቤቱ ወጡ። ሙራት ግን ብቻውን ቀረ።

ሙራት እድሜው ከ55 የሚበልጥ ባለ ትዳር የሁለት ልጆች አባት ነው ሙራት ሁሴን ትውልዱ ቱርክ ብዙ ዘመን ጀርመን ውስጥ የኖረ፣

በትምህርቱ ያልገፋ፣ በዚሁ በታክሲ ሹፌርነቱ ለረዥም ጊዜ ያገለገለ አውንም በዚሁ ሙያ የሚሠራ ሰው ነው። ቁመቱ አጠር ብሎ ሰውነቱ ቀጠን ያለ ሰው ነው። የራሱ ፀጉሮች ብን ብለው ያለቁ በራማ ፀጉሮች በግንባሩ ላይ በስሱ በቅለው ግንባሩንብ ሸፍነውታል። በሩቅ ሲያዩት የተዘቀዘቀ ትልቅ ቅል አንኮላ ይመስላል። ገራገርና ተለማማጭ ሰላምተኛና ቅን ጠባዮች አሉት። ሲሄድ እረጋ ብሎ መራመድ አይችልም። ኩስ ኩስ ወይም እንደ ሕፃን ልጅ ድክ ድክ ማለት ያበዛል። በተለይ የሴት ተሳፋሪዎች ሲያጋጥሙት ከመጠን በላይ ይጨነቃል። ይርበተበታል። በር ከፍቶ ያስገባል ይቅበጠበጣል ሰላምታና ትህትና ያበዛል። በዚህም ብዙ ሴቶች ይወዱታል። ታክሲው ውስጥ ብስኩት ከረሜላ ወይም ሌላ ፍራ ፍሬ አይታጣም። መብላት ለፈለገ ተሳፋሪ አቅርቦ ይጋብዛል። የረዥም ጊዜ አገልግሎትና ጥሩ ጠባይ ስላለው የሚነዳው ታክሲ ኤስ ክላስ ማርቼዲስ ነው። ኤር ኮንዲሽኑ የተሟላ ድሎትና የውስጥ ስልክ ያለበት ሰፊ ትልቅ መኪና ነው። እሱ ግን እውስጥ ሲታይ ብርሌ ውስጥ የገባች አተር ይመስላል።

በእርግጥ ሙራት ሁሴን አይጠጣም። አያጨስም። ያው ያለው ደካማ ጐን ቢኖር ቅንዝረኛነቱ ብቻ ነው። የሴት ነገር አይሆንለትም። ባለትዳር ቢሆንም ሴት ካየ መቅበጥበጡ አይቀርም። ያቺንም ያቺንም ይመኛል። ከቀናውም ያረጋል። በተለይ ሴቶች ከመኪናው ወንበር ፈንደስ ብለው ሲወጡ ዓይኑ የሚያርፈው እዛው ዳሌና መቀመጫቸው ላይ ነው። ሲጫወትና ሲቀልድ ያምርበታል። ጥርሶቹ ክርክም ብለው የተሠሩ የተላጠ የበቆሎ እሸት ይመስላሉ ሲስቅ የደስ ደስ አለው። በዚህም ከሌሎች ታክሲ ነጅዎች ጥሩ አግባብ አለው። ሌሎችን መስሎ ለመታየት ድምፅና ገፅታውን መለዋወጥ የሚችል ጥሩ አክተር ነው። አተኩረው ሲያዩት ግን ውስጡ ተንኮልና ሸር ቅናትና ምቀኝነት ያለበት ይመስላል። በእለት ገቢ ሌሎች ሲበልጡት ጥርሱን ነክሶ ይናደዳል። ሌላው ታክሲ ነጂ አንዷን ካወጣ በከንቱ ይቀናል። ዓይኖቹ ደም ስለሚመስሉ ያለው የአክተርነት ችሎታው ይህን ጉዳይ ሊሸፍኑለት አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ይቀያየም እንጂ ቂም አይዝም። መልሶ የተጣላውን ሰው ተለማምጦ መታረቅ ይችልበታል። ባይማርም ጥሩ የዲፕሎማሲ ችሎታ አለው።

ሮዚ ገና የታክሲ ሥራ መሥራት እንደ ጀመረች ከጆኒ ቀጥሎ የሥራውን ዓይነት በምክር አስረድቶ ያለማመዳት እሱ ነው። በዚህም ውለታው ይሁን በተጫዋችነቱ ሮዚም አባቷን ቢያክልም እንደ ወንድም አቅርባ በማየት ወደደችው። አብዛኛውን ጊዜ ለእረፍት እራት የሚበሉትም አብሮ መሆን ጀመረ። በዚሁ እየቀጠለ አንድ ዓመት አብረው አሳለፉ። ሙራት ያው ባለው የአክተርነት ችሎታ የሀገሩን ባሕል ልዩ ልዩ ቀልዶችና ጫወታዎች እያወጋ ዘወትር ያስቃታል። ሮዚ «ሙራት የዋህ ሰው ነው» ብላ ይበልጥ ወደደችው። እቤቷም ምግብ አዘጋጅታ ጋበዘችው። አብረው ይቀልዱ፣ አብረው እራት ይብሉ እንጂ የመዋደድ ፍቅራቸው ከወንድምና እህት ደረጃ አላለፈም።

ሙራት ግን ያው ያለበት ደካማ ጐን ስላየለበት ሁኔታውን በዚህ ዓይነት ግንኙነት ሊቋቋመው አልቻለም። አፍ አውጥቶ ደፍሮ አይጠይቃት እንጂ በልቡ ሮዚን በጣም ያፈቅራታል የሱ እንድትሆን ዘወትር በሕልሙም በውኑም ይመኛታል። የሙራት ሁኔታና መለዋወጥ ሮዚ እያደር ገባት። ከዚህ ወጥመድ በዘዴ ለማምለጥ ፈልጋ «ለምን ባለቤትህን ልጆችህን አታስተዋውቀኝም» ብላ ጠየቀችው። ሙራት ያልታሰበ ዱብ እዳ ወደቀበት። እንቢ ሊል አይችልም። የሆነ ቀን ትልቅ እራት ቤቱ ተዘጋጅቶ ተጋበዘች። ከሚስቱና ከልጆቹ ተዋወቀች። ልጆቹ የሚጫወቱበት አሻንጉሊቶች ቀጭኔ ዝሆንና ጥቁር መልክ ያላት የሴት አሻንጉሊት ናቸው። ሮዚን ለማስደሰት አውቆ የተደረገ መሆኑን ገምታ የጠየቀችው ጥያቄ አልነበረም። ሁኔታውን ያልወደደችው የሙራት ሚስት ባሏ ያዘዛትን አድርጋ ጥቁር እንግዳዋን በጥሩ ሁኔታ አስተናገደች።

እንዲህ ያለ የቤተሰብ መቀራረብ ቢኖርም አሁንም የሙራት ስሜት አልተለወጠም። እንዳውም ይባስ ብሎ አልፎ አልፎ ጥቁር ሴቶች ያሉበትን የፓርኖ ሥዕል ከሆነ የማስታወቂያ ፎቶ ጋር እየደባለቀ ማሳየት ጀመረ። ሮዚ በልቧ «ቀላል ሽማግሌ ወራዳ የሰው ወራዳ ቅሌታም እስላም» ብላ ተሳድባ በቁጣ ቃል «ሁለተኛ እንዲህ ያለውን የብልግና ፎቶ እንዳታሳየኝ ከፈለግህ ወስደህ እዛ አቤት ለተወዘፈችው ሚስትህ አሳያት» ብላ ጮኸችበት።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሙራትና የሮዚ ግንኙነት እየላላ ሄደ። አብሮ እራት መብላት ቀረ። ሰላምታቸው የአንገት በላይ ብቻ ሆነ። ሙራት መልሶ ለመታረቅ አቆበቆበ። ጆኒንም ፋጡማንም አማላጅ ልኮ አልተሳካም። እራሱም መሳሳቱን አምኖ እጅ ነስቶ ተንበርክኮ ይቅርታ ጠየቀ አልሆነም።

ቁራን አምጥቶ ሁለተኛ ስህተቱን አልደግምም ብሎ ምሎ ተገዘተ። ሮዚ «ከእግዚአብሔር ሰላምታ በስተቀር እኔና አንተን የሚያገናኘን ነገር የለም።» ብላ ዘጋችው።

ይህ ሁኔታ በቅርቡ የተፈጠረ በመሆኑ ሙራት እንደ ቀድሞው ደስተኛና ተጫዋች መሆኑ ቀረ። ሀዘንና ትካዜ ወረሩት። የክላውዝም ሮዚን መያዝ ተጨምሮ ልቡን የቅናት መርዝ ነደፈው። በቅጡ መሥራት ቀርቶ ምግብ በስነ ሥርዓት መብላት አቃተው። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል ሌሎች ታክሲ ነጂዎች እራታቸውን በልተው ተመልሰው ወደ ሥራ ሲሰማሩ እሱ ብቻውን በሀዘን ተውጦ የቀረው። ማን ያውቃል አይ ሙራት ምስኪኑ።

ጆኒ ከምግብ ቤት እንደ ወጣ መኪናውን ይዞ እዛው አካባቢ ከሚገኘው ሞሜንት (Moment) ከሚባለው ዲስኮቴክ በራፍ ላይ ገተራት።

ሮዚ እሷም ከዛ ሳትርቅ ፈርፈልድ (Fehrfeld) ከሚባለው የታክሲዎች ማቆሚያ ቦታ መኪናዋን አሳልፋ ሲጃራዋን እያቦነነች ጠበቀች።

ፋጡማና እንድሪያስ በተለያየ አቅጣጫ መኪናቸውን ይዘው ከሽታይንቶር መንደር እርቀው ተፈተለኩ።

ሰዓቱ ሊነጋጋ ተቃርቧል። የሳምንቱ መጨረሻ ቢሆንም አብዛኛውን ሰው በዚህ ሰአት ከመጠጥ ቤትም ሆነ ከዲስኮቴክ ደካክሞ እየወጣ ወደ ቤቱ የሚሄድበት ወቅት ነበር። ቅድም እርጭ ዝም ፀጥ ያለው የሽታይንቶር መንደር መልሶ ደመቅ ደመቅመቅ ማለት ጀመረ። ታክሲዎች ሲሽከረከሩ ሰካራሞች ሲጮሁ ወፎች ሲንጫጩና የከተማ ባቡር ሲዘዥር ሁሉም ሥራቸውን በየፊናቸው ቀጠሉ።


ጆኒ መኪናውን እጥግ አሲዞ የሰውን ብዛት አይቶ ለመገመት ዲስኩቴክ ውስጥ ገባ። እንደ ጠበቀው ያህል እንብዛም ብዙ ሰው አልነበረም። ሙዚቃው የጆሮ ከበሮ ጡንቻ የማይችለው ጩኸት ነበር ጉልቶ ይሰማል። ይደለቃል። ፈንክ ሶል ቴክኖ ወዘተ. ሽክላና ሲዲው እየተቀያየሩ ይሰማሉ። ጆሮን አልፎ ልብ የሚነዝርና የሚነርት የሙዚቃ ምት ቀለም ያላቸው ልዩ ልዩ መብራቶች እንደ ሰማይ ኳክብት ያብረቀርቃሉ። የዲስኮ ነጭ ፓውዛ ብልጭልጭ እያለ ዓይን ያጭበረብራል። አዳራሹ በሲጃራ ጭስና በሴቶች የተለያየ ሽቶ ታውዷል። የመደነሻ መድረኩ በጥቂት ዳንሴሪዎች ተይዟል። ትከሻቸው ንፋስ እንደ መታው ዛፍ ቅጠል እየተርገበገበና...እየተንዘፈዘፈ ይጨፍራሉ። እንደ አዶከብሬ ጉንበስ ቀና ይላሉ። ውቃቢ እንዳለበት ዛር ውላጅ እያጓሩ ይውረገረጋሉ። ጥግ ጥጉን ይዘው የተቀመጡትም ፍቅረኞች እርስ በእርሳቸው ተቃቅፈው ይሳሳማሉ። ይማጠጣሉ።

«ደከመኝ ታከተኝ የማይባልበት ያሥረሽ ምችው ቤት» ብሎ ጆኒ መኪና ውስጥ ተመልሶ ገባ። ከማዶ የወሲብ ሱቅ (Sexshope) ታየው። መብራቱ ቦግ እልም እያለ አይናችን አባብሎ ኑ ግቡ እያለ አባብሎ ይጋብዛል። የሆነ አንድ ሽማግሌ በላስኪት የተጠቀለለ ነገር ይዞ ከሱቁ ብቅ አለ። ጆኒ መኪናውን ካለበት ቦታ አስነስቶ ወደሰውየው ተጠጋ። በእርግጥም ሽማግሌው ታክሲ ፈላጊ ነበር። በር ከፍቶ አስገባው። የተጠቀለለውን እቃ ተቀብሎ የመኪናውን የጀርባ በር ከፍቶ አስቀመጠው። የላስኪት አሻንጉሊት ሥዕል፣ እንደ ፊኛ ተንፍቶ እራቁቷን ያለች ትልቅ ሴት የምትሆን አሻንጉሊት ነበረች። የሴት ችግር ያለባቸው አንዳንድ ወንዶች ይህን የመሰለ የወሲብ ፊኛ እየገዙ አብረው ከላስቲክ አሻንጉሊት ሴት ጋር ይዳራሉ። ይህን ጉዳይ ጆኒ ስለሚያውቀው በነገሩ እንብዛም አልተደነቀ።

ሽማግሌው የሚሄድበትን ቦታ ለጆኒ ነግሮት ጉዞ ቀጠሉ። ትንሽ እልፍ እንዳሉ በመሐሉ አንዲት ቀጭን ሴት በመርፌ የሚወሰድ ዕፅ ተወግታ ቀልቧን የሳተች እጆቿ (ክንዶቿ) የቆሳሰሉ መኪና ውስጥ ድንገት ጥልቅ አለች።

ጆኒ ፍሬን ይዞ አዳናት። ሽማግሌው ተነሜነጨ። «ለምን አትገጫትም ነበር? መሞቷ እንደሆን አይቀር» አታያትም ቅጥነቷንና ቁስሏን በኤድስ በሽታ የተለከፈች ኑሮ የመረራት መርዘኛ ሴት ናት።» አሉ። ቆምጨጭ ብለው። ሴት በማጣታቸው ድክመታቸውን በኤድስ በሽታ አሳበው የላስቲክ አሻንጉሊት ፊኛ በመግዛታቸው ተደስተው እራሳቸውን በማጽናናት።

ጆኒ የሽማግሌው ንጭንጭና መጣደፍ ምስኪን ሴት የመግደል ስሜትና ጭካኔ ግራ አጋባው ሰውየው ጤነኛ እንዳልሆኑ በልቡ ጠረጠረ። «መጣደፋቸው እንኳን ይሁን ምናልባት የገዟትን አሻንጉሊት አቅፎ ለመተኛት ቸኩለውና ተጣድፈው ይሆናል» ብሎ እራሱን ጠየቀ። ፍጥነቱን ጨምሮ ሽማግሌውን የተባለው ቦታ አደረሳቸው። ሂሳቡን ተቀብሎ አሻንጉሊቱን ደረታቸው ላይ በማስደገፍ አስታቀፋቸው።



የብረመን የድንጋይ በር ቀበሌ አንዱ መንደር

ጆኒ ሥራ ጨርሶ መኪናውን አቁሞ ትልቁ የባዝል አዳራሽ ገባ። ወደ 30 የሚጠጉ የታክሲ ሹፌሮች በተለያየ ቦታ ተቀምጠዋል። ብዙዎቹ ከተለያየ ሀገር የመጡ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ጀርመኖች ናቸው። ሁሉም በተለያየ ቋንቋ ስለሚ ነጋገር መደማመጥ ያስቸግራል። ጠረጴዛውን ተደግፈው የምሽት ሥራቸውን የሂሳብ ውጤት ለማወቅ ይደምራሉ ይቀንሳሉ።

የአዳራሹ ጥቂት መስኮቶች ቢከፈቱም ቤቱ በሲጃራ ጭስ ታፍኗል። የለሊቱ ሥራ በርካታ ገበያ ስለነበር የብዙዎቹ ፊት አልጨፈገገም።

ሮዚና ፋጡማ ማዶ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል። ወረቀት

ይዘው ሲጃራቸውን እየማጉ ሂሳባቸውን ያስባሉ። እንድሪያስ ሂሳቡን ሳያስብ የመኪናውን ቁልፍ አስረክቦ ቸኩሎ ወጣ። ፋጡማ እየሳቀች ያለፈውን ታሪክ አስታውሳ «ዛሀርም ሌላ ሴት አገኘህ እንዴ? ምን አስቸኮለህ» አለችው እየሳቀች። አልሰማትም።

ጆኒ እነሱ ያሉበት ቦታ ሄዶ ተቀመጠ። ሰላምታ ተለዋውጠው የለሊቱን ገበያ ተጠያይቀው ሁሉም ወደ ሂሳብ ሥራቸው አቀረቀሩ። ጆኒ «ምን ልጋብዛችሁ» ብሎ ጠየቀ። ሮዚ ፋንታ ፋጡማ ኮላ ብለውት ፍራንክ ውጦ የፈለጉትን ከሚተፋው አውቶማት የማቀዝቀዣ ሳጥን ውስጥ ለእራሱ ሶዳ ውሃ ለሌሎቹ እንዳሉት ገዝቶ አከፋፈላቸው። ፋጡማ አንገቷን ቀና አድርጋ በፈገግታ ጆኒን ተመልክታ አመሰገነችው ድምጿ የማባበል መረዋ ሆኖ ተሰማው አይኖቹ ፈዘው ልቡ በመውደድ ወላፈን ሞከከ።

ጆኒ አይጥል ጥሎበት ሆኖ ፋጡማን «የኔ ብትሆን» እያለ ዘወትር ይመኛታል። ያልማታል። እሷ ግን ለእሱ እንብዛም ግድ የላትም። የሮዚ የሀገር ተወላጅና የቅርብ ጓደኛዋ መሆኑን ስለምታውቅ ብቻ ታቀርበዋለች እንጂ እሱ እሷን እንደሚያስባት አልሆነችም። እሱም የልቡን ደፍሮ ሊነግራት አልቻለም።

ጆኒ በዚሁ ስሜት ተሞልቶ አጠገቧ ስለነበረ ሂሳቡን ማሰብ አቅቶት እጁ ተንቀጠቀጠ። አይኖቹ እሷን እያዩ ቦዘዙ። ፋጡማ ከእሷ ምናምን የከጀለ መስሏት የሲጃራዋን ፓኬት አንስታ ጋበዘችው። «አመሰግናለሁ አላጨስም» አላት በተቆራረጠ ድምፅ። ለእራሷ ለኩሳ ጭሱን አቦነነችው። ጆኒ ግራ ተጋባ ከአፏ የቦነነው ጭስ አማረው» ይቅርታ ፋጡማ ከፈለግሽ አንቺ የለኮሽውን ልሞክረው» ብሎ ጠይቆ ሰጠችው። የከንፈሮቿ ቀለም የነካውን አፏ የጨበጠውን ትንፋሿን አምቆ የያዘውን ቁራጭ ሲጋራ ይዞ ማግ! ማግ! አደረገው ልቡ ጮቤ ረገጠ። ሳንባው ግን ተቆጥቶ በቶሎ አኮረፈ። «ኡህ! ኡህ! ኡህ! ኢህ! ኢህ! ኢህ!» ጭሱ ጉሮሮውን ኮርኩሮት ቆሞ ደጋግሞ ሳለ። ሳይወድ በግድ ፋጡማ የሰጠችውን ሲጋራ ይቅርታ ብሎ መተርኮሻው ላይ ደፈጠጠው። አሁንም ደጋግሞ ሳለ።

ሮዚ ደንግጣ «ምነው ወንድሜ ምን ነካህ?»

«ሲጋራው ነው! ኡህ! አህ» እያለ መለሰላት። የልብ ውጋት ስላለው ጆኒ ሲጃራ አይስማማውም።

ሮዚ ወደፋጡማ ዞር ብላ «ለምን ሰጠሽው? ወንድሜን ልትገድይው ነው» ብላ ቆጣ ቆጣ አለች። ፋጡማ «ስጪኝ አለኝ ሰጠሁት ምን ይጠበስ ብለሽ ነው አሁን ይለቀዋል» አለቻት።

ጆኒ ሳሉ እየቀነሰ ሄዶ አይኖቹ አነቡ። ቶሎ ቶሎ ተንፍሶ ደግሞ አሳለው። ሮዚ «ሶዳውን ጠጣበት ይለቅሃል» ብላ ውሃውን ሰጠችው ተቀብሎ ግጥም አርጐ ጠጣው ትኩስ አየር ለመቀበል ተሰናብቷቸው ወጣ ክፍሉን ለቆ ሲወጣ ከአዳራሽ ሳይሆን ከግድቤት የወጣ ያህል መሰለው። አሁን ትኩስ አየር ተንፍሶ እፎይታ ተሰማው።



ክፍል አራት

ጊዜው እየሮጠ ሄዶ ሽጋው
የሰኔ የበጋ ወር በደማቁ የሐምሌ ወር ተተካ። ኢትዮጵያ ክረምት ጀርመን
በጋ። ደማቂ ፀሐይ በምድረ አውሮፓ ወለል ላይ ጥርሶቿን ፈልቅቃ እየሳቀች
መጣች። የማይጠገብ ሙቀትና ብርሃንዋን ለሕዝቡና እፅዋቱ እያደለች።

ለአውሮፓ ሕዝብ በጋ ብርቁ ነው። ዓመቱን ሙሉ ለፍቶ
ያጠራቀመውን ገንዘብ የሚያውለው ለዓመት እረፍቱ (Urlaub) ማለት
ፀሐይ ወዳለችበት ዘወትር በጋ ከሆነበት ልዩ ልዩ ሀገሮች ነው።
የአውሮፓ ሕዝብ የረዥም ወራቶችን ብርድና ቁር ቢለምደውም
አንገፍግፎታል።

ታዲያ ክረምት አልፎ በጋ ሲመጣ ሕዝቡ እንደ ክብረ በዓል ቆጥሮ
ከበጋው ወራቶች ጋር አብሮ ይፈነጥዛል። ይጨፍራል። የበረንዳ
ሰንጠቶች፣ የጓሮ ሚዳዎች፣ ለዚሁ ፈንጠዝያ የግሪል ጥብስ መጥበሻ
የቀዘቀዘ ቢራ መጐንጫ የድግሥ አውድማ ሆነው ያገለግላሉ።

የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች የበጋውን ልብስ በብዛት አምርተው
በደንብ ለሕዝቡ የሚቸረችሩበት የሚያተርፉበትና የሚከብሩበት
ወቅቶች ቢኖሩ ይሄው ሰኔ ሐምሌና ነሐሴ የበጋ ወራቶች ናቸው።

የሴቶች ባትና ዳሌ፣ የወንዶች ያበጠ ትከሻና የተነፋ ደረት፣ የልጅ
አገረዶች ያጐጠጐጡ ጡቶች፣ ሳንቃ የመሰለ ደረት፣ ሆድና እንብርት
በግላጭ ታይቶ የሚቋመጥበት የስሜት አውታሮች የሚነቃቁበት የወሲብ
ሲግይ ፀጋ የሚዘከሩበት በነዚሁ የበጋ ወራቶች ነው።

ጊዜ እንደ ተራራ ተንዶ ያለፈው የሰንበት ቀን ተንሸራቶ፣ ሌላ ብዙ
እሁዶችን ተክቶ፣ ሰኞና ማክሰኞ እንደ ዋዛ አልፈው የዛሬን የሳምንቱን

መሐከል እረቡን ወለዱ። ሮዚ የሦስት ቀን እረፍት ወስዳ ትላንትን እንደ
ዋዛ አሳልፋ የቀሩትን ሁለት ቀኖች በደንብ ለመዝናናት አቅዳለች።

ቤታ ፈንዶርፍ ከሚባለው የብሬማን አንዱ ቀበሌ የጥቁሯ ፓይለት
መኖሪያ አፓርትመንት ነው። ሮዚና ክላውዝ በፍቅር ተቃቅፈው
ከአደሩበት ሰፊ አልጋ ላይ እያዛጉ ተነሱ። የለሊቱ የፍቅር ሞውዉት
ጥቂት ቢያደክማቸውም አብረው ዋና ቦታ ለመሄድ ስላቀዱ በቶሎ
ተነስተውና ተጣጥበው ለመለባበስ እንብዛም ጊዜ አልወሰደባቸውም።

ሮዚ ቁም ሳጥኗን ከፍታ የዋና ልብሶቿን ይዛ ለመሄድ ፈልጋ አጣች።
አንዳንድ ጊዜ ያስቀመጠችው ነገር ከፊታ ሲሰወርና ሲጠፋባት
ያናድዳታል። ቀልቧን ምን እንደሚገፈው ይገርማታል። ፍቅር አይሉት
እርጅና ሰሞኑን የዋል ፈሰስ ሆናለች። ክላውዝ ስለተጣደፈ እሮዚ
እቃውን በመፈለግ ስለዘገየች ቤት ውስጥ ጭቅጭቅ ተፈጠረ። «እንሂድ
እባክሽ» «ቆይ ትንሽ» «ቶሎ በይ እንጂ» «እባክህ ታገሥ» አሉታና
አውንታ እሰጥ አገባ አይነት ክርክር። እቃው ጠፍቶ ሮዚ እቃዎችን
መነቃቀረች። ክላውዝ መቀመጥ ሰልችቶት ተነስቶ ተንቆራጠጠ።

አንጥፈው የሚተኙበት የላስቲት ፍራሽና ፎጣዎች የመታሻ ክሬምና
የሻንፓ ሳሙና የሚበሉት ፍራፍሬ በቅርጫት ቦርሳ አብረው ተከተው
ተያዙ። የዋናው ልብስ ባይጠፋም ለጊዜው አልተገኘም። በዚህም
ምክንያት እግረመንገዳቸውን የግድ ወደ ሱቅ መሄድ አስፈላጊ ሆኖ
ተገኘ። የመዋኛና የመዝናኛ ጊዜያቸው ሳይባክን ተጣድፈው እጅ ለእጅ
ተያይዘው አብረው ከቤት ወጡ።

የፀሐይዋ ግለት ሰውነትን ይለመጥጣል። የሁለቱም አለባበስ
ሙቀትን አሸሾ የሚገፈትር ነበር። እንደ ወተት አረፋ የነጣ የሐር
ሸሚዝና ካኪቴራ። ክላውዝ የመኪናውን በር ከፍቶ ሮዚን አስገብቶ ወደ
ከተማው እንብርት ገበያ ፈረጠጠ። የሮዚ ሹርባ በንፋሱ እየተመታ
ተውረገረገ ወደኋላ ተለጥጦ ተርገበገበ። የክላውዝ ሰፊ ደረት በኩራት
ወደ ፊት ተለጠጠ።

ሁለቱም ከመኪናቸው ወርደው ሰፈው አዳራሽ ሱቅ ገቡ። ሕዝቡ
እንደ ዋርካ ዛፍ ወፎች በለዘብታ እርስ በርሱ እያወራ ይንጫጫል።
ቀፎው እንደ ተነካ ንቦች ከወዲህ ወዲህ ሽቀጦችን እያማረጠ
ይርመሰመሳል።

ሮዚ ያን ስታወርድ፣ ያን ስትጥል ያየቸውን ትታ ሌላ ስታማርጥ፤ ክላውዝ በበኩሉ ለፍቅራቸው መታሰቢያ የሚሆን ስጦታ በልቡ ድንገት አሰቦ ኪሱን ሲዳብስ፣ ጊዜ ቆማ አልጠበቀቻቸውም። የገዙትን ገዛዝተው ወጡ። ከዋና በኋላም አብረው ተጉራርሰው የሚበሉትን ሳንድዊች በተጨማሪ ለመግዛት ወደ ቡርገር ኪንግ ፈጣን የምግብ አዳራሽ አመሩ።

መንገድ አቆራርጠው ሲያልፉ ድንገት ደመቀ ጉበና ከተባለ ኢትዮጵያዊ ጋር ተገናኙ ሰላምታ ተለዋውጠው ሲጨርሱ በሀገራቸው ቋንቋ ተወያዩ።

«በቅርቡ ለእረፍት ወደ ኢትዮጵያ እሄዳለሁ»

«አትለኝም»

«ውድ ሀገሬን አይቼ በደንብ ተዝናንቼ እመጣለሁ»

«ታድለህ ግን እኮ ደመቀ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ከረምት ነው»

«አውቃለሁ። ጨለማ ነው አትበይኝ እንጂ ምን የኢትዮጵያ ክረምት የጀርመን በጋ ነው።»

«በል ስትሄድ ደውልልኝ ለቤተሰቦቼ ትንሽ ስጦታ ይዘህልኝ ትሄዳለህ»

«ካልበዛ በደስታ» ተባብለው ሲሰነባበቱ ደመቀ እየሳቀ «ሲያዩዋችሁ ልክ ሳምሶንና ደሊላን ትመስላላችሁ» ብሎ ሮዚን አሳቃት።

ክላውዝ ቋንቋው ስላልገባው የሳቀችበትን መክንያት ጠይቆ እሱም አብሮ ሳቀ። የሳቀው ግን በተነገረው ቀልድ ብቻ ሳይሆን ደመቀ ጉበና በዚህ በሞቃት ወራት ሙሉ ገበርዲን ለብሶ ከረባት አሥሮ ላቡ ግንባሩ ላይ እየተንቆረቆረ በሙቀት መጨነቁን ማየቱን ጭምር ነበር። «ሲያጌጡ ያምራል እንደወቅቱ» ብሎ የሀገሩን ተረት በጀርመንኛ ተርቶ የሮዚን ወገብ በቀኝ እጁ አቅፎ ወደተባለው ፈጣን ሬስቶራንት አብረው ገቡ።

ምግባቸውን ለመግዛት ተራቸውን ይዘው ተሰለፉ። በቅርቡ ጀርመን የመጡ ሁለት ኢትዮጵያውያን ሴቶች እዚሁ የምግብ አዳራሽ ተቀጥረው ሽር ጉድ ጉንበስ ቀና እያሉ ምግብ ያዘጋጃሉ። አየሩና የግሪሉ ሙቀት ተጨምሮ ወበቁ አፍናአቸዋል። ላባቸው ችፍ ብሎ ይንጠባጠባል። ሮዚ

ስለምታውቃቸው በፈገግታ ሰላም አለቻቸው። ሥራ መሥራት ያስነውር ይመስል ትንሽ አፈር ቀለስለስ ሽምቅቅ በማለት አጸፋውን መለሱ።

ሮዚ ዓይኖቿ እነሱን እያየ ሀሳቧ እርቋት ሄደ። ገና ጀርመን እንደመጣች ሰሞን ገንዘብ ቸግሯት ጀኒን ብድር ስትጠይቀው «ለምን አትሠሪም ሥራ ከፈለግሽ በጥቁር እኔ አስቀጥርሻለሁ።» ብሎ የሆነ የግሪክ ሬስቶራንት ውስጥ አስቀጥሯት ነበር። ያኔ ያየችውን ስቃይና ፍዳ በማስታወስ አዘነች። «እስኪያልፍ ያለፋል» ብላ ተረተች። እነዚህን አሁን ሽር ጉድ የሚሉትን ለግላጋ ወጣቶች በዓይኖቿ ገርምማ በማየት «ይሄኔ እነሱም እንደ እናታቸው ጓዳ ተቀምጠው ሙቅ እያንከኩ «ውሃ ቀጠነ» የሚሉ ሳይሆኑ አይቀርም ማን ያውቃል» ብላ ገመተች።

«አምን ጀርመን ገንዘብ የሚታፈስበት ገነት ትምህርት የሚቀሰምበት ዩኒቨርስቲ ፈረንጅ ሀገር ባሕር ማዶ የስንቱን ቀልብ የገፈፈ ምኞት። አዳሜ ከሀገር ለመውጣት የማያደርገው ውጣ ውረድ የማያደርገው ሽር ጉድ አልነበረም። ኢንባሲዎች በራፍ ላይ ተኮልኩሎ እንደመሻገር የሙጥኝ ብሎ የማያወላዳ ጉቦ ሰጥቶ ተመላልሶና ደጅ ጠንቶ ኧረ ስንቱ አበሰገበርኩ። መጨረሻው ይሄው የምናየው የፈረንጅ ሰሃን አጣቢ መሆን ነው ትርፉ። ፈረንጅ ሀገር ካልተማሩበት ደደብ ሆኖ ሆድ ሞልቶ ጭንቅላት ባዶ። እንደኔ ዝቃጭ ኑሮ እየኖሩ ሕይወትን መግፋት። ኧረ በስንት ጣእሙ ሀገሬ። በህልና ወጉ ምግብና አየሩ ያልጐደለባት ምንም ብትደኸይ ፍቅር ያለባት ውድ እናቴ ኢትዮጵያ አንቺ ነሽ መኩሪያዬ» ብላ በሆዷ ተናግራ በትዝታ ተዋጠች።

ጊዜ እንደሳሙና እያሚለጨ ሄዶ ሳይታወቃቸው 14 ሰዓት ሆነ። ሮዚና ክላውዝ ምግባቸውን ገዝተው እጅ ለእጅ ተያይዘው ደመቀ እንዳለው ሳምሶንና ደሊላ መስለው ከምግቡ አዳራሽ ብቅ አሉ። የፀሐይዋ ግለት ትንሽ በረድ ብሏል። ንፋሱ የደረቀ ቢሆንም ይነፍሳል። መኪናቸው ውስጥ ገብተው የፓርካሌን መንግድ ይዘው ወደ ብሪማን ዩኒቨርስቲ ጓሮ ተጓዙ።

በመንገዱ ግራና ቀኝ ተተክለው የሚታዩት ዛፎች ቅጠሎቻቸው ተንዥርጉና አብቦ የላይኛው ቅርንጫፎቻቸው እርስ በእርሳቸው ተገጣጥመው ቀስተ ዳመና መስለው ይታያሉ። በዚህ የገነት ማሰገቢያ

በመሰለ የተከሉች ዋሻ ጉዳና ሮዚና ክላውዝ ውስጥ ውስጡን አቆራርጠው ትኩስ ሙሽራ መስለው አለፉ።

«ምነው ቅር አለሽ?» አለ ክላውዝ እሮዚን ወደ ጉን እያየ

«ሀገሬ ትዝ ብሎኝ ነው» አለች የሹርባዋን አንድ እግር በጣቶቿ እያፍተለተለች።

«ትዝታን አሁን ምን አመጣው?»

«የምታያቸው ለምለም ዛፎች የበጋው ፀሐይ የሀገሬ የትዝታ መሐደሮች ናቸው።»

«እንቺን ሊጠይቁ ይሆናላ የመጡት? ማን ያውቃል።» አላት እየሳቀ ትካዜዋን በቀልድ ሸፍኖ ለመለወጥ እየሞከረ።

«እባክህ አትቀልድ ክላውዝ» ብላ በትዝታ ቅላጼ «ተራራው ሸንተረሩ የመስከረም አዬ አበባው ፏፏቴና ወንዙ ድህነት ነው እንጂ ሀገር ማለት ኢትዮጵያ ናት! እኮ!» ብላ አንገቷን ሰበቅ ትከሻዋን ወዝወዝ በማድረግ ተኩራራች።

«ለመጪው ዓመት ለእረፍት አብረን እንሄዳለን»

«አንተማ እዛ ከገባህ ጨርሶ አትወጣም።»

«እስከዚህ ድረስ ገነት ሀገርሽን ማድረግሽ ነው እንዴ?»

«ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ! ባየሀት ከገነት ትበልጣለች» አለች ቆምጨጭ ብላ።

«አስተዳደሩስ እንዴት ነው?» አላት ቁንጅና ብቻ ታጥቦ አይጠጣ በሚል ስሜት

«ስለ እሱ አትጠይቂኝ ያናድደኛል። ከውድ ሀገሬስ የወጣሁት በዚሁ ምክንያት አይደል ነግሬሀለሁ» ብላ ሲጃራዋን አውጥታ ለኮሰች።

የደርግ ግፋዊ አስተዳደር፣ የቀይ ሽብር ዘመቻ (E.P.R.P) ለሕዝብ ነፃነት ያደረጉትን ተጋድሎ እፊታ ተደቀነ። ታላቅ እህቷ በዚሁ ግርግር ከ(E.P.R.P) ድርጅት ጋር ሆና ወረቀት ስትበትን በወታደር ጥይት ተመታ መሞቷን አስታውሳ ዓይኖቿ እንባ አቀረሩ። «ዘር ከሎጋም ይስባል» ሆነና እሷም የእህቷን ፈለግ ተከትላ ወረቀት ብተና ሽር ጉድ ማለት ጀመረች። እናቷ ወ/ሮ ቦጋለች ከባለቤታቸው ጋር ተመካክረው ከአዲስ

አበባ ገጠር በየዘመዱ ቤት ደብቀውና ደባብቀው በኬንያ በኩል ከሀገር እንድትወጣ አደረጉ። የስደት የመከራ የመንገላታትና የስቃይ ኑሮ ሮዚ ያለፈውን ጥቂት ዓመታት የጨለመ ኑሮ ኑሮዋን አስታውሳ ትከሻዋን ወዝወዝ አድርጋ ተንገፈገፈች።

የእግረኞች መተላለፊያ ቀይ የትራፊክ ማብራት ድንገት ስለበራ የመኪናው ፍሬን የሲጢታ ጩኸት ከገባችበት የሕልም ዓለም ገፍትሮ አስወጣት። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጅ ጥቁርና ነጭ ልብስ ለብሰው እጅ ለእጅ ተያይዘው በእግረኛ መተላለፊያ ዜብራ ቀለም ላይ የሕፃን ጋሪ እየገፉ መንገዱን አቋረጡ። የክላውዝና የሮዚ ዓይኖች በነዚህ ባልና ሚስት በሚመስሉ ፍቅረኞች ላይ አረፈ። አረንጓዴ በርቶ መኪናዋ ተንቀሳቀሰች። የሮዚና የክላውዝ ውይይት ከሀገር ትዝታና ፍቅር ወደ ትዳር ልጅ ወልዶ ወደመሳም ለሶስት ጉልቻ ወግ ለመብቃት ፍቅር ደስታ ሰላምና እርካታ የሚገኝበትን ጉጆ ለመቀየስ ወደሚያስችለው እቅድ ተላልፎ ውይይቱ ቀጠለ።

ክላውዝ ጥያቄውን ለመጠየቅ ሲፈራ ሲቸር ደፍሮ እያመነታ ድምጹን ለዘብና ለስለስ አድርጉ ፊቱን ወደ ሮዚ አዘንብሎ።

«አትቀየሚኝና አንድ ነገር ልጠይቅሽ ሮዚዬ» አላት ስሟን እያቆላመጠ በተለማማጭ ድምፅ።

«ምን?» አለች እሷም እንደሱ ስሙን ጠርታ እያቆላመጠች።

«ለትዳር ያለሽ ፍላጐት፣ ስሜትና እቅድ እንዴት ነው?» አላት በተቆራረጠ ድምፅ ከአሁን በፊት እንዲህ ያለ ጥያቄ ጠይቆ ስለማያውቅ ሁኔታው ትንሽ አስደነገጣት።

«እህ!» ብላ በመተንፈስ ትንሽ አሰበች። «ትዳር ትዳር» ብላ ቃሉን በአንክሮ ደጋገመችው። ለወግ ለመአረግ ደርሶ፣ የሙሽራ ልብስ ተለብሶ፣ ለጫጉላ ወግ በቅቶ ብራንባር የሚያሠብሩበት፣ «ሎጋው ሽቦ» «ዋርዳው ሽቦ» ተብሎ የሚጨፈርበት «የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው» «ኩሉን ኩሉን ማን ኳለሽ» ተብሎ የሚዘፈንበት የሀገሯ የሙሽርነት ባሕል የትዳር ምሥረታ በዓል ተመልሰው በትዝታ መጡባት። ዓይኖቿ የትዝታን ሥዕል እያዩ ተንከራተቱ።

«ለነገሩማ ሀገር ቤት እንዳለሁ ለትዳር የሚመኝኝንና አማላጅ ልኮ የጠየቀኝን የወንዶች ብዛት እሱ ይቁጠረው። እኔ ለዚህ አልታደልኩም» ብላ በሆዷ በማሰብ እድሏን እረግማ ኑሮዋን አማረረች።

ሮዚ ድንግልናዋን ያስወሰደችው በትዳር ሳይሆን ገና በልጅነቷ ትምህርት ቤት እያለች ነበር። አንድ ትውልዱ ሕንዳዊ የሆነ የሂሳብ መምህር አስጠናሻለሁ ብሎ ነበር ከብርናዋን የገፈፈው። አሁን እሱ አልቆጫትም። ብቻ «ትዳር» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ትንሽ አመን ትታ «ምን ተይዞ ጉዞ በአሁኑ ጊዜ ይቅርታ አድርግልኝና ጋብቻ ትዳር ፈጽሞ አይታየኝም» አለችው መልሷ የክላውዝን ስሜት እንዳይጐዳ ተጠንቅቃ እየፈገገች።

ክላውዝ «ምን ይዞ ጉዞ ከማለት ለትዳር ክላውዝን ይዞ መሞሸር ነው» አላት እንደ ቀልድ ምንም የሮዚ ፊት በፈገግታ ቢሞላም ውስጧ የሀዘን እረመጥ እንዳለው ጠርጥሮ። እየሳቀ አባብሎ ወደቁም ነገሩ ውይይት እያመራ።

«አየህ ክላውዝ በእርግጥ እወድሃለሁ ከልቤም አፈቅርሃለሁ ግን ያልከኝን በአሁኑ ጊዜ አላደርገውም እንዳንተ የመማር ፍላጐት ሌላም ብዙ ዓላማዎች አሉኝና ለጥያቄህ የአወንታ መልስ ባለመስጠቴ ይቅርታ» ብላ በለሰለሰ ጣቶቿ ጉንጮቹን አባብሳ አባበለችው።

«ልጅስ ብንወልድ ምን ይመስልሻል?»

«በእርግጥ ልጅ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ ግን ከትዳር በፊት መሆን የለበትም።»

‹ለምን?›

«የፈረንጅ ዲቃላ ማሳደግ ስለማልፈልግ ብቻ ነው» ብላ እቅጩን ደፍራ ነገረችው።

አርእስቱ ከባድ ውይይቱ ሰፊ ቢሆንም ዋናው ቦታ ስለደረሱ ንግግራቸው ተቋረጠ።

ዩኒዚ ከሚባለው የመዋኛ ትልቅ የባህር ሽለቆ ደርሰው መኪናቸውን ጥግ አሲዘው እቃቸውን ይዘው ወደ ባህሩ ተጠጉ። ልክ የደብረ ዘይትን ሆራ ይመስላል። ማዶ የሞተር ጀልባ የሚያከራዩ ሰዎች እንደ ታክሲ ገበያ ተራቸውን ይዘው ቆመዋል። ወዲህ ወጣት ሽማግሌ ወንድ ሴት

የተለያዩ ቀለም ያላቸው የዋና ልብሶች ለብሰው ባሕር ውስጥ ይዋኛሉ። በባህሩ ዳርቻና ሌላ ማዶ ሥፍራ ቮሊቦል የሚጫወቱ ግሪል ጠብሰው የሚበሉ ተቃቅፈው ሜዳ ላይ የሚንከባለሉ ሰዎች ይታያሉ።

የቀዘቀዘ ቢራና ለስላሳ አይስ ክሪምና በረዶ የሚሸጡ ቸርቻሪዎች በየቦታው ሰፊ ጥገጥላቸውን ዘርግተው ንግዳቸውን ያጧጡፋሉ። የሚነበብ ጋዜጣና መጽሔት በየቦታው በመሸጥ የሚያከፋፍሉ ወጣቶች ከወዲያ ወዲህ ውር ውር ይላሉ። ቀደም ብለው ዋኝተው የጨረሱ ያነጠፉት የላስቲት ፍራሽ ላይ ተጋድመው እርስ በእርሳቸው በክሪም ይተሻሻሉ። አንዳንዴም የፍቅር ጥፊ የፍቅር ንክሻ ይለዋወጣሉ። በቁም ነገር ቁጭ ብለው ዓይን ለዓይን እየተያዩ የዛሬን ትተው ስለ ነገው አልመው ባልተጨበጠ ተስፋ ሙግት ገጥመው የሚጨቃጨቁም አሉበት።

አቅጣጫው የማይታወቀው የሞቀ ደረቅ ንፋስ ባህሩን በጥፊ እየመታ የመአበል አረፋ ፈጥሮ ይንቻቻል። እንደልተገራ ፈረስ ወደ ላይ እየዘለለ ተመልሶ እየወረደ ፺! እንቦሽ! የሚል ድምፅ ያሰማል። ዋናተኞች ከዚሁ የውሃ ግፊት ጋር አብረው ይታገላሉ። አንዳንዶቹ እርስ በእርሳቸው እየተደፋፈቁ የጠራውን ውሃ ያደፈርሳሉ።

ሰማዩ ጠርቶ ፀሐይዋ ጥርሶቿን አግጣ በብርሃን የደመቀ ፊቷን እያሳየች ትቁለጨለጫለች። የባህር አሞራና ወፎች ከወዲህ ወዲያ እየበረሩ እርስ በእርሳቸው ያስካካሉ። ጥቂት የሞተር ጀልባዎች በርቀት ባሕሩን እየቀዘፉ ውሃውን ለሁለት ከፍለውና ሰንጥቀው በሃይለኛ ፍጥነት ይተላለፋሉ።

ሮዚና ክላውዝ ልብሳቸውን ለመቀየር ከባህሩ አጠገብ ካለው የልብስ መለወጫና መጠዳኛ ቤት በየጸታቸው ባለው ክፍል ተለያይተው ገቡ። ሮዚ የለበሰችው የዋና ልብስ ቀለሙ የጐላ በመሆኑ ጠይም ገላዋን ትንሽ አጠቆረው። ያጐጠጐጡ ጡቶቿ በአዲሱ የላስቲክ መወጠሪያ ጡት መያዣዋ ስለተወጠሩ ገና ሊተኮሱ የተጠመዱ መንታ ሮኬቶች መሰሉ። ሹርባዋ በላስቲክ የዋና ቆብ ተሰብስበው ታሸጉ።

ክላውዝ የወንድነት ሀብቱን ወጥሮ የያዘውን ቀይ የዋና ቡታንቲ አጥልቆ እርቃኑን ያበጠ ደረቱን ነፍቶ የፈረጠሙ ጡንቻቹን አጉረጥርጦ ብቅ አለ። ተንደርድሮ እየሮጠ ወደ ላይ ዘሎ ባህር ውስጥ ሶቶ ገባ። ውሃው ቦንብ እንደ ወደቀበት ለሁለት ኗ! ብሎ ተገመሠ። ነጭ አረፋ ፈጥሮ ተፍለቀለቀ። ሮዚም እንደሱ እሮጣ ባሕር ውስጥ ድርግም ብላ በሁለት እግሮቿ ዘላ ገባች። ክላውዝ እርቆ ባሕሩ ማህል ደርሷል። የዋና ችሎታው የሚደነቅ ነው። የእጁ አወዛወዝ የእግሮቹ ቅልጥፍና የትንፋሽ አወሳሰድና የሰውነት አገላባበጥ ቶሎ ሳይደክም ብዙ መዋኘት አስችለውታል።

ሮዚ ባሕሩ ላይ ተኝታ ትንቦራጨቃለች። ፍጥነቷ ካለችበት እንብዛም እርቆ አልወሰዳትም። ውሃውን በመጠኑ አረፋ አጉረፈችው። ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በቶሎ ደከመች። ወደ ፊት ከመሄድ ተቆጥባ ወደኋላ ወደ መሬቱ ዳርቻ ተመለሰች። ዋና ከዋኘች ሰንብቷል። ቅልጥፍና ባይኖራትም የጥንት የልጅነቷን የዋና ችሎታዋን ባለመዘንጋቷ ደስ ብሏት ፈገግ አለች።

ክላውዝ በኃይለኛ ፍጥነት ተመልሶ ሮዚ ወዳለችበት ተጠጋ። አብረው ታያይዘው ጥልቅ ካልሆነው ቦታ ተቃቅፈው ቆሙ። እርስ በእርሳቸው ተሻሽተው ተገፈታተሩ። ክላውዝ የሮዚን እግር ይዞ ወደ ጥልቁ ባህር አመራ። ሁለቱም አብረው ሰመጡ። ብቅ ጥልቅ እያሉ ተደፋፈቁ። እርስ በእርሳቸው እየሳቁ ወደዳር ተመልሰው መጥተው ውሃ እየተራጩ እንደ ሕፃን ልጆች አብረው ተንቦራጮቁ። በዚህ አይነት ባሕር ውስጥ ብዙ ቆይተው ሲደክማቸው እየወጡ አርፈው እንደገና ተመልሰው ዋኝተው ጥሩ ጊዜ አሳለፉ። በመጨረሻም ሰውነታቸውን በቀዝቃዛ ሻወር ተለቃልቀው ከባህር ማዶ ባለው ጥሩ ቦታ የላስኪት ፍራሻቸውን አንጥፈው በጀርባቸው ተንጋለሉ።

ፀሐይዋ ለብ ያለ ሙቀቷን ለገሠቻቸው። ክላውዝ ከተኛበት ቀና ብሎ የሮዚን ጀርባ በቅባት ማሸት ጀመረ። ሮዚ ሰውነቷ ተፍታታ።

ደረቷንም እንዲያሽላት ፈልጋ ተገላብጣ በጀርባዋ ተኛች። ሰውነቷ በቅባት ተብለጨለጨ ክላውዝ አይቶ ጉመጀ። ማሸቱን ትቶ ከንፈሩን ከከንፈሯ ገጥሞ አብረው ተመጣመጡ። እሷም እንደሱ የክላውዝን ሰፊ ጀርባ በቅባት አሸችለት። ወገቡ ላይ ወጥታ እንደ ፈረስ ጋለበችበት። ሁለቱም በዚህ አይነት ልፊያ ተቀላልደው በደስታ ቦረቁ። ያመጡትንም ፍራፍሬ እንደ አዳምና ሔዋን እየተቀባበሉ በሉ። አንድን የትርንጎ ፍሬም ተጐራርሰው ተገማመጡ።

ክላውዝ ለትውውቃቸው መታሰቢያ ለፍቅራቸው ማዳበሪያ እንዲሆን ቅድም ከሮዚ ተሸሽጐ የገዛውን የወርቅ ሐብል ከደበቀበት ሥርቻ አውጥቶ አንገቷ ላይ አጥልቆ ሸለማት። ሮዚ በስጦታው ተደስታ «አመሰግንሃለሁ» የሚለውን ቃል ሳትናገር አቅፋ ሳመችው። ወርቅ ከመጠን በላይ ትወዳለች። ባለፈው ሰኔ ወር ልደቷን ስታከብር የአልማዝ ፈርጥ ያለበት ጉትቻ ሸልሟታል። ከናቷ ከሌላም ወዳጆቿ እራሷም በግል የገዛችው ብዙ ወርቆች አሏት። ወርቅ አትጠግብም ትወዳለች። በሥራዋ ብዛት እንብዛም ባታጌጥባቸውም የራሴ ብላ የምትኮራባቸው የወርቅ ጌጣ ጌጦች ማጠራቀም ትወዳለች። ባንገቷ የጠለቀውን ሐብል አውልቃ በእጆቿ ይዛ ደጋግማ ስማ «ልክ የምወደውን ዓይነት ነው የገዛህልኝ» ብላ «ና! ና! ተጠጋኝ» ብላ ሲቀርባት ደግማ ከልቧ ሳመችው። ሁለቱም በጀርባቸው ተንጋለው የምሽቷን ጀንበር ሙቀት ተቀበሉ።

ሮዚ ሰማይና ባሕሩን ተመልከታ እንደሰመመን ያለ ሽልብታ ወሰዳት። የቆየ ትዝታ በሀሳቧ መጣባት። ያኔ ድሮ ልጅ ሆና ጊዎን ሆቴል ዋና እንዴት እንደተማረች ከዛም በኋላ አድጋ ለእረፍት ሲዳሞ ላንጋኖ ከሚባለው ትልቅ የባህር ጅረት ውስጥ እንደዋኘች አስታወሰች። በተለይ ከቅርብ የትምህርት ቤት የሴት ጓደኛዋ ጋራ ሆና በዚሁ ሥፍራ ያሳለፉትን የደስታ ምሽት ትዝ አላት። ባሕሩ አጠገብ አሸዋው ላይ አሳት አንድደው እየሞቁ ያለፈውን የፍቅር ታሪካቸውን አንስተው እያወጉ የተሳሳቁትን፣ የምሽቱን ሙሉ ጨረቃ ወደ ላይ አንጋጠው እየተመለከቱ።

«ጨረቃድንቡል ቦቃ
አጤ ቤት ገባች አውቃ
አሊሆ አላሊሆ
ጣይልኝ ድፎ ዳቦ
የማካፍለው ለብዙ ሺ
ይቺን ትተሽ ይቺን አንሺ»

እያሉ አብረው እየዘፈኑ የተጫወቱትን አስታውሳ ዓይኖቿ እንባ አቆርዘው አሸልባት ሳታስበው ተኝታ አንኮራፋች።

ክላውዝ ሳይቀሰቅሳት ከአጠገቧ ተነስቶ ማዶ ከሚገኘው ሱቅ የሚጠጡትን ለስላሳ መጠጥና ቢልድ የሚባለውን ጋዜጣ ገዝቶ መጣ። ሮዚ ነቅታ ጠበቀችው። ቀዝቃዛውን መጠጥ ተጐንጭተው ተመልሰው በጀርባቸው ተንጋለው ተኙ። ክላውዝ የገዛውን የቢልድ ጋዜጣ ጮክ ብሎ ለሮዚ ማንበብ ቀጠለ።

ከሰዓት በፊት ሙሽራ ከሰዓት በኋላ ጋለሞታ የሚለውን አርእስት ይዞ ሙሽሪት ከነሙዚዎቿና ደንገጡሮቿ የጋብቻ መፈጸጸሚያ ቢሮ በነጭ ልብስ አምራ ሙሽራዋን ባሏን ከአሁን አሁን ይመጣል እያለች ትጠባበቃለች ባል በመኪናው ወደሷ ሲገሠግሥ ምክንያቱ ባልታወቀ ጥይት ተመቶ ይሞታል ሚስት እረፋዳው ላይ ነጭ የሙሽራ ልብሷን አውልቃ ጥቁር ቀሚስ ለብሳ በሀዘን ተውጣ ታየች።

«ጥቁር ስደተኞች በሚኖሩበት መኖሪያ ቤት የክብቴል ፈንጂ ወርውረው በተኙበት ቤቱን አቃጥለው ብዙ ሰዎች የገደሉት ዘረኛ ወጣቶች ከሁለት ዓመት እሥራት በኋላ በነፃ ተለቀቁ» ሮዚ እራሷን ይዛ ጮኸች «ይሄ ትክክል አይደለም እኔ ብሆን አሥር ዓመት ወይም ሞት ነበር የምፈርድባቸው» ስትል ክላውዝ በጀርመን ሀገር በሞት ቅጣት ፍርድ እንደሌለ ነገራት።

«ኃይሌ ገብረ ሥላሴ የሚባለው የኢትዮጵያ እሯጭ በአትሌቲክ ውድድር በአምስት ሺ እሩጫ የአለምን ሪኮርድ በጠሰ።» ሮዚ ከተቀመጠችበት ተነስታ እየዘለለች ደስታዋን ገለጠች። ይሄውልህ ክላውዝ ስማው የኛን ጉብዝና ብላ ፎከረች። የጥንቱንም የማራቶን ጀግና የአበበ ቢቂላንና የማሞ ወልዴን ታሪክ አንስታ አወራችለት።

ክላውዝ ማንበቡን ቀጠለ «እድሜያቸው ከስምንትና ከአሥር የማይበልጡ ሕፃን ሴቶች ባልታወቀ ሰው ተጠልፈው የሕፃናት ፓርኖ ፊልም እንዲሠሩ ተገደውና ተደፍረው እራሳቸው ተገኘ።»

ሮዚ «እናንተ ነጮች አረመኔዎች ጨካኝና ግፈኞች ናችሁ አበስኩ ገበርኩ» ብላ ክላውዝ ላይ አፈጠጠችበት።

ክላውዝ «ሁሉን ነጭ በጅምላ አትሳደቢ ከጥቁሮችም ቢሆን ይህን የሚያደርጉ አይታጡም» አላት።

ሮዚ በቁጣ አንደበት እየተቅበጠበጠች «ጥቁር በጭራሽ አያደርገውም አንገቴን እሰጣለሁ እስላም ሆነ ክርስቲያን አረመኔ ይሁን ሃይማኖት አልባ በምንም መንገድ ሕፃናቶችን አስገድዶ አይተኛም። በርግጥ ሌላ አይነት ወንጀል ያደርግ ይሆናል እንደዚህ ያለውን ግን ሰምቼም አላውቅ።» ብላ በነገሩ ተንገፈገፈች። ንግግሯን ቀጥላ «መች የናንተ ጉድ በዚህ ያበቃል። አባት ከሴት ልጁ እናት ከወንድ ልጁ የወሲብ ማስገደድ ወንጀል ያለው እዚህ ነው። በለፀግን ትላላችሁ እንጂ በባህልና በሞራል ገና ደሃ ናችሁ። ሆሞና ሊዝቢያ የበዛበት እርኩስ ሀገር።

«ችግር ሆኖብኝ እንጂ እዚህ ያለሁት ሀገሬን በጣም እወዳለሁ። ባሕሉ ሥነ ምግባሩ የሕዝቡ ሞራል ያልተበላሸ እንደናንተ ያልጨቀየ ንጹህ ሕብረተሰብ ያለበት ሥፍራ ኢትዮጵያ ናት» ብላ ጮኸችበት።

ክላውዝ ጋዜጣውን ጨምድዶ እንደኳስ አድበልብሎ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በርሜል ውስጥ መጣል ስለታከተው እራሱን እየታዘበ ሜዳ ላይ ወርውሮ ጣለው። እራሱን ዞር አድርጐ እንደ ተልባ የሚንጣጣውን የሮዚን አፍ በከንፈሮቹ ከድኖ ሳማት። ጠቅሎ የወረወረው ጋዜጣ ንፋስ እያንከባለለ ወደ ባህሩ ከተተው። ሮዚና ክላውዝም ተቃቅፈው እየተሳሳሙ እንደ ጋዜጣው ተንከባለው ከጭቅጭቅ አውድማ ወደ ፍቅር ባሕር ውስጥ ሰጠሙ።

ከትንሽ ቆይታና ፋታ በኋላ ዓይን ለዓይን ተያይተው ታረቁ። የሮዚ ጭንቅላት የሕፃናቶችን መጠለፍ በወሲብ ተገዶ መደረግን አሰላስሎ እያሰበ ተመልሶ መጣባት። ቢቸግራት የሆነ ጥያቄ አቀረበችለት።

«ከአሁን በፊት ሴት አስገድደህ ታውቃለህ?» ክላውዝ ጥያቄውን ተቀብሎ እየሳቀ «እኔ ሳልሆን ሴቶች አስገድደውኝ የሆነ ወቅት አድርጌአለሁ።» «የናንተ ሴቶች አያደርጉም ብዬ አልከራከርም የሴትን ክብር የሚያስንቁ እፍረተ ቢሶች።» ክላውዝ «አንቺስ» ብሎ ጠየቃት።

«ምን?»

«ከአሁን በፊት ያስገደደሽ ሰው እንዳለ...ማለቴ ነው»

«እኔ ልጅቷ ቀሚስ ብለብስ ልቤ ወንድ ነው። በርግጥ የሞከረኝ አለ ግን በቀላሉ አልተበገርኩለትም» ብላ ወደ አስከፊ ትዝታ ውስጥ ገባች።

አዎ ከብረ ንጽሕናዋን ወዳ ያደረገችው ስለሆነ እንደማስገደድ አልቆጠረችውም። ያስከፋት ቢኖር ግን ሌላ ነው።

ገና ጀርመን እንደ መጣች ሰሞን «አገር አማን ነው ወዳጅና ዘመድ አለበት» ብላ የተማሩ በእድሜም የበሰሉ ትዳር መሥርተው ልጅ ወልደው የሳሙ ቤተሰብ ቤት ተጋብዛ ትሄዳለች። ሚስት እቃ ለመግዛት ትወጣለች ባል የሮዚን ቁንጅና እያደነቀ እንደ እባብ ተሰቦ ድንገት እላይዋ ላይ ወጥቶ ሶፋ ላይ አንቆ ይይዛታል። ሮዚ እንደ ምንም ተፈራግጣ እጆቿን በማስለቀቅ ፊቱን በጥፍሮቿ ቦጫጭራና ቧጣ ታደማዋለች። ባል ደንግጦ ይነሳል። የፊቱን ደም በፎጣ እያደራረቀ በሁኔታው ተጨነቀ። ሚስት ተመልሳ ትመጣለች። የባሏ ፊት ደማምቶ በማየቷ ደንግጣ «ምን ነካህ? ምን ሆንክ?» ብላ ትጠይቃለች። ባል ነገሩን ሸፋፍኖ «ይሄውልሽ አንቺ እንደ ወጣሽ የሆነ ጩኸት ሰምቼ በመስኮት ተመለከትኩ ሦስት ነጮች አንድን ጥቁር ይዘው ይደበድቡታል። እየሮጥኩ ሄጀ ስገላግል የደረሰብኝ ጉዳት ነው።» ብሎ አታለላት። ሚስት ያለውን አምና በሁኔታው አዘነች። ሮዚም «የሰው ትዳር በኔ ጦስ አይፈርስም» ብላ ነገሩን በሚሰጪር ይዛ ያሳለፈችውን መጥፎ ትዝታ አስታውሳ ለክላውዝ አጫወተችው።

ክላውዝ በደረሰባት ሁኔታ አዘነ። ይህ ሁኔታ ምናልባት በሮዚ የወሲብ ስሜት ላይ ትልቅ ጠባሳ ሳይጥል አይቀርም ብሎ ሠጋ። አልነካም ባይ ድፍረቷን ግን ወዶ ከልቡ አደነቃት።

ሆዳቸውን ትንሽ እርሃብ ስለሞረሞረው የገዙትን ሳንዱች ተከፋፍለው መብላት ጀመሩ። ድንገት ማዶ ባሕር ውስጥ ጩኸት ተሰማ። አንዲት ወጣት ኮረዳ ባሕር ውስጥ ገብታ ብቅ ጥልቅ ትላለች። ክላውዝ የገመጠውን ሳንድዊች ጥሎ እየሮጠ ልጅቷን ለማዳን ዘሎ ከባሕሩ ገባ። በተቀላጠፈ ሁኔታ ዋኝቶ ልጅቷን በቀኝ እጁ ደግፎ እየጮተተ ዳር አደረሳት። ሕዝቡ በአድራጐቱ አጨበጨበለት። ሮዚ በሁኔታው ተደስታ ኮራች።

ክላውዝ ልጅቱን እመሬት በጀርባቸ አጋድሞ፣ ማጅራቷን በእጆቹ ወደ ላይ ደግፎ ፊቷን ወደ ቀኝ አዘነበለ። አፏን ከአፉ ጋር አጋጥሞ ውሃውን እየመጠጠ ደጋግሞ በማድረግ አስወጣላት። ሮዚ አድራጐቱን አይታ ክላውዝን ተጠየፈች። የቅናት ዛር በልቧ ተቀጣጥሎ መጨስ ጀመረ። የወደቀችው ኮረዳ ቀስ በቀስ ትንፋሽ አግኝታ ከተኛችበት ተደግፋ ቀና ብላ ቁጭ አለች።

ክላውዝ ልጅቱን ለጓደኞቿ ትቶ እየሮጠ ወደ ሬዚ መጣ። ሮዚ «ሂድ! ሂድ! አትጠጋኝ» ብላ አመናጨቀችው። ክላውዝ በነገሩ ግራ ተጋባ።

«የማንንም ለሃጫም ፈረንጅ አፍህን ለጉመህ በሳምክበት እንዳት ነካኝ» ብላ ተመነቃቀረች። ክላውዝ እየሳቀ ሁኔታውን ለማስረዳት ሞከረ። ወዲያው አንቡላንስና የፖሊስ መኪና እየጮሁ ተከታትለው ባሀሩ አጠገብ ደረሱ።

ሮዚ ልብሷን ለባብሳ እቃዎቿን ሰብስባ ያዘች። ክላውዝ የአደጋውን ሁኔታ ለፖሊሶች ነግሮ በቶሎ ልብሱን ለባብሶ ሮዚን ማባበል ያዘ። በዘንቢል ቦርሳ ያለውን እቃ ተቀብሏት እመኪና ውስጥ አስገባ። ጀንበሯ ብትጠልቅም ጊዜው ገና አልመሸም። የሆነ መናፈሻ አብረው እንዲሄዱ ቢጋብዛት እንቢ አሻፈረኝ ብላ ቤቷ እንዲያደርሳት ተማጠነችው። እረኛሙን መንገድ ምንም ሳይነጋገሩ ተኳርፈው እቤት ደረሱ።

ክላውዝ ሮዚ የምትወደውን ሙዚቃ ከፍቶ ስሜቷ መለስ እንዲል ማባበል ጀመረ። በመሐሉ ስልክ ተደወለ። ሮዚ ስልኩን አንስታ «ሃሎ» አለች «ምነው ቀረሽ እየጠበቅሁሽ እኮ ነው» አለች ከማዶ ሆና ስልክ የደወለችው ፋጡማ። «ሶሪ ገና ከዋና መጥቼ መግባቴ ነው። ትንሽ አርፌ ሲመሻሽ እመጣለሁ አልቀርም።» አለቻት በተሰላቸና በደከመ ድምፅ።

«ምን ሆንሽ ምነው ድምፅሽ ደካከመ።»

«እየነገርኩሽ የፀሐይ ግለት ዋናው ተጨምሮ ሰውነት ያደክማል።»

«ብቻሺን ነው ወይስ ከሰው ጋር ነበር የሄድሽው?»

«አ! እንግዲህ እንደ ፖሊስ አትጨቅጭቂኝ በኋላ ስንገናኝ አጫውትሻለሁ» ብላ ስልኩን ዘጋችው። በመሐሉ ክላውዝ የቀዘቀዘ ሴክት ከፍቶ በትንሽ ብርጭቆዎች ለሮዚና ለእሱ ሞልቶ ቀዳ። «ለጤናችን» ብሎ የራሱን ብርጭቆ ከፍ አደረገ። ሮዚ አልጠጣም ብላ አኮረፈች። ክላውዝ ተለማምጦ ይቅርታ ጠይቆ በመጨረሻ ብርጭቆቸውን አጋጭተው ተጐነጩ።

አሁን የሮዚ መልክ ትንሽ ፈገግ። ከመጠጡ ፉት ብላ ሲጃራዋን ለኩሳ ተመቻችታ ተቀመጠች። ክላውዝ ጉሮሮውን በሳል ሞርዶ «የሚቀና ሰው አልወድም ትያለሽ ግን አንቺ በማይቀናበት ቀንተሽ ትናደጃለሽ።» ብሎ «እወድሻለሁ» ባይልም እሱ ለእሷ ያለውን ፍጹም ታማኝነትና ፍቅሩን በሚችለው ቋንቋ እየገለጠ አጫወታት።

ሮዚ – «እኔን ያናደደኝ አንተ እንደምትለው ቅናት አይደለም። የጤንነት ጉዳይ ነው። በአሁኑ ጊዜ መድኃኒት ያልተገኘላቸው ተላላፊ በሽታዎች እንዳሉ ታውቃለህ እንዴት የማታውቃትን ሴት አፍህን ካፏ

ጋር ለጉመህ ትስማታለህ? ከባሕር ውስጥ አወጣሃት ሌላው የራሳቸው ጉዳይ ነው። ሶሪ ክላውዝ እንዲህ ያለውን ቅጥ ያጣ አድራጉት አልደግፍም» ብላ የጐደለ ብርጭቆዋን አንስታ ጨለጠችው።

ክላውዝ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ኤድስ የተባለው በሽታ እንደማይተላለፍ ነገራት። ሮዚ «ይተላለፋል እንጂ» ብላ ተከራከረች እንዲገባውም ብላ ማስረጃ ሰጠችው። ምናልባት የተባለችው ሴት የጥርስ ሕመም ወይም ከንፈሯ የቆሰለ ሆኖ ቅድም ያደረከውን ብታረግ ከበሽታው ጨርሶ አትድንም። ለሁሉም እግዜር ያውጣን» ብላ ብርጭቋዋን ለእሷ ሞልታ ለክላውዝ ስትጨምር «በቃኝ መኪና እኮ ይዣለሁ» ከአንድ ብርጭቆ በላይ አይፈቀድም» ብሎ እንቢ አላት።

ጥርርርር! ጥርርርር! ስልኩ አሁንም ተደወለ። ፋጡማ ነበረች። ሮዚን እቤቷ እራት ጋብዛት ስለዘገየች አላስችል ብሏት በድጋሚ ሮዚ የቆየችበትን ምክንያት ጠየቀች።

«ፀጉሬን እየተሠራሁ ነው መጣሁ»

«እንዴ ፀጉርሽ እራስታ (ሹርቤ) አይደለም እንዴ ምኑ ነው የሚሠራው።»

«ሹርባም እኮ ቢሆን ውሃ ስለነካካው መስተካከል አለበት።»

«ሌላ ቀጠሮ አለሽ ወይንስ ለኔ ብለሽ ነው»

«ይቺ ደደብ ጀመራት ደግሞ» አለች በሆዷ።

«ሰው ንጽሕናውን የሚጠብቀው ለራሱ ነው። ሴት ልጅ በተለይ የትም ትውጣ የት አምራ መገኘት አለባት። መጣሁ» ብላ ስልኩን ዘጋችው። ድጋሚ ሲጋራ ለኩሳ እያጨሰች ፋጡማን ማማት ጀመረች።

አዎ ፋጡማ ዑስማን ቱርክ ሀገር ብትወለድም ያደገችው ጀርመን ነው። ቋንቋውን በደንብ ትናገራለች አጠር ደልደል ያለች እድሜዋ ወደ ሠላሳው የሚጠጋ ወጣት ነች። ፊቷ ክብ ሆኖ ሁሌ መቀለድና መሳቅ ታበዛለች። የፀጉሯ አበጣጠር ዘወትር አይለወጥም። ቢሆንም ያምርባታል። እንደሌላ ቱርኮች ፀጉርና ፊቷን በሻሽ መሸፈን ጨርሶ አትወድም። ዓይኖቿ ደፍረስ ብለው ጐላ ጐላ ያሉ ናቸው። ከንፈሮቿ አበጥ ብለው ሳሙኝ ብለው ያስጐመጃሉ። ትንንሽ ጡቶቿ እንደ ሮዚ አልፈረጠሙም። ከኋላ በኩል ያለው መቀመጫዋ ደበልበል ፈርጠምጠም ብሎ ፈንዳሳ አስመስሏታል።

ሽንቧ ቀጠን ዳሌዋ ሰፋ ያሉ ናቸው። ጣቶቿ አጫጭር ሆነው ጉልድምድም ያሉ ስለሆነ እንብዛም አያምሩም።

ፋጡማ ስትሄድ ትፈጥናለች ኩስ ኩስ ድክ ድክ ማለት ታበዛለች። አነጋገሯም እንደ አካሄዷ ይፈጥናል። ውሳኔ ለመስጠት ቆራጥ ነች። ጠባይዋም እስከዚህ አይከፋም ከሁሉ ትግባባለች ቂም አትይዝም። ግን ቀናተኛ ናት። ወሬና ሀሜት ትወዳለች። ልቧ ቅን በመሆኑ ግልጽነትና ደግነት አለባት። የራሷንም ገመና ነውርና ወሲብ እንኳን ለሌላው ሳትደብቅ ለሁሉም ታወራለች። በዚህም አንዳንድ ሰዎች ይንቋታል። በተለይ ሮዚ «ለአፍሽ ጋት ይኑረው» ብላ ብትመክራትም ልማዷን አልተወችም። ሌላው ቀርቶ ያወቧትን ወንዶች እንኳን ሳትደብቅ ታወራለች ያንንም ያንንም ለመያዝ ትከጅላለች። እስካሁን ግን ጠበቅ አርጋ የያዘችው ጓደኛ የላትም። በልቧ ግን የሮዚን ክላውዝ ትወደዋለች። ፋጡማ ጥሩ መኖሪያ ቤት አዲስ ማርቼዲስ መኪና አላት። በእረፍት ጊዜዋ እቤት መቀመጥ አትወድም። ዛሬ ግን ሮዚን ስለጋበዘቻት ከቤቷ አልወጣችም።

ሮዚ ልብስ ቀያይራና ተኳኩላ ክላውዝ የሸለማትን ሐብል አጥልቃ የምትወደውን ሽቶ ተቀባብታ ጨረሰች። የግል መኪናዋ ቢኖርም መጠጥ ስለጠጣች ክላውዝን «በል ተነስ አድርሰኝ» ብላ ተጣደፈች። ክላውዝ እንደ ሹፌር ታዞ ሮዚን ወስዶ ፋጡማ ደጃፍ አደረሳት። የመሰነባበቻ ሰላምታ ለመስጠት አፉን ወደ ሮዚ አስጠጋ። ሮዚ አገጩን ይዛ ሳትስመው ዞር በማድረግ «ቻው!» ብላ ከመኪናው ወረደች። ክላውዝ «መልካም ምሽት» ብሎ ሳየመኝላት ወደ ቤቱ ብቻውን ፈረጠጠ።

ሮዚ ፋጡማ በራፍ ላይ የተለጠፈውን ዑስማን የሚለውን የአባቷን ስም ተጭና ሁለቴ ደወለች። በሩ አልተከፈተም። ፋጡማ ቀኑን ሙሉ ቤቱን ብታፀዳውም ደውሉን ሰምታ ምናልባት የዘነጋችው ጠያፍ ነገር እንዳለ ተመለከተች። የመተርኮሻ አመዱን ዘርግፋ በሩን ከፈተችላት። ሁለቱ በፈገግታ ተገናኝተው ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ።

እለቱ የሳምንቱ መሐል አረቡ በመሆኑ የታክሲ ገበያ እንደ አርብና ቅዳሜ ሆኖ አልደራም። ፈርፈልድ የታክሲዎች መቆሚያ ብዙ መኪናዎች ተደርድረው ተራቸውን ይጠብቃሉ።

ሙራት ጆኒ መኪና ውስጥ ሆኖ አብረው ተራ እየጠበቁ የቆጥ የባጡን ያወራሉ። ሙራት የሮዚን ነገር አንስቶ ለእሷ ያለውን ፍቅርና አክብሮት እየዘረዘረ ያጫውተዋል። ጆኒ ነገሩን አዳምጦ ፍቅር ያላቻ ዘላቂነት እንደ ሌለው በዘዴ መክሮ አጽናናው። ውይይታቸው የሮዚን ጉዳይ አልፎ ሙራት ባለፈው ሳምንት ያጋጠመውን ምስጢር ለጆኒ ሳይደብቅ አጫወተው።

ነገሩ እንዲህ ነው «አንዲት ጥቁር ሴት ሀንቡርግ ለመሄድ ባቡር አምልጧት ስለቸኮለች እንዳጋጣሚ ሙራት ታክሲ ውስጥ ትገባለች። በኮንትራት ዋጋ ተስማምተው ጉዞ ከጀመሩ በኋላ ሙራት ማርሽ እንደሚቀይር አድርጉ የልጅቷን ታፋ ይዳስሳል ልጅቷ ነገሩ ስለገባት ሥራዋም የቡና ቤት አሻሻጭ በመሆኑ በገንዘብ ተስማምተው ያደረጉትን እርካሽ የወሲብ ግንኙነት ነበር። እንደ ትልቅ ጀብዱ ያወራለት።

ጆኒ በፋንክ ተጠርቶ የሆነ በር ማለት የታክሲ አገልግሎት እንዲሰጥ ታዘዘ። የተባለው ቦታ ደርሶ የበሩን ደወል ደውሎ በራፉ ላይ የተኛችውን ድመት ሳይነካ መኪና ውስጥ ተመልሶ ገባ።

አንዲት ቆንጅዬ ልጅ ጥቁር ጅንስ እንብርት የሚያሳይ አጭር ቢጫ ካኒቴራ ለብሳ ብቅ አለች። ጉትቻ አንባር ቀለበትና ሰዓት ጮርሶ የላትም። ከቤቷ እንደ ወጣች ደጅ የተኛችውን ድመት በእጆቿ ዳሰስ ዳሰስ አደረገቻት። ድመቷ ተነስታ ወገቧን ወደ ላይ በመወጠር ተንጠራራች። ወጣቷ ኮረዳ የመኪናውን በር ከፍታ ሰላም በማለት ጆኒ ጐን ተቀመጠች። የተቀባችው ሽቶ አፍንጫውን አወደው። የምትሄድበትን ቦታ ጠይቆ የመኪናውን ሞተር አስነሳ። ያው እንደ ተለመደው ወሬ ለመጀመር ያህል «ድመቷ የእርሶ ናት?» አለ «አይ የጐረቤት ናት» ዳግም እባክህን እርሶ አትበለኝ አልወድም» አለችው «ታዲያ ለምን እቤት አትገባም?» «መናፈስ ፈልጋ ነው እንዴት ያለች ጠባየ ሽጋ ፍቅር የተሞላባት ድመት መሰለችህ እኔ በጣም ነው የምወዳት» አለችው።

ጆኒ የድመት ፍቅርና ጠባይ ጨርሶ አይገባውም። ውሻ እንኳን ጭራውን ሲቆላ ፍቅሩን ጥርሱን አግጦ መሬት እየጫረ ሲጮህ ጥላቻውን ማወቅ ይቻላል። ግን የድመት ምኑ ይታወቃል ብሎ በነገሩ ተገረመ።

ቀጠል አድርጉ «የተቀባሽው ሽቶ ደስ ይላል ግን የሚሉት ነው?» «ሰንፍላወር» አለችው «ግሩም» ብሎ ዝም አለ። ጆኒ ስለሽቶ ጥሩ መአዛ

እንጂ የስም መጠሪያና የዋጋዎችን መጠን እንብዛም አያውቅ። ሮዚ ግን በዚህ የሰለጠነች ነች።

ተሳፋሪዋ ኮረዳ ጆኒ የሰጣትን ቀና አስተያየት ሽጋማ በመሆኑ ይሁን ወይም በሌላ እንደ ወትሮ ተሳፋሪዎች ስሙን ወይም የመጣበትን ሀገር ሳትጠይቅ «ይቅርታ አድርግልኝና ኮከብህ ምንድን ነው?» አለችው ጆኒ ትንሽ ደንገጥ ብሎ አያት። ይሄን የመሰለ ጥያቄ የሚጠይቁት አልፎ አልፎ አንዳንድ ያረጁ ባልቴቶች ሲሆኑ ከወጣቷ ያልጠበቀው ቢሆንም ፈገግ ብሎ ሰፊሊንግ ማለት ጂሚኒ ነኝ» አላት። «አዎ ጅሚኒዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው። ብቻ ባሉበት አይረጉም ሁለት ገፅታ በአንድ ፊት አላቸው» «አንቺስ» አላት «ሹትስ ማለት ካፕሪኮርን ነኝ» «አለቃዬ የሮላንድ የታክሲ ድርጅት ኃላፊ ያንቺን አይነት ኮከብ ነው ያላቸው ሥራ ወዳድ በጣም ሀብታም ናቸው።»

«ሥራስ እኔም እወዳለሁ ግን እንዳለቃህ ሀብታም አይደለሁም።»

«ገና ልጅ ነሽ እድሜ ከሰጠሽና ሥራ ከወደድሽ ሀብታም እንደምትሆኚ ጥርጥር የለውም።» ብሎ አስደሰታት። ቀጥላ «ስንት ሰዓት ነው?» ብላ ጠየቀችው ነገራት። ፍጥነቱን ጨምሮ እየነዳ ለምን ሰዓት አንባር ጉትቻና ሐብል እንደሌላት እንደ ቀልድ አርጉ ጠየቃት «ለእንደዚህ ዓይነት ጌጣ ጌጦች አለርጂ አለብኝ» አለችው።

ጆኒ በልቡ «አንቺን ያገባ ታደለ ገንዘቡን ቆጠበ» ብሎ ቅር እንዳይላት «አይ ባታጌጪም ታምሪያለሽ» ብሎ ያለችው ቦታ አደረሳት።

ሮዚ ከፋጡማ ጋር ያላት ወዳጅነት እረኸም ጊዜ ቢሆንም መኖሪያ ቤቷ ስትመጣ ገና የመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

ታኮ ጫማዋን አውልቃ ሳሎን ልትገባ ስትል ፋጡማ «እባክሽን ኢታውልቂው የቤቱ ምንጣፍ ያረጀ ነው። እንዲሁ ግቢ» ብላ ለመነቻት። ሮዚ ግን እግሮቿ ስለሞቁ ቀለል እንዲላት አወላልቃ በራፉ አጠገብ አስቀምጣው ገባች። ለፋጡማም ይዛላት የመጣችውን የማርቲኒ ኮኛክ ሰጠቻት።

ፋጡማ ኮኛኩን አመስግና ተቀበለች። ሮዚን አረፍ በይ እንኳን ሳትላት ቤቷን ማስጐብኘት ጀመረች። በሳሎኑ ወለል ላይ ትልቅ የአበባ ምንጣፍ ተነጥፏል ክብ የመስታወት ጠረጴዛ መሐሉ ላይ ሰፍሯል።

የሳሎኑን ግርማ የሰጠው የግራውን ግድግዳ ከዳር እስከ ዳር የያዘው የቡፌ መደርደሪያ ቁም ሳጥን ነው። የውስጡ ማብራት በርቶ የተቀመጡትን ልዩ ብርጭቆዎችና ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጦች አንፀባርቆ ያሳያል። በቀኝ በኩል ቴሌቪዥንና ቪዲዎ ከሙዚቃ ማዘፈኛ ዲክ ጋር አብረው በሥርዓት ተቀምጠዋል። ፎቴዎቹ የተዝጎረጎረ መልክ ያላቸው ሲቀመጡባቸው ሽሙክ ሽሙክ ብለው ይደላሉ። ሳሎኑ ሰፊ ቢሆንም እቃ ስለበዛበት የጠበበ ይመስላል።

ሁለቱም ከዚህኛው ክፍል ወጥተው ሌላ ክፍል ገቡ የፋጡማ ቤት በአጠቃላይ አንድ ሳሎን ሁለት መኝታ ቤት፣ አንድ መታጠቢያና ኪችን በስተጀርባ ጠባብ ባልኮን ያለው ነው። አሁን የገቡበት ክፍል አንድ ከመዲናና ጠባብ አልጋ አለው። የክፍሉ ቀለም ሮዝ ቢሆንም ስላረጀ ደብዘዝ ብሏል። በአንድ በኩል ባለው ግርግዳ የመካ መዲና ሥዕልና የአንዲት አሮጊት ፎተግራፍ ተሰጥቷል።

ፋጡማ «ይሄ ክፍል የናቴ መኝታ ቤት ነበር ያው እንደ ነገርኩሽ በክሬብስ በሽታ ታማ ሞተች። ቤቱን እኔ ወሰድኩት። ማለቴ ውርስ ሳይሆን ያው የኪራይ ልውውጥ ነው። ታዲያ ሌላውን ክፍል ሳሳድስ ይሄኛውን ክፍል እንዳለ ትቸዋለሁ ቀለሙን እናቴ ስለምትወደው ለመንፈሷ ብዬ ነው። ግን ክፍሉን አንዳንዴ እንግዳ ሲመጣብኝ እጠቀምበታለሁ።» ብላት ክፍሉን ዘግተው ወጡ።

«ይሄኛው ደግሞ የኔ መኝታ ቤት ነው» አለቻት ሰፊ የፈረንሳይ ክብ አልጋ ነው። በደንብ ተነጥፎ የቱርክ ስስ የአበባ ያልጋ ልብስ ተከናንቦ ለዓይን ይማርካል። አጠገቡ በቁም መስተዋት የተያያዘች ኮመዲኒ አለች። እላይዋ ላይ የመቀስቀሻ ሰዓትና ቀለማቸው የተለያዩ ሦስት ኮንዶሞች ተቀምጠዋል። ፋጡማ ሮዚ ሳታያት ሮጥ ብላ ወደ ውስጥ ከተተቻቸው።

ሮዚ ፈንጠር ብላ ከዳር እስከ ዳር በመስታወት መዝግያ የተሠራው ቁም ሳጥን ፊት ለፊት ቆማለች። እቃውን ሳይሆን የሷን ቁመና በመስታወት ውስጥ ተመለከተች። ፋጡማ ሽር አርጋ ወደ ጐን በመክፈት ያላትን ልዩ ልዩ ልብሶች አሳየቻት። ሮዚ ጉረኛ መሆኗን አውቃ «እንዴ ይሄ ሁሉ ልብስ እያለሽ ለምንድነው ሁሌ ሱሪ አንድ አይነት ልብስ የምትለብሽው?»

«ሥራ ነዋ እኔ ለሥራ የሚመቸኝ ቀለል ያለ እንደዚህ ሸሚዝና ሱሪ ነው። ቀሚስ ስለብስ አሮጊት ስለሚያስመስለኝ እንብዛም አልጠቀምበትም» ብላ መልሳ ዘጋችው። ከዛም ማድቤቱን (ኪችኑን) መፀዳጃ ክፍሉንና በረንዳ (ባልኮኑን) አሳየቻት። ሮዚ ጥሩ የመኖሪያ ቤት እንዳላት ነግራት የእቃ አቀማመጡንና ንጽሕናውን ጨምር አድንቃ ተያይዘው ሳሎን ገቡ።

ፋጡማ ሰው ማስተናገድ ትችልበታለች። «በይ እንግዲህ እርዝዙ የምትጠጭውን ንገሪኝ ምን ላምጣልሽ? ወይስ ያመጣሽውን ኮኛክ ልክፈተው? ምን ላቅርብልሽ?»

«አይ እሱ በኋላ ይሆናል አሁን ስለጠማኝ ቀዝቃዛ ቢራ ካለሽ ብትሰጭኝ ጡሩ ነው»

ፋጡማ ፈገግ ብላ «ቤክስ (Beck's) ቢራ አለኝ» አለች። እንደ ባለሙያ ሴት ጥሩ ጠላ ጠምቃ ያቀረበች ይመስል ትከሻዋን በኩራት እየነቀነቀች። በእርግጥ ቤክስ በዓለም የታወቀ ብሬመን ከተማ የሚጠመቅ ቢራ ነው። ፋጡማ ቢራውን ከፍታ በብርጭቆ ለእሷም ለሮዚም ሞልታ ብርጭቆአቸውን አጋጭተው «ለፍቅራችን!» ብለው ተጐነጩ። ሲጃራቸውን ሁለቱም ለኩሰው እያጨሱ የቆጥ የባጡን መቀበጣጠር ጀመሩ።

ሮዚ ቀን የዋለችበትን የዋና ቦታ ወሬ የክላውዝን ስም ሳትጠቅስ አጫወተቻት። ፋጡማ ነገሩን በመጠራጠር «ውነት ሮዚ ብቻሽን ነው እንዲህ ያለ ቦታ የምትሄጂው ፈጽሞ አላምንም»

«ደስ ይበልሽ ከድሮ ጓደኛዬ ጋር ነበርኩ።»

«ማነው የድሮ ጓደኛሽ»

«አታውቂውም ምን ያደርግልሻል»

«ውይ ሮዚ ምሥጢር ስትደብቂ እኔ እንኳን የቅርብ ጓደኛዬ ሳልሆንሽ ብዙ ነገሮች አጫውቼሻለሁ ያንቺ ልብ ግን ድፍን ነው።»

«አየሽ ፋጡማ ምሥጢር የባቄላ ወፍጮ መሆን የለበትም።»

«ምን ማለትሽ ነው አልገባኝም»

«አንቺማ ምሥጢሩንም ምኑንም አታውቂው ገመናሽን ዘክዝከሽ ነው የምታወሪው»

«ምን ላርግ ብለሽ ነው ሮዚ ተፈጥሮዬ ነው እኔ ድብብቆሽ አላውቅም በተለይ ለወደድኩት የልቤን ነው ገልጬ የምነግረው።»

«ይጉዳሻል ለአፍ ለከተ ያስፈልገዋል» ብላ ሳየታወቃት ሐብሏን በእጇ ነካካች።

«ውይ ደስ የሚል ሐብል ማነው የሸለመሽ?»

«ማንም እኔ አልገዛም እንዴ»

«ምነው ቆጣ ቆጣ አደረገሽ ሮዚ» የጋበዝኩሽ እኮ አንቺን ላስቆጣ ሳይሆን አብረን እየሳቅን እንድንጫወት ነው። አስቀይሜሽ እንደሆን ይቅርታ» ብላ የቱርክ ሙዚቃ ከፈተች። የሮዚንም የቁጣ መንፈስ ለመለወጥ የቱርኮችን የሆድ ዳንስ ቆማ እየተንጐራደደች አሳየቻት። ሮዚ ከት ብላ ስቃ እሷም ተነስታ አብራ ደነሰች።

እንዲያበላላቸው ኮኛኩ ተከፍቶ ደጋግመው ተጐነጩ። ፋጡማ ያዘጋጀቻቸውን የበግ አሮስቶ ከሰላጣ ጋር አምጥታ ጣፍጧቸው እየተጐራረሱ በልተው ጨረሱ። መአድ ተነስቶ ኮኛኩ ተደግሞ ሲጃራ ማጨስ ተጀመረ። ሁለቱም ትንሽ ሞቅ ስላላቸው በሆነው ባልሆነው መሳሳቅ አበዙ። ሮዚ ግን የቱርክ ሙዚቃውን ስላልወደደችው ፋጡማን ይቅርታ ጠይቃ ተለወጠ። የዘፈኑን ጥላቻ ምክንያት ብትጠይቃት «ያንን ሙራትን ስለሚያስታውሳኝ ብቻ ነው። ያኔ እሱ መኪና ውስጥ ሲሆን የሚያስለቅስ የሀገሩን ካሴት አድርጐ አብሮ ይዘፍን ነበር»

«እሱማ አሁንም ናላው ባንቺ ፍቅር ነው ዚል።»

«እንኳን ናላው እራሱም ድብን ቢል ግድ የለኝም»

«ወይ ወይ ሞቱንስ አልመኝም። እንዳው ጥሎበት ነው እንጂ እንዴት ደግ ሰው መሰለሽ»

«በናትሽ ወሬ ቀይሪ ስለእሱ መስማት አልፈልግም»

«በቀደም አግኝቼው ሮዚ እኮ ሱዚ ናት የኔ ማር ወለላ እያለ እንደሴት ያለቅስ ነበር።»

«ምንድነው ሱዚ?»

«ጣፋጭ ስኳር ማር ማለቱ ነዋ»

«እዛ ሄዶ ቤቱ የተዘፈዘፈችውን አሮጊት ሚስቱን ያሞግስ ሁለተኛ የኔን ስም እንዳያነሳ ንገሪው።»

ፋጡማ አሁንም ኮኛኩን ለሁለታቸውም ደግማ እየሞላች «እባክሽን ሮዚ ፍቅር ሲይዝ አይጣል ነው። የምታረጊውን አታውቂም ያሳብዳል።» ብላ በልጅነቷ የደረሰባትን የፍቅር ታሪክ አጫወተቻት።

«የሴትነት ክብሬን የሰጠሁት ቱርክ ሀገር ቤት እንዳለሁ አንድ እዚህ ግባ የማይሉት ውርጋጥ ወድጄ ነው። የመጀመሪያ ፍቅር ስለሆነ ነው መሰለኝ ይገርምሻል አለሱ ሌላ ሰው ጨርሶ ማየት አቃተኝ። እህል መብላት ቀርቶ ውሃ መጠጣት ተሳነኝ። እንቅልፍ አጣሁ። ሰውነቴ በሀሳብ መነመነ። ወጣቱ የደሃ ቤተሰብ ስለሆነ ወላጆቼ አልወደዱትም። እኔ ከነሱ ፍቃድ ወጥቼ አሻፈረኝ ብዬ በድብቅ ጥብቅ አልኩበት። ይገርምሻል ያም ሆኖ ኮራብኝ። በፍቅር ላይ እልህ ተጨምሮ አንገበገበኝ። «ራሴን እገላለሁ» ብዬ ስሞክር አባብሎ የሆነ ቦታ ወስዶ፣ የሴትነት ክብሬን ገረሠው። ከዛ አብረን መውጣት ጀመርን ደግነቱ አላረገዝኩም በመጨረሻ ሳንጋባ ፍቅራችን አለቀ። አንቺስ ፍቅር ይዞሽ አያውቅም?» አለቻት ሮዚን ሲጋራዋን ለኩሳ በጭሱ መሐል እያየቻት።

ሮዚ ኮኛኳን ፉት ብላ ትንሽ ማሰብ ጀመረች። ያገር ቤቱን የልጅነት የፍቅር ታሪክ የክብርናዋን መገሥ አሁን አንስታ መጫወት አልፈለገችም ያው ጀርመን ከመጣች በኋላ ያጋጠማትን ባጭር ባጭሩ ነገረቻት።

«ይሄውለሽ ፋጡማ እዚህ ከመጣሁ በመጀመሪያ በያዝኩት ጓደኛ ጥቁር አሜሪካዊ የጦር መኮንን (አፊሰር) ነበር። ገና ያላገባ ወጣት ነው። ቁመናው ለሴት ያለው አመለካከትና አክብሮት አስደሰተኝ ተዋወቅሁት። በመጨረሻ ተስማምተን አብረን መኖር ጀመርን። «ፍቅር ያዘኝ። ሥራ ውሎ እስከሚመለስ ይናፍቀኛል። አንዳንዴ ቤት ውስጥ ምንም ሳልሠራ ፈዝዤ ያገኘኛል። ስሜቴን በመረዳት እንደ ሕፃን ልጅ አባብሎ እንደ ጓደኛው አክብሮ አብረን ሦስት ዓመት ተቀመጥን። በመጨረሻ ወደ አሜሪካን ተቀይሮ ሄደ።»

«አንቺን ጥሎ?»

«ምን ያድርግ ብለሽ ነው? የወታደር ግዴታው ሆኖበት እኔን ይዞ ለመሄድ አልቻለም። ተለያየን። ግን አሁንም እወደዋለሁ።»

«በደብዳቤ ወይም በስልክ ትገናኛላችሁ?»

«ነገሩ እኮ የቆየ ነው ፊት ነበር አሁን የት እንዳለ አላውቅም አረስቼዋለሁ።» ብላ ሲጋራዋን ለኩሳ ለጥቂት በትዝታ ተከዘች።

«አንቺስ እዚህ ጀርመን ከመጣሽ ምን አጋጠመሽ?» አለቻት ፋጡማን።

«እዚህ እንደ መጣሁ ከሆነ ጀርመን ጋር ተዋውቄ አብሬ መውጣት ጀመርኩ። ወደድኩት ቤቱን ትቶ ከኔ ጋር መኖር ጀመረ። ይገርምሻል ሮዚ ድሮ ቱርክ ሳለሁ ፈረንጆች በወሲብ ሥራ ደካማ ናቸው ሲሉ እሰማ ነበር። ውሸት ነው። እንዴት ጐበዝ መሰሉሽ...»

«እንዴ አንቺ ከስንት ሰው ወጥተሽ ነው ይህን ልትይ የምትችይው።»

«ይሄው ከዚሁ ካልኩሽ ሰውዬ ጋር ነዋ።»

እሱ ጐበዝ ከሆነ ሁሉም አይምሰልሽ ብቻ ይቅርታ ወሬውን ጨርሽልኝ።

«እውነት ለመናገር እሱንም ሌላም አውጥቻለሁ እስካሁን ያጋጠሙኝ ጐበዞች ናቸው። ግን የመጀመሪያዬ የሚያደርገው የወሲብ የቅድሚያ መተሻሸት ጫወታ ተወዳዳሪ የለውም።»

«ምን ማለትሽ ነው?»

«ይገርምሻል ሮዚ፣ በአንድ ለሊት ከእሱ ጋር ከሆንኩ አምስት ጊዜ ስሜቴን እጨርሳለሁ።»

«አምስት ጊዜ አትዋሺ ፋጡማ።»

«ወላሂን ዑስማን ይሙት» እያልኩሽ።

«የምትገርሚ ፍጡር ነሽ እኔ ለአንዱም በግድ ነው» ብላ ደፍራ የማታወራውን የወሲብ ወሬ በኮኛኩ ምክንያት የስሜቷን እውነት ተናገረች።

ፋጡማ ኮኛኩን ሞልታ እየተጐነጨች የጀመረችውን ጫወታ ቀጠለች።

«ታዲያ ያልኩሽ ሰውዬ መወደዱን ሲያውቅ መኩራት ጀመረ። ፊቱን አዙሮ መተኛት በእልህ በላዩ ላይ ሌላ አወጣሁ። ብሎ ልም ብሎ በቅናት ነደደ። አላስገባ አላስወጣ አለኝ። «አንዴ ባሌ እኮ አይደለህም ብለው «አብረን ከኖርን ምን ቦታ አለው» ብሎ ሲውል ሲያድር እየጠጣ

መደባደብ ጀመረልሽ እኔ ለጅቷ «ውጣልኝ» ብዬ ፖሊስ ጠርቼ ሻንጣውን አሸክሜ አባረርኩት።» ብላ እየፎከረች ዱብ ዱብ ብላ ኪችን ገብታ ፍራፍሬና ኬክ፣ ይዛ መጣች። ሮዚ ስካሩን እንዲያበርድላት አስባ አንዱን ሙዝ ልጣ በላች። ፋጡማ መስኮቱን ከፍታ ሙዚቃውን ቀይራ ተመልሳ ፎቱው ላይ ዝርፍጥ ብላ ተመቻችታ ተቀመጠች። የመጠጥ ልምድ ስላላት ሞቅታው እንደ ሮዚ አልበረታባትም። ሲጋራዋን ለኩሳ የወሬ ብልት ጥሟት «አንቺስ ከጥቁሩ አሜሪካ ሌላ ያወጣሽው ጓደኛ የለም?» «አሉ ግን እድሌ ሆኖ አብረን መኖር አልቻልንም። ከአሜሪካኑ ቀጥዬ ያወጣሁት ጓደኛ ጀርመናዊ ነው። ያኔ የምኖረው ማቴልዲን ከሚባል ጐዳና እከተማው አካባቢ ነበር። ብዙ ጊዜ ከቤት አልወጣም የሆነ ቀን ሲጀራ አልቆብኝ ፈራንክ መንዝሬ ከአውቶማቲክ ለመግዛት የሆነ ትንሽ ምግብ ቤት ጐራ አልኩኝ። አንድ አሞር ወፍራም ጀርመናዊ በፈገግታ ተቀብሎ አነጋገረኝ። በኋላ ሳውቅ የንግዱ ቤት ባለቤት ነው። የጠየቅሁትን አድርጐ የምጠጣውንም ጋብዞ አድራሻ ተለዋውጠን ተለያየን። በሦስተኛው ቀን እራት ጋብዞኝ አብረን አመሸን። ሀብታም ቢሆንም ገና አላገባም። ከአንድ ወር በኋላ አብረን ወጣን። ሲውል ሲያድር ይገርምሻል እየወደድኩት መጣሁ ቤቴን ትቼ ከእሱ ጋር መኖር ጀመርኩ። ፍቅራችን ጦፎ ከዘመዶቹ ሁሉ በይፋ አስተዋወቀኝ አባቱ ግን ዘረኛ ናቸው። ሲያዩኝ በመጥቆሬ ይሁን በሌላ ፊታቸው አልተፈታም። ይገርምሻል የናጠጡ ሀብታም ናቸው አዲሱ ከተማ መደዳ የክስሚትክ የልዩ ልዩ ሽቀጥ መደብር የሳቸው ነው። ግን ምን ያደርጋል ከልጃቸው ለጋብቻ ብንስማማም ፍቃደኛ አልሆኑም። አሱም ውርስ እንዳይቀርበት ፊርቶ ተለያየን። አሁን ያለው ስፔን ሀገር ነው። ፊት ፊት ሰሞን እንደዋወል ነበር። ነገሩ «ዓይን ካላየ ልብ ይርቃል» ሆነና ተረሳሳን። ግን ይገርምሻል ፋጡማ አሁንም እወደዋለሁ።»

ፋጡማ «ያንቺ መውደድ በርከትከት አለብኝ አንዱን ያዥው እንጂ ሮዚ»

«አየሽ ፋጡማ ማፍቀር አንድ ነው መውደድ ግን ሊበዛ ይችላል» አለቻት። የሁሉም ወዳጆቼ ደግነትና ውለታቸው እየታወሳት መውደዷ አፋዊ ሳይሆን ልባዊ መሆኑን እየገለጸች።

«እኔስ ምንም ቢያደርጉልኝ በወሲብ በኩል ካልተጣጣምን ሰውን ጨርሶ አልወድም።»

«እንዴ ምን ማለትሽ ነው ፋጡማ የሰዎች ሥነ ምግባር ጥሩ ግንኙነትና መተሳሰብ ከሁሉም ይበልጣል።»

«አየሽ ሮዚ ወሲብ የፍቅር መሠረት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ካልተስማማኝ ሌላው ትርፍ ነው።»

ሮዚ የፋጡማ አነጋገር ባይጥማትም ልትከራከራት አልፈለገችም። ግን ሁኔታዋን ለወሲብ ያላትን ቅብጥብጥነት በአንድ ለሊት አምስቴ ስሜቷን መጨረስ ገርሟት የእሷ የወሲብ ስሜት የቀዘቀዘው በሴቶች ግርዛት ምክንያት ስለመሰላት ሰግታ፣

«እናንተ የቱርክ ሴቶች አትገረዙም እንዴ?» ብላ ጠየቀቻት። ፋጡማ ግራ ገብቷት «ምንድነው ግርዛት?» አለቻት። ሁኔታውን በትክክል ለማስረዳት ፈልጋ «የሴቶች እንቡጥ አበባ ከትባት» አለቻት እየፈራች።

«የምትይው ጨርሶ አልገባኝም» ሮዚ ጥቂት አሰብ አድርጋ ዲክሺነሪ ካለሽ አምጭልኝ ብላ ሰጠቻት። «ክሌቶርን የሚለውን ቃል አውጥታ አሳየቻት።» ፋጡማ ከት ብላ ስቃ ቀሚሷን ገልባ ለሮዚ አለመገረዟን ለማሳየት ሞከረች። ሮዚ ከመቀመጫዋ ደንግጣ ብድግ አለች። «አንቺ እፍረተ ቢስ ምን አይነት ጉድ ነሽ ሮዚ በመሐከላችን ወንድ የለ ሁለታችን ገላችንን በግልጽ ብንተያይ ምን የሚያሳፍር ነገር አለበት?» ተባብለው፣

ሁለቱም ተያይዘው ትንሿ ባልኮን ላይ ወጥተው ቆሙ። የምሽቱ አየር የቀዘቀዘ ስለ ነበር የኮኛክ ሞቅታቸውን አራገበላቸው። ሰማዩ ጠቁሮ ግማሽ ጨረቃ ከማዶ ትብለጨለጫለች።

ድንገት የቤቷ ስልክ ተደወለ። ፋጡማ ዘላ ሳሎን ገብታ ስልኩን አነሳችው። የደወለላት የምታውቀው የታክሲ ደንበኛዋ ነበር።

«ዛሬ ትሠሪያለሽ ብዬ ሴንተራል ብደውል አለመሥራትሽን ነገሩኝ። ታዲያስ እረፍት እንዴት ያደርግሻል?»

«ደህና ነው። ከአንዲት የሴት ጓደኛዬ ጋር ሆነን እየተጨዋወትን ነው።»

«አ! ሴትና ሴት ምናልባት የወንድ አጫዋች ካስፈለገ እመጣለሁ።»

«አያስፈልግም ይቅርታ ቻው!» ብላ ስልኩን ዘጋችው። ሮዚ ከባልኮን መጸዳጃ ክፍል ገብታ ፊቷን በቀዝቃዛ ውሃ ታጥባ ተመልሳ ቁጭ አለች። «ማነው የደወለልሽ? ብላም አልጠየቀቻትም። ፋጡማ እራሷ በራሷ ስለደወለላት የታክሲ ደንበኛዋ መሆኑን ገልጻ ከአሁን በፊት ከዚህ ሰው የደረሰባትን አጋጣሚ አጫወተቻት።

«ይሄውልሽ ሮዚ ይሄ ሰው ባለትዳር የልጆች አባት ደንበኛዬ ነው ግን በሚስጢር ያዥው ብዙ ጊዜ በሴንተራል እያስጠራኝ ከሚስቱ ጋር አመላልሼዋለሁ። እንዳውም አንዴ ቤታቸው ጋብዘውኛል። የሆነ ቀን እቤቱ አስጠርቶ ሄድኩኝ።» የታክሲው ሂሳብ ለኩሰች እቤት ግቢ ገና አልተዘጋጀሁም» አለኝ። ለኩሼ ገባሁ።

የምጠጣውን አቅርቦ በደንብ አስተናገደኝ ሚስቱና ልጆቹ እቤት ስላልነበሩ ብጠይቀው «ይመጣሉ ጐረቤት ናቸው» ብሎ የሆነ የፓርኖ ቪዲዎ ከፍቶ ሻወር ለማድረግ መታጠቢያ ክፍል ገባ።

ሮዚ–ንግግሯን አቋርጣ «መቼም ቁጭ ብዬ ጠበቅሁት እንዳትይኝ»

«ምን ችገረኝ የታክሲው ሂሳብ ይቆጥር የለ።»

«ገንዘቡን አይደለም ማየት ክብርሽን ነው።»

«የታክሲ ሹፌር ሆነሽ የምን ክብር ነው የምታወሪው?»

«የሴትነት ክብርሽን ነዋ! እርካሽ መሆን የለብሽም።

«ተጋብገሬ የታክሲ ደንበኛዬን መጠበቅ ምን ነውር አለበት።»

«አለበት እንጂ ፋጡማ ፓርኖ ከፍቶ ገላውን እስከሚታጠብ አንቺን ማስቀመጥ ውርደት ነው ወይንስ ከእኔ የምትደብቂኝ ሌላ ምሥጢር አለ?»

«ወላሂ ውስማን ይሙት ምን ደግሞ ከአንቺ የምደብቀው ይኖራል? አንቺ እንደምታስቢው ቢሆን ኖሮ ጫወታውንም አላነሳ ነበር። እመኚኝ እኔማ ሚስቱ ያለች መስሎኝ ገባሁ። ትመጣለች ስለተባለ አምኜ ጠበቅሁ ።ይሄው ነው ታሪኩ። አንቺስ እንዲህ አይነት ሁኔታ አጋጥሞሽ አያውቅም እውነት?»

«በጭራሽ። ቢያጋጥመኝም እኔ ለጅቷ አላረገውም። ደግሞ የግል መኖሪያ ቤት አይነካካኝም። ለእንደዚህ ላለ እርካሽ ነገር አልበገርም። «ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ» ቆዳዬ ቢጠቁር እንደ ማንም ነጭ በቀላሉ

ከብሬን አልሸጥም። ለካ አታውቂኝም ፋጡማ ካልመሰለኝ የአራስ ነብር ነኝ» ብላ አፈጠጠችባት።

«አ! እንግዲህ አትጩሂብኝ ምን ላድረግ ብለሽ ነው?»
«እንዲያው አንቆ ቢያስገድድሽ ምን ታደርጊያለሽ?»
«መስጠት ነዋ። ሌላ ምን አደርጋለሁ»
«ያለ አንዳች ትግል እግርሽን መበርገድ?»
«ከወደቁ በኋላ መፈራገጥ ለመመላለጥ» ሲባል አልሰማሽም?»
«እኔ ሕይወቴ ድብን ትላለች እንጂ በአለኝ አቅም እታገለዋለሁ።»
«ከትግል ምን ጊዜም ዘዴ ይበልጣል ሮዚ።»
«ምን አይነት ዘዴ ነው የምታወሪው።»

«አየሽ ሮዚ የሆነ ሰው ሲያስገድድሽ ስጪው። ምናልባት ያደረገውን አድርጉ ወደደችኝ ብሎ ያላንዳች ጉዳት በነፃ ይለቅሻል። ያለፍታድሽ መደረግ እራሱ ትልቅ ጉዳት ነው እኮ ፋጡማ»

«አውቃለሁ። ግን ከሱ የበለጠ እሱን የምጉዳበት ዘዴ አለኝ።»
«ምን አይነት ዘዴ?»

«ሁኔታው ካለፈ በኋላ ያደረከውን ለሚስትህ እነግርብሃለሁ ብለሽ በማስፈራራት ገንዘቡን እለት በእለት ማስተፋት ነው ዘዴው።»

«ቢገልሽ ወይም በእጅ አዙር ቢያስገድልሽስ?»

«አይመስለኝም። እንኳን ይሄ ተራ ሰው ፕሬዚዳንት ክሊንተን ሞኒካን ማስገደል አልቻሉም። ቅሌታቸውን ተቀብለው ከስምንት አስከ አሥር ሚሊዮን ዶላር ካሣ ለመክፈል ዝግጁ ሆነዋል።»

«ወይ አንቺ ቆዳሽ ለስልሶ ለካ ተንኮለኛ ኖረሻል?»
«ሮዚ ይሄ ተንኮል አይደለም መብትን የማስከበር ግዴታ ነው።»

«ያደረገውን ቅሌት ለሚስቱ ነግረሽ፣ የሰው ትዳር አፍርሰሽ፣ ገንዘብ መቀበል ከተንኮልም አልፎ ወንጀል ነው»

«አየሽ ሮዚ ተንኮል የሚሆነው እኔ አባብዬና አግባብቼ ብዳራው ነበር። ግን እሱ ለኔ ባዘጋጀው ወጥመድ ተጐድቼ ብጐዳው በሰማይ ኩነኔ በምድርም ወንጀል ሊሆንብኝ ጨርሶ አይችልም እመኚኝ»

«እኮ በኋላ መጨረሻው ምን ሆነ በምን ተለያያችሁ?»

«በኋላማ ተጣጥቦ ቡታንቲ ሳያደርግ ብቅ አለ። እኔ ድንግጥ አልኩ ወደ ሌላ ክፍል ሲገባ በሩን ከፍቼ ተንደርድሬ ወጣሁ። በሶስተኛው ቀን ቤቴ ስልክ ደውሎ ይቅርታ ጠይቆ የታክሲውንም ሂሳብ በሌላ ቀን ከፈለኝ።»

ሮዚ «እንኳን በሰላም ተገላገልሽ» ብላት ሰዓቷን አይታ ጊዜው ስለመሸ ገረማት። ወዲያው ሮላንድ ታክሲ ሴንተራል ስልክ ደውላ ከሃያ ደቂቃ በኋላ ጆኒ እፋጡማ ቤት መጥቶ እንዲወስዳት በቅድሚያ አዘዘች።

ፋጡማ የጆኒ ስም ሲጠራ ሰምታ ስለእሱ ሮዚን አንዳንድ ነገር እየጠየቀች የመጨረሻውን ዙር ኮኛክ ከጠርሙስ ውስጥ የቀረውን አንጠፍጥፋ መለኪያዎቹን ሞላች።

«ውይ ጆኒ እንደ ታላቅ ወንድሜ የማያው የማከብረው የሀገሬ ልጅ ለዚህም ሥራ የሞራል ብርታት የሰጠኝ ትልቅ ባለውለታዬ ነው።»

«በቀደም ከጆኒ ጋር ባዝል ተገናኝተን «ሰላም» ብሎኝ እጇን ጥብቅ አድርጐ ይዞ ዓይን ዓይኔን ተመለከተኝ። ምነው ብለው እጅሽ ይሞቀኛል አለኝ። ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም።» ብላ እንደቁብ ዶሮ አስካካች።



«እወድሻለሁ ማለቱ ነዋ» እውነት ፋጡማ ነገሩ ሳይገባሽ ቀርቶ ነው ወይስ እኔን ለማስለ ፍለፍ? ፈልገሽ ነው። ደግሞ ይሄን በማድረጉ ምን ያስቃል?»

«ታዲያ እንደሱ ብሎ ለምን እቅጩን አይናገርም። ጥሎብኝ ዳር ዳር የሚል ሰው አልወድም። አንዳንዴ ደግሞ ይገርምሻል ሮዚ ፊት ለፊት እያየኝ ዘግቶኝ ያልፈኛል። ምን አይነት ባህሪ ነው ያለው?»

«ሽጋ ነዋ አየሽ ፋጡማ ወንዶች ከልባቸው ሲወዱ ኮምተርተር በማለት ይንጠባረራሉ። አልፎ አልፎ ደግሞ ፈገግ በማለት ይፍለቀለቃሉ። ይሄ ያለ የወንዶች ጠባይ ነው። እንዴት አታውቂም?»

«አሃ ለካ ለዚህ ነው ክላውዝ የሚዘባነንብኝ።»

«አይ ክላውዝን ለቀቅ አድርጊው። ይልቅ የሚስማማሽ በኔ ይሁንብሽ ጆኒ ነው። እንዳውም በአሁኑ ጊዜ ብቸኛ ስለሆነ ጥሩ ወዳጆች እንደምትሆኑ አልጠራጠርም» ብላ እየተንገዳገደች ሄዳ የፋጡማን ትከሻዎች ይዛ ወተወተቻት።

ወዲያው የቤቱ ደወል ሁለቴ ተንቃጨለ። ታክሲ እንደመጣ አውቃ ስለ ግብጣው ከልብ አመስግና ሹራቧን ደርባ እየተንገዳገደች ከቤቱ ወጣች። ከአንደኛ ፎቅ ወደታች ቾኩላ ጡብ ጡብ እያለች በችኮላ ወረደች። የበረንዳውን እጀታ ባትይዝ ኖሮ ወድቃ ነበር። እግሮቿን ቀዘቀዟት። ትዝ ሲላት ጫማዋን አላደረገችም። በታከተ ስሜት ወደ ላይ ተመለሰች። በራፉ ላይ ደርሳ የረሳችውን ታኩ ጫማ መልሳ ተጫማችው። ፋጡማ በራፉ ላይ ቆማ በሁኔታው ከት ብላ ሳቀች። ሮዚም የፋጡማን ደረጃዎች በታኩ ጫማዋ እየረገጠች አስቃ ወደታች ወረደች። ቂው! ቃ! ቂው! ቃ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂው! ቂው! ግው! ጋ! አድርጋ ታክሲ ውስጥ ገባች።



ክፍል አምስት

ገሀ ቀደደ። የሰማይና የምድር መንጋጋ ተላቀቀ። ውቂያኖስ የመሰለ የሰማይ ሜዳ የምድርን አድማስ ተንተርሶ የጨገገ ጉም ነክሶ በርቀት ታየ። የአካባቢው ወፎች ከእንቅልፋቸው ነቅተው ተንጫጩ።

የሐምሌ ወር የንጋት ጮራ በምሥራቅ በኩል ብቅ አለች። የተፈጥሮ ሀብቷን የቁንጅና ውበቷን ለማሳየት ተጣደፈች። የብርሃን ፍንጣቂዋን እንደጠበል ከአድማስ እስከ አድማስ ለሁሉም አርከፈከፈች።

የሮዚ የመኝታ ቤት የመስኮት ደማቅ ቢጫ መጋረጃዎች ከውጪ የሚመጣውን የብርሃን ጨረር ለመከላከል ጋሻ ጃግሬ ቆመዋል። ክፍሉ የቀለጠ ወርቅ የፈሰሰበት ወለል መስሏል።

ሮዚ – ለሊቱን በደንብ አልተኛችም። ሰፊው መሐጐኒ አልጋ፣ ሽሙቅ ሽሙቅ የሚለው የስፖንጂ ፍራሽ፣ የሐር አንሶላና የሱፍ ብርድ ልብስ እንደ ስማቸውና ተግባራቸው ሆነው እሷን አቅፈውና አሙቀው በእለቱ አላደሩም። ያ እንደሳሙና የለሰለሰ ጠይም ዓሣ መሳይ ገላዋ ምክንያቱ ባልታወቀ ሰበብ ብቻውን ከወዲያ ወዲህ ሲገላበጥ አድሮ ነጋ። በቀኝ በኩል አራስጌ ከመዲናው ላይ ያለው የመቀስቀሻ ሰዓት ወቅቱን ጠብቆ አባረቀባት ጥርርርር! ጥር...ሮዚ ከእንቅልፏ ባና በደመነፍስ እንቅስቃሴ ሰዓቱን ተጭና አጠፋችው።

ሮዚ ከድሮ ጀምሮ የጠዋት እንቅልፍ እንደጥንቅሽ ይጣፍጣታል። ሰውነቷን ለማዝናናት ተንጠራርታ ተውጠረጠረች። ወደ ግራ ተገላብጣ ተመልሳ በጀርባዋ ተኛች። እፎይ ብላ የሞቀ ትንፋሽ ተነፈሰች። በመስኮቱ መጋረጃ ሾልከው የገቡ ቀጫጭን የብርሃን ዘንጐች በተከደኑ